ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስና የሶሻል ሣይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ደህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የየም ብሔረሰብ የአንገሪ ቤተ-ማግስት ባህላዊ የንግስና ሥርዓት ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና

በ

አያልነሽ ወንድሙ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስና የሶሻል ሣይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ

አያልነሽ ወንድሙ

አማካሪ ለማ ንጋቱ /ዶ.ር/

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስና የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርትክፍል

የድኅረ ምረቃ ሞያ ግብር

የየምብዜረሰብ የአንገሪ ቤተ-ማግስት ባህላዊ የንግስና ሥርዓት ሽግግር

ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና

በ አያልነሽ ወንድሙ

ነሐሴ 2011ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

---------------------------------
-----------------------------

የፈታኝ ስም ፊርማ

----------------------------------
----------------------

-----------------------------------
-----------------------

----------------------------------
------------------------

ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳዘጋጅ በማስተርስ ደረጃ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጥናቴን በሚያማ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ገንቢ አስተያየትና ምክራቸውን በመለገስ ለተባበሩኝ አማካሪዬ ዶ/ር ለማ ንጋቱን ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡ ለጥናቴ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ከማስክ ተገኝቼ እንደሰበስብ ቀና ትብብር ያደረጉልኝን የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊና ሰራተኞች እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ለጥናቴ የሚሆኑ ተገቢ መረጃዎችን በቅንነትና በታማኝነት ውድ ጊዜያቸውን መስዕዋት በማድረግ የሰጡኝን የየም ልዩ ወረዳ አባላት በሙሉ እግዚአብሄር ይስጥልኝ፤ በማለት እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ቀጥሎም ከመረጃ አቀባዮች ጋር በማገናኘትና የትርጉም ስራ በመስራት ከኔ ጋር አቀበት ቁልቁለቱን በመውጣት በመውረድ ከጎኔ ላልተለያችሁኝ የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቼ ለመምህር በድሉ ካሳሁን ፣ለመምህር ምስጋና ፈርዲና ለመምህር አፈወርቅ ገ/ሚካኤል ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡ ብድራችሁን ፈጣሪ ይክፈላችሁ፡፡

በተጨማሪም ለዚህ የትምህርት ደረጃ እንድደርስና በማስተርስ ዲግሪ እንዳልወሰን ማበረታቻና ምክር ለለገሱኝ ውድ መምህሬ ለአቶ ሐብታሙ እንግዳወርቅ ትምህርቴን በምማርበት ወቅት ከጎኔ ሆነው በማበረታታትና በአስፈላጊው ሁሉ በመደገፍ ለረዱኝ ውድ ቤተሰቦቼ ማለትም ባለቤቴ አቶ ሣሙኤል ገ/ሚካኤል፣ ወንደሞቼና እህቶቼ ከነ ቤተሰቦቻችሁ በተለይ ወ/ሮ አስቴር አለሙ ልጆቼን እንደ ልጆቿ አድርጋ በማከባከብ ትምህርቴ ላይ ብቻ እንዳተኩር ለረዳችን ለሁላችሁም ውለታችሁ የማይረሳ ነው፡ እግዚአብሄር ይስጥልኝ፡፡

i

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና››በሚል ርዕስ ከባህላዊ የንግስና ሽግግሩ ጋር ተያይዘው የሚገሩ ተረኮችን ማህበረ ባህላዊ አንድምታ መመርመርን አላማ አድርጎ በማነሳት፣ አላማውን ከግብ ለማድረስና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ በቃለ መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎችን በማሰብሰብና በማስታወሻ ደብተር በመመዝገብ፣ በቪዲዮ ካሜራና በፎቶ ግራፍ በመቅረጽ የተያዘና ምርምሩም በአይነታዊ የምርምር ዘዴ የቀረበ ሆኖ ለጥናቱ የሚረጅ የንድፈ

ሐሰብ መፅቀፍም የጠቀሜታነት ንድፈ ሐሰብ /Functionalism Theory/ በመጠቀም ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በዚህም በአንገሪ ቤተ መንግስት ነገስታት ዙሪያ የተነገሩ 84 ተረኮች ተሰብስበው ከነዚህም መካከል ከጥናት አላማዬና የምርምር ጥያቄዎቼን ከመመለስ አንጻር አብረው በሚሄዱ በ61 ተረኮች ላይ የይዘት ትንተና ተደርጎ የሚከተሉት ውጤቶች ላይ ተደርሷል፡፡

በአንገሪ ቤተ መንግስት ይነግሱ የነበሩት ነገስታት በየም ብሔረሰብ ከሚገኙት ከ300 /ከሶስት መቶ/ በላይ ጎሳዎች መካከል አንዱ የሆነው ‹‹የጫዋ›› ጎሳ አባላት እንደ ነበሩ፣ የዚህ ጎሳ አባላት የንግስናውን ስልጣን ከመያዛቸው በፊት ግን ሌሎች ሁለት ጎሳዎች ንግስናውን ይዘው ይመጡ እንደነበር እነሱም ‹የጋማ ጎሳና የጌመሎ ጎሳ» ተብለው እንደሚጠሩ የእነሱ የንግስና መቀመጫቸውም ሌሎች በታዎች ላይ እንደነበሩና፣ የአንገሪ ቤተ መንግስት ግን የጫዋ ጎሳ ነገስታት መቀመጫ ብቻ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ የጫዋ ጎሳም እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ድረስ 12 የጫዋ ጎሳ ነገስታት ተፈራርቀው የየምን ሕዝብ ያስተዳደሩት መሆኑ በጥናቱ ሊታወቅ ችሏል፡፡

ሌላው ለመረዳት እንደ ተቻለው ነገስታቱ የሚሾሙበት /የሚቀቡበት/ ባህላዊ ስርዓት ያለ ሲሆን ይህም ‹‹በዘር ማፈስ ›› ወይም በወቅቱ ነገስታቱና ህዝቡ ያሚሉኩት ለነበረ‹‹ዓዘ›› መስዕዋት በማቅረብ መቀባት/መሾም/ ሲሆን እስከ ሹመት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ሌሎች ባህላዊ ስርዓቶች እንደ ነበሩ ፣በመጀመሪያ ለንግስና የሚታጨው ወጣት ፣ያላገባና ድንግልናውን ያላፈረሰ በተጨማሪም የሟች ንጉስ ልጅ(የሚሼፈሻ ልጅ) መሆን እንዳለበት፤ ምን አልባት ንጉሡ ልጅ የሌላቸውና ኖረውም ይህንን መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ መስፈርቱን የሚያሟላ የንጉሱ የወንድም ልጅ ተፈልጎ ይመረጥና በቤተ መንግስቱ ዙሪያ ጫካ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፣ በዚህን ጊዜ ነብር ወይም ዘንዶ መጥቶ ሳይተናኮለው ተሻሽቶት ጥሎት ከሄደ ያንን ወጣት የዘር ማፈሱ ለንግስና ሚጠታል ተብሎ ለዓዘው የከብት መስዕዋት ይቀርብና ይሾማል /ይቀባል/፤ ከዚያም ህዝቡን ያስተዳድራል፡፡ ህዝቡም ከፈጣሪ አንደተሰጠ በመቁጠር በታማኝነትና በቅንነት ይታዘዙለታል፡፡ የነገስታቱን የአሚራር ጥበብ ስንመለከት ደግሞ ከላይ ከንገሱ ቀጥሎ አስተሰሮች፣ ከአስተሰሮች ጋኛ፣ ከጋኛ፣ ኤራሾ በሚባሉ ከላይ እስከታች በተዘረጉ መዋቅሮች አማካኝነት ያስተዳደሩ አንደነበር ታውቋል፡፡

ii

**ማውጫ**

**ርዕስ** **ገጽ**

**ምዕራፍ አንድ**-----------------------------------------------------------------------------------------------1

1.1 *መግቢያ*-----------------------------------------------------------------------------------------------1

1.2 **የጥናቱ ዳራ**-------------------------------------------------------------------------------------------2

**የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**-----------------------------------------------------------------------------4

**የምርምር ጥያቄዎች**---------------------------------------------------------------------------------4

1.5 **የጥናቱ ዓላማዎች** ----------------------------------------------------------------------------------5

ዋናዓላማ--------------------------------------------------------------5

1.5.2 ዝርዝርዓላማዎች--------------------------------------------------------5

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ--------------------------------------------------------5

1.7 የጥናቱ ወሰን--------------------------------------------------------6

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት--------------------------------------------------------6

1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች--------------------------------------------------------7

1.9.1 ያጋጠሙ ችግሮች--------------------------------------------------------7

1.9.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች--------------------------------------------------------7

ምዕራፍ ሁለት--------------------------------------------------------9

2 የየም ብሄረሰብ መልክዓ ምድራዊ ፤ ታሪካዊና ማህበራዊና ዳራ----------------------------9

2.1 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት--------------------------------------------9

2.1.1 በየም ልዩ ወረዳ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መስዕቦችር--------------------10

2.1.1.1 የተፈጥሮ ፍል ውሃ --------------------------------------------------------10

2.1.1.2 የአንገሪ ቤተ መንግስት--------------------------------------------------------11





2.1.1.3 ትክል ድንጋዮች--------------------------------------------------------12

2.1.1.4 የተፈጥሮ ዋሻዎች--------------------------------------------------------14

2.1.1.5 የዛቤ ወንዝ ብርብርሳ ፏፏቴ --------------------------------------------------17

2.2. የየም ብሔረሰብ አመጣጥ ታርክ --------------------------------------------------18

2.2.1 የብሔረሰቡ ስያሜ፤ቋንቋና አሰፋፈር --------------------------------------------21

2.2.2 የሕዝብ ቁጥር--------------------------------------------------------23

2.2.3 የየም ብሔረሰብ ኢኮኖሚያዊ መሰረት--------------------------------------------24

2.2.4 የየም ብሔረሰብ ሃይማኖት--------------------------------------------------------25

2.3 ማሕበራዊ ተቋማት--------------------------------------------------------27

2.3.1 ባህላዊ ዳኝነት--------------------------------------------------------27

2.3.2 ባህላዊ የጋብቻ ዓይነቶች--------------------------------------------------------29

2.3.3 የ« ሄቦ» በዓል(የብሄረሰቡ የዘመን መለወጫ በዓል------------------------------------30

ምዕራፍ ሦስት--------------------------------------------------------32

3. ክለሳ ድርሳናት------------------------------------------------------------------------------32
3.1. ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት -----------------------------------------------------------------------32
3.1.1 የተረክ ንድፈ ሀሳብ---------------------------------------------------------------------------32
3.1.1.1 ቃላዊ ዝርው ተረክ(Oral prose narrative)--------------------------------------------32
3.1.1.2. የተረክ ዓይነቶች--------------------------------------------------------------------------36
3.1.1.2.1 ሚት-------------------------------------------------------------------------------36
3.1.1.2.2 አፈ ታሪክ ----------------------------------------------------------------------37
3.1.1.2.3 ተረት-----------------------------------------------------------------------------38
3.1.1.3 የኦክፔውሁ የተረክ አከፋፈል----------------------------------------------------40
3.1.1.3.1 አፈ ታሪክ-------------------------------------------------------------------40

iv

3.1.1.3.2 ገላጭ ተረቶች----------------------------------------------------------------------41
3.1.1.3.3 ፋቡላ-----------------------------------------------------------------------------42
3.1.1.4 ተረክን የማጥናት ጠቀሜታና የአጠናን ስልት--------------------------------------42
3.1.2 ባህል------------------------------------------------------------------------------------43
3.1.3 ባህላዊ አስተዳደር---------------------------------------------------------------45
3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት----------------------------------------------------------50
ምዕራፍ አራት-------------------------------------------------------------------------57
4. የአጠናን ዘዴ-----------------------------------------------------------------------57
4.1 የጥናቱ ዘዴ----------------------------------------------------------------------------57
4.2 የንሞና ዘዴና የመረጃ ምንጮች-------------------------------------------------------57
4.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ---------------------------------------------------------------58
4.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች---------------------------------------------------------59
4.4.1 ቃለ መጠይቅ----------------------------------------------------------------------59
4.4.2 የሰነድ ፍተሻ------------------------------------------------------------------------60
4.4.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት-------------------------------------------------------61
4.5 የመረጃ አደረጃጀት ዘዴ-----------------------------------------------------------61

4.6 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ----------------------------------------------------------------------------63

ምዕራፍ አምስት--------------------------------------------------------------------------------------65

5.የመረጃ ትንተናና ፍከራ-------------------------------------------------------------------------------65

5.1 ባህላዊ የንግስና ሽግግሩን የሚያሳዩ ተረኮች------------------------------------------------66

5.2 ከየትኞቹ ጎሳዎች በምን መስፈርት እንደሚመረጡ የሚያሳዩ ተረኮች-------------------72

5.3 የንግስና አሰጣጡን ባሕላዊ ሥርዓቶች የሚያሳዩ ተረኮች-----------------------------------76

5.4 በቤተ መንግስቱ አመሰራረትና በነገስታቱ ዙሪያ የተነገሩ አፈ ታሪኮች-----------------86

5.5 የባህላዊ ነገስታቱን የአመራር ጥበብ የሚያሳዩ ተረኮች--------------------------------------90

ምዕራፍ ስድስት-------------------------------------------------------------------------------------98

6.የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች----------------------------------------------------------98

6.1 የጥናቱ ማጠቃለያ -------------------------------------------------------------------------------98

v

6.2 የይሁንታ ሐሳቦች-------------------------------------------------------------------------------100


ዋቢዎች

አባሪ 1 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

አባሪ 2 የተሰበሰቡ መረጃዎች(ተረኮች)

አባሪ 3 የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

አባሪ 4 የጥናቱን መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች




የየም ልዩ ወረዳ ማኛ ካርታ (ምንጭየደ.ብ.ብ.ሕ.ክ.መ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ)

viii

መፍቻ ቃላት

1. ማላቆ፡- የጎሳ ስያሜ
2. ሜዬ፡-ባህላዊ አምልኮ

3. ማገ፡-ለዓዘ ማዕዋት አሳራጊ ሰው
4. ሞዋ፡- የጎሳ ስያሜ ሲሆን በአንገሪ ቤተ–ማግስት ይነግስ የነበረው ጎሳ ነው
5. ሰከኩ- የጎሳ ስያሜ
6. ሶኣላ፡-የንጉሱ አፈ ጉባኤ
7. ሼሻካምዓዘ
8. ታቶ፡ – ንጉስ
9. ታቶ ባላሞ – ንጉስ ባለዉልድ የሚጀሚያው የሞዋ ንጉስ የነበሩት
10. አስተሰር ፡- የአስራ ሁለት ጎሳዎች ሚዎች ሆነው የንጉሱ አማካሪዎች ናቸው
11. አንገሪ፡ – ቤተ ማግስቱ ያለበት የቦታ ስያሜ
12. አንገሪ ፎችራ-የቤተ–ማግስቱ ደጃፍ
13. ኤሪሾ፡- የማደር ሚዎች
14. ኤንኪ፡- ለዛር ማፈስ ማዕዋት የሚቆርጠበትና ነገስታቱ የሚቀበበት ቦታ
15. ኦያ ቄዶ፡- የቦታ ስያሜ/አንድ ቀበሌ/
16. ካሻ፡- ዋርካ
17. ካን ፎቻ- የቦታ ስያሜ ሲሆን የጌማሎ ጎሳ ነገስታት መቀመጫ የነበረ ቦታ ነው፡
18. ኬሎ- ጥብቅ ደን የሚገኝበት የሚጨፈሸው የጋማ ጎሳ ንጉስ የተገደለበት ቦታ
19. ኮርቦ፡- የጎሳ ስያሜ
20. ዛር፡-ባዕድ አምልኮ/የሰይጣን ማፈስ እምነት
21. ዛንሶ፡-በነገስታቱ ዘመን ወንጀለኞች ተገፍትረው የሚደለቡት የገደል ስያሜ
22. ዝሜ ኣማ – የቦታ ስያሜ ሲሆን የጋማ ጎሳ ነገስታት መቀመጫ የነበረ ፡፡
23. የሱ፣ አማ ጋዜው፣ አብከሚ ካውም፣ ካንሺሮ፣ ሶአላ ፡-የጎሳ ስያሜዎች
24 .ዲዛይዛዋ ( ሺዛይ ሆራ ) ፍል ውሃ
25 .ጋኛ፡- የየጎሳ ሚዎች /ከ300 መቶ በላይ ጎሳዎች ሚዎች/
26 ጋሜ የጎሳ ስያሜ

xi

27. ጋው ዋሻ

28.ጌማሎ- የጎሳ ስያሜ

29. ፋጋ፡- የጎሳ ስያሜ/የሸክላ ሞተኞች መጠሪያ/

30 .ፎችራ ፡-ደጅ

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 መግቢያ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ የንግስና ስርዓት ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ የሚያሳዩ ተረኮች ይዘት ትንተና ላይ ነው፡፡የአንገሪ ቤተ-መንግስት የሚገኘው በየም ልዩ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ከልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ከሣጃ ከተማ በ32 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከፎፋ ከተማ ደግሞ 3.2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በግሩምና አንገሪ ቀበሌ ውስጥ ይገኛል፡፡በዚህ ቤተ-መንግስትም የተለያዩ ነገስታት ተፈራርቀው ይመሩ እንደነበር ይነገራል፡፡ የአንገሪቤተ-መንግስትስያሜናአመሰራረት እንደ ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ አገላለጽ የጊቤአንገሪ ቤተ-መንግስት የተመሰረተው በጻድቁንጉሥ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት በ1520ዓ.ም እንደነበር ነው፡፡ስለ አመሰራረቱም ጸሐፊው እንዲህ ብለዋል፡፡ጻዲቁ ዮሐንስ ከባለቤታቸውና ከነፍስ አባታቸው ጋር አብረው ሆነው የተጠበሰ ዓሣ እየበሉ እርስ በርሳቸው ይወራረዳሉ፤ውርርዱም እንዲህ በሚል ነው «ዛሬ በዚህ ሰዓት እውነት የተናገረ ሰው ከተገኘ ይህ የተጠበሰ ዓሳ ነፈስ ዘርቶ ወደ ባሕሩም ተጥሎ ይኖራል››፡፡አሉና ውርርዱን ከባለቤታቸው ጀመሩ ባለቤታቸው ግን ለንስሃ አባታቸው ቅድሚያ ሰጡ እሳቸውም እንዲህ አሉ፡፡‹‹ እኔ እሜቴን በጣም አፈቅራታለሁ የነፍስ አባትነት ክብሩ ቀርቶብኝ እሜቴን አግብቼ በደስታ በኖርኩ›› አሉ፡፡እሜቴም በተራዋ ‹‹ እኔም የንግስትነት ክብሩ ቀርቶብኝ የሚወደኝን ሰው አግብቼ በፍቅርና በደስታ በኖርኩ ›› አለች፡፡ጻድቁ ዮሐንስም በተራቸው ‹‹ ይህ ሁሉ የዓለም ዝባዝንኬ ክብሩ፣ሀብቱ፣ሥልጣኑ ሁሉ ቀርቶብኝ እጅግ አስፈሪ ወደ ሆነው ወደ ጊቤ ወርጄ የአንበሳ፣ የነብር፣ የተኩላና የልዩ ልዩ አራዊት መኖሪያ ውስጥ በስጋትና በሰቀቀን በኖርኩ ›› አሉ፡፡ ሁሉም እውነት እውነቱን ሲናገሩዓሣው መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ ንጉሱም ዓሣውን አንስተው በእንጨት ገበቴ ውስጥ ውሃ ሞልተው አስቀመጡትና ወደ ሐይቅ እንዲጣል አደረጉት፡፡ ከዚያም ንጉሱ ወደ ጊቤ አራዊት መኖሪያ ገብተው መንነው መኖር ጀመሩ ቦታው ሰው የማይደርስበት ቦታ ስለነበር እንደ ገዳምም እንደ ቤተ-መንግስትም አድርገው ኖሩበት፡፡

ንጉሱም መጀመሪያ በነበሩበት በጎንደር እስከ ዛሬ ድረስም ጎኑ የተጠበሰ የሚመስል ዓሣ አጥማጆች ሲያገኙ የጻድቁ ዮሃንስ ዓሣ ብለው መልሰው ወደ ሐይቁ ይወረውሩታል ይባላል፡፡ በወቅቱ የንጉሱ ምክትል የነበረው ሰው «ጊዮርጊስ ሐንገሪ» ተብሎ ይጠራ ነበር ይባላል፡፡ የቤተሰቦቹ መጠሪያም የሐንገሪ ንጉሳዊ ቤተሰቦች (Hungarians Royal Family) ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ከጻድቅ ዮሐንስ ሞት በኋላ በነገሰው ንጉስ ሥያሜ ያ ቦታ ሐንጋሪ ተብሎ ተጠራ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስም ቦታው ሐንገሪ ተብሎ ሲጠራ የአካባቢውም ሆነ የቀበሌው መጠሪያ «አንገሪ» ይባላል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች መነሻነት የአንገሪ ቤተ-መንግስት ስያሜውምበዚሁ ጸንቶ ቀረ፤ ባህላዊ ቤተ-መንግስትነቱንም ይዞ እስካሁን ሊዘልቅ ችሏል፡፡ አንባሳደር ምትኩ ነጋሽ፤ (2005፣ 34-35) ጥናቱም ትኩረት አድርጎ የተነሳው በዚህ ቤተ-መንግስት ይነግሱ ስለነበሩ ነገስታት የሚነገሩ ተረኮችን መሰረት በማድረግ ስለ ባህላዊው የንግስናው ስርዓት ሽግግር ይዘት መተንተን ላይ ነው፡፡

## 1.2የጥናቱዳራ

ይህጥናትበስነ-
ቃልዘውግስርከሚመደቡትንውሳንክፍሎችመካከልበተረክላይያተኮረነው፡፡ስነ-
ቃልበስሩሚቶችን፣ቃልግጥሞችን፣ቀልዶችን፣ምሳሌያዊንግግሮችንወዘተእንደሚያካትት ፊቃደ/1991፤2-4/ያስገነዝባል፡፡በተጨማሪምC.Sims(2005:1-2) ሲገልጹFolklore is many things,and it's almost impossible to difine succinetly, It'sboth what folklorist study and the name of the discipline they work within.yes Folklore is Folksongs and legends,It's also quilts,Boy scout badges,high school Marchingband intiations,jolkes holidyfoods and many other thingsyou might or might not expect. በማለትበዘርፉ ብዙ ነገሮች እንደሚካተቱ ያስረዳሉ፡፡

እንዲህ ፎክሎር በማንኛውም መደበኛ ያልሆነ የሐሳብ ልውውጥ ማለትም ፎክሎርን በቃላዊ(Oral and written texts)፣ በቁሳዊ(material) እና በልማዳዊ (customary) ድርጊቶች እንደሚገለጽና፤በተጨማሪም ፎክሎር የዚያ የተገልጋዩ ማሕበረሰብባህል፣አስተሳሰብ፣ባህሪየሚገለጽበትና ሰዎች ስለማንነታቸውና ስለዓለም የሚያውቁበትጥበብነውይላሉ፡፡ Martha C.Sims(2005:1-2)፡፡Dorson(1971:4)የፎክሎር የጥናት መስኮች በአራት ይከፈላሉ፡፡እነዚህም ቃላዊ

ፎክሎር(oral Folklore)፣ ሃገረሰባዊ ልማድ(Social Folk costom) ፣ቁሳዊ ባህል(Material culture) እንዲሁም ሃገረ ሰባዊ ጥበብ (Folk art) ናቸው፡፡ፈ.ቃደ(1991፣10-15)

የፎክሎር አንዱ ክፍል የሆነው የሥነ-ቃል ጥናትም በአፍሪካ መጠናት የጀመረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ እንደሆነና በመጀመሪያFinnegan (1970:17)‹‹Oral literature in Afirica ›› በሚል መጽሐፍ ማሳተሟንና ይህንኑ መሰረት በማድረግ ኦክፔውሁ እ.ኤ.አ /1992/‹‹ አፍሪካን ኦራል ሊትሬቸር›› በሚል ስያሜ አስቀምጠውታል፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለፎክሎር ብያኔ ለመስጠት የሞከሩትና ልዩ ልዩ የስነ- ቃል ዓይነቶችን አሳትመውከምናገኛቸው ቀደምቶች እነ ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/የሱስ፣ ብላታ ጌታ ዕሩይ ወ/ስላሴ፣ እነደብተራ ክንፌ እና ሀጂ የሱፍ አብዱራህማን፣ ባላምባራስ ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል፣ ብላታ ወ/ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ፣ አበበ አይቼ እና ተክላይ ዘወልድ እስከ 1950 ባለው ጊዜ ስነ- ቃል ነክ ስብስብ ካጠኑት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑፈ.ቃደ አዘዘ (1991፣41-43)ያስረዳሉ፡፡

በመቀጠልም ስለዘርፉ ምንነት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡ መቆየታቸውንና በኋላም ዘሪሁን አስፋው (1992፣20) ስነ-ቃል ብለው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሐብት ሆኖ የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድ እና ባህል ማስተላለፊያና የልዩ ልዩ የህይወት መልኮች መግለጫ ኪነ- ጥበብ መሆኑንና ተስተላልፎውም በመነገር፣በመተረት፣በመዜምና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በመከወን መሆኑን አስረድተዋል፡፡

አጥኚዋ በዚህ ጥናትዋ ላይ ፎክሎር ምንም እንኳን በውስጡ አራት የጥናት ዘርፎችን የሚይዝ ቢሆንም ከፎክሎርዘውጎችመካከል አንዱ በሆነውበስነ- ቃል ዘውግ ስር ከሚመደቡ በርካታ ሎሮች መካከል ተረኮች ላይ የምታተኩር ይሆናል፡፡የጥናቷ ዋና ትኩረትምየየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ- መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና ላይ ነው፡፡

የየም ብሄረሰብ የተለያዩ የፎክሎር ሃብቶች ባለቤት ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በጥቂቶቹ ዙሪያ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን ለምሳሌ በመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፣‹‹በየም ብሄረሰብ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ይዘት ትንተና»፣

አያልነሽ ወንድሙ(2006 ዓ.ም) ‹‹የየም ብሄረሰብ ባህላዊ የመስቀል በዓል አከባበርና በበዓሉ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች» ብርሃኔ ቆያስ (2002 ዓ.ም)፣ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍለማ ንጋቱ (1999 ዓ.ም) ‹‹በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና»፣እናደጀኔ እጅጉ (2008) «ባህላዊ የግጭት አፈታት በየም ብሄረሰብ» ፣ የተሰሩ ሲሆን እስከ አሁን ባደረኩት ፍተሻ ግን«የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና» በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ባለመጠናቱ ያለውን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ የጥናቴ ትኩረት ሊሆን ችሏል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህንጥናትርዕስለመምረጥያነሳሱኝሁለትምክንያቶችናቸው፡፡የመጀመሪያውግላዊምክ ንያትሲሆንሁለተኛውአካዳሚያዊምክንያትነው፡፡
ግላዊ ምክንያቴየብሔረሰቡ አባልና በመምህርነት ሙያም በተለያዩ የልዩ ወረዳው አካባቢዎች በስራ ጉዳይ የቆየሁ በመሆኑ ባህሉን በቅርበት ስለማውቀውና በየም ብሔረሰብ ይነግሱ የነበሩ ነገስታትን ታሪክ ዕፎ ለትውልድ የማስተላለፍ ሀሳብም ስለነበረኝ በአማርኛ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ስማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቴን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመስራት ዕቅድ የነበረኝበመሆኑ ነው፡፡ አካዳሚያዊ ምክንያቴ ደግሞ የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ የንግስና ሥርዓት ሽግግር ታሪካዊ አመጣጡንየሚገልጹ ተረኮች ማህበራዊ ደረጃን እንዴት እንደሚፈጥሩና ማጠየቂያ ሆነውእንደሚቀጥሉ ለመመርመር ከነበረኝ ውስጣዊ ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡በየም በርካታ የፎክሎር ዘውጎች ይገኛሉ፡፡ከነዚህም መካከል የተወሰኑት በተለያዩ አጥኚዎች የተጠኑ ቢሆንም በብሄረሰቡየአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ ሥርዓት የንግስና ሽግግር አመጣጥ ጋር የተያያዙ ተረኮች ጋር የተያያዘ ጥናት ባለመኖሩ ይህን ክፍተት በተወሰነ መልኩ ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

የዚህን ጥናት ዋናና ዝርዝር አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ይሰራል፡፡

1.ከየትኞቹ ጎሳዎች ወደ ንግስና ይመጡ ነበር? ምክንያቱስ?

2. በአንገሪቤተ-መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገስታት ወደ ንግስና እንዴት ይመጡ ነበር? መስፈርቱ ምን ይመስላል?

3. ነገስታቱ ከሚመረጡባቸው ጎሳዎች፣ ከአመራረጥ ሂደቱ፣ ከሚከናወኑት ሥርዓቶች ጋር የተያያዙት አፈ-ታሪኮች ማኀበረ -ባህላዊ አንድምታ ምን ይመስላል?

4. በወቅቱ የነበሩት ነገስታት ህዝቡን ያስተዳድሩበት የነበረው የአመራር ጥበብ ምን ይመስል ነበር?

## 1.5 የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.5.1ዋናዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ- መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር አመጣጥ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ማህበረ ባህላዊ አንድምታ መመርመር ነው፡፡

### 1.5.2 ዝርዝርዓላማዎች

1.በነገስታቱና ከሚመረጡባቸው የሞዋ ጎሳዎች ጋር የተያያዙ ተረኮች አሁን ላለው የብሄረሰቡ ማህበራዊ መዋቅር ያበረከቷቸውን አስተዋጽኦዎች ያሳውቃል ፡፡

2. በአንገሪ ቤተ መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገስታት ባህላዊ የአመራረጥ ስርዓትን ይተነትናል፡፡

3. ነገስታቱ ወደ ንግስና ለመምጣት (ለመቀባት) የሚያልፏቸውን ባህላዊ ሥርዓቶች ይተነትናል፡፡

4. በወቅቱ የነበሩት ነገስታት ህዝቡን ያስተዳድሩበት የነበረውን የአመራር ጥበብ ማህበራዊ ፋይዳን ለተተኪውትውልድ ልምድ ይሰጣል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.አንድ ማህበረሰብ በሥነ-ቃሎቹ አማካኝነት ያካበተውን ዕውቀት፣ የህይወት ገጠመኝ ፣እምነት፣ዝንባሌና ባህል ወዘተ በማወቅ ለተተኪውትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡

2.የየም ብሄረሰብ ባህላዊ የንግስና ሥርዓት ታሪክ ምን ይመስል እንደነበር አሁን ላለው ትውልድ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. የብሄረሰቡን ተረኮች ለቀጣይ ትውልድ ሰንዶ ለማስተላለፍና በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ጥናት ለሚያካሂዱ ሌሎች አጥኚዎችእንደ መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

4. የፎክሎር ዘውጎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረሱና እየጠፉ የሚሄዱ በመሆናቸው ጨርሶ ከመጥፋታቸውበፊት ሰንዶ ለማስቀመ፡፡

## 1.7የጥናቱወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን ከቦታ አንጻር በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በየም ልዩ ወረዳ በአንገሪ ቤተ-መንግስት ላይ የተካሄደ ሲሆን በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ 35 ቀበሌዎች መካከል በአራት ቀበሌዎች ማለትም በአንገሪ ቀበሌ ፤በኢዲያ ቀበሌ፤በኦያ ቀበሌና በፎፋ ከተማ ላይ በዋነኝነት ትኩረት ያረገና በተጨማሪም በሌሎች የልዩ ወረዳዋ ቀበሌዎች ማለትም ሣጃ ከተማ ፣ ቶባ ቀበሌና ከሽሊ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ አፈ ታሪክ አዋቂዎችን ጭምር በማካተት መረጃው የተሰበሰበ ሲሆን እነዚህን አካባቢዎች የመረጥኩበት ዋና ምክንያት ስለባህላዊ ንግስናው የሚያውቁ መረጃ ሰጪዎችን አገኛለሁ በሚል እምነት ነው፡፡ጥናታዊ ጽሁፉከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ደግሞ «የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ የንግስና ሥርዓት ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ የሚገልጹ ተረኮች ይዘት ትንተና» ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱየሚያተኩረው የየም ብሄረሰብ የአንገሪ ቤተ-መንግስትባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ የሚገልጹ ተረኮች ይዘት ትንተና ላይ ሲሆን ስድስት ምዕራፎች አሉት፡፡ምዕራፍ አንድ የጥናቱን አጠቃላይ ንድፍ ይዟል፡፡ እነዚህም የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ ዋና ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች፣የምርምር ጥያቄዎች ፤የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ፤የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን፤በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች በቅደም ተከተል የቀረቡበት ነው፡፡በምዕራፍ ሁለት ለጥናት የተመረጠውን ብሄረሰብ አጠቃላይ ዳራ የሚያስተዋውቅ ሲሆን በውስጡም የየም

ብሄረሰብ አመጣጥ ታሪክ፣የብሄረሰቡ ስያሜ ቋንቋና አሰፋፈር፣ የጥናቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣የህዝብ ቁጥር፣የኢኮኖሚ መሰረት፣ የሃይማኖትና ማህበራዊ ኑሮ ሁኔታ ተካቶ ቀርቧል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ክለሳ ድርሳናት የቀረበ ሲሆን በስሩም ጥናቱን ለማከናወን የሚረዳ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ የቀረበበትና እንዲሁም ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ተዳሰዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የጥናቱ ዘዴ ፣የናሙና አመራረጥ ዘዴና የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የመረጃ አደረጃጀት ዘዴና የጥናቱ አተናተን ዘዴ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አምስት የጥናቱ ትንተናና ፍከራ የቀረቡ ሲሆን በምዕራፍ ስድስት ደግሞ የማጠቃያና የይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡በመጨረሻም ዋቢ መጻህፍት፣ልዩ ልዩ አባሪዎችና የተለያዩ ፎቶ ግራፎች ይገኙበታል፡፡

## 1.9በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

### 1.9.1. ያጋጠሙችግሮች

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ከመስክ ተገኝቼ መረጃዎችን ለመሰብሰብበየቀበሌዎቹ በምዘዋወርበት ወቅት የተወሰኑ ችግሮች ገጥመውኛል፡፡ ያጋጠሙኝን ችግሮች ሁሉ እዚህ ማቅረብ ባልችልም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

- ✓ መረጃ አቀባዮቹ በተለያዩምክንያቶች በቀጠሩኝ ቀንና ሰዓት አለመገኘት፡፡
- ✓ በጥናቴ ርዕስ ዙሪያ ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸው በቂ የሆኑ የካልዓይ መረጃ ምንጮችን ያለማግኘት፡፡
- ✓ መረጃ አቀባዮቹ የሚኖሩበት አካባቢ የተራራቀ የገጠር ቀበሌ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእግር ጉዞን የሚጠይቅና ለተሽከርካሪ አመቺ ካለመሆኑ የተነሳ የትራንስፖርት ችግር መታየት፡፡

### 1.9.2. የተወሰዱመፍትሄዎች

ከላይ የተገለፁ ችግሮችን ለመፍታትየሚከተሉትን መፍትሄዎች ወስጃለሁ፡፡

- ✓ ከመረጃ አቀባዮቹ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ደጋግሜ በመሄድ ከስራ ነፃ የሚሆኑበት ቀን እና አጋጣሚዎችን እየጠበቅኩ፣ በትዕግስትና በማግባባት መረጃ ለመሰበሰብ ችያለሁ፡፡

- ✓ በጥናቴ ርዕስ ዙሪያ ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸው በቂ የሆኑ የካልዓይ መረጃ ምንጮችን ለማግኘት ባልችልም ከልዩ ወረዳው ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት በየም ብሄረሰብ ዙሪያ የተጻፉ መጽሀፎች፣ መጽሄቶችና በራሪ ጽሁፎችን በማገላበጥ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡
- ✓ የትራንስፖርት ችግርን ለማቃለል አመቺ በሆኑ ቦታዎች በሞተርሳይክል እየከፈልኩእንዲያመላልሱኝ በማድረግ፣ ሞተር ሳይክልየማይገባበትን ደግሞ በእግር በመመላለስ ችግሮችን በመቋቋም አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍሁለት

## 2.የየምብሄረሰብመልክዓ ምድራዊ፣ ታሪካዊና ማህበራዊዳራ

## 2.1 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ሁኔታ

የየም ብሔረሰብ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ሰሜን ምዕራብ በየም ልዩ ወረዳ የሚኖር ሕዝብ ነዉ፡፡ ልዩ ወረዳው በልዩ ወረዳነት የተመሰረተው በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ የወረዳው የቆዳ ስፋት 724.5 ሄክታር ነው፡፡መገኛውም በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀዲያ ዞን፣በሰሜን ምሥራቅ የጉራጌ ዞን ፣በሰሜን ምዕራብ የኦሮሚያ ክልል የጅማ ዞን ጋር እንደሚዋሰን ከየም ልዩ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የልዩ ወረዳው የመሬት አቀማመጡም በአብዛኛው ወጣ ገባና ሸለቆዋማ ነው፡፡የየም ልዩ ወረዳ መልከዓምድራዊ አቀማመጡ ተራራማና ኮረብታማ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ 930 እስከ 2939 ሜትር ከፍታ ያላቸው አካባቢዎችን ይሸፍናል፡፡ ይህም 20 በመቶው ተራራማ፣ 3 በመቶ ሜዳማ፣ 12 በመቶ ተዳፋታማ ሲሆን ቀሪው 65 በመቶው ኮረብታማ፣ ሰንሰለታማና ወጣገባማ የመሬት ገጽታን የያዘ ነው፡፡ የአፈሩ ዓይነትም 60 በመቶው ቀይ አፈር፣ 25 በመቶው ቡናማ ሲሆን ቀሪው 15 በመቶው ጥቁር አፈር ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ 16 በመቶው ደጋ፣ 73 በመቶ ወይናደጋና 11 በመቶ ቆላማ ቦታዎችን የሚይዝ ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ801-1400 ሚሊ ሜትር ይደርሳል፡፡ ዓመታዊ አማካይ የሙቀት መጠኑም ከ12-30 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መካከል ነው፡፡ ‹‹ቱባ መጽሔት››፣ ቁ.26፣ መስከረም 2010 ዓ.ም.)

የልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ሣጃ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ 239 ኪ/ሜ ፣ከደቡብ ክልል ዋና ከተማ ከሀዋሳ ደግሞ 528 ኪ/ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ በሚወስደው ዋና መንገድ ላይ በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳና በናትሪ ወረዳ መካከል ላይ ይገኛል፡፡በልዩ ወረዳው 35 ቀበሌዎችይገኛሉ ፡፡ ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስዕቦች አንጻር ሲታይ የብርብርሳ ፏፏቴ ፣ የዎማ ፍል ዉሃ ፣ የኩሙል ጥብቅ ደን ፣ የአዋሾ ዱጋዱግ ዋሻ፣ የመሊሳ ትክል ድንጋይና የአንገሪ ቤተመንግስት ይገኙበታል፡፡ (ሸኡ ቁ-2 መጽሔት 2001 ዓ.ም)

## 2.1.1 በየም ልዩ ወረዳዋ የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽመስህቦች

### 2.1.1.1የተፈጥሮፍልውሃ/ዖማ/

የም ልዩ ወረዳ አነስተኛ የባህላዊ፣የተፈጥሯዊና ታሪካዊ የቱሪስት መስህቦች ባለቤት ናት፡፡ከተፈጥሮ መስህቦቿ አንዱ የሆነው የተፈጥሮ ፍል ውሃም እንዳላት ይታወቃል፡፡ለህመም መፈወሻ ተደርጎ የሚቆጠረው የዖማ ፍል ውሃ ለአካባቢው ተወላጆም ሆነ ከሌላ አካባቢ ለጉብኝት ለሚመጣ ቱሪስት መንፈሱን የሚያድስ፣ደስታና እርካታን የሚያጎናፅፍ ነው ፡፡ ከዚህም ባሻገር ለኢኮ ቱሪዚም ምቹ መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ዘርፍ ለሚሰማራ አካል ጥሩ አጋጣሚ የሚፈጥርለት ይሆናል፡፡የዖማ ፍል ውሃ ከክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ 586 ኪ.ሜትር ከወረዳው ከፎፋ ከተማ 31 ኪ.ሜትር በወረዳው ደቡባዊ አቅጣጫ ባለው ሶሩናጎን ቀበሌ ጫፍ እና ለጊቤ ወንዝ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ነው ፡፡ ይህፍልውሃ ከመጠን በላይ የሚያቃጥል ስለሆነ ሰዎች ሲጠመቁ እንኳን አጠገቡ ካለው ቀዝቃዛ ውሃ ቀላቅለው እየበረዙ ካልሆነ የማይደፈር ነው፡፡ ፍል ውሃው የተለያዩ ደዌዎችን የመፈወስ ሀይል ያለው ሲሆን ከእነዚህም ለቁርጥማት ፣ለወገብ ህመም ፣ለእከክ ፣ለአላርጂክ፣ ለቆላ ቁስል ፣ለካንሰር ፣ለምግብ አለመስማማት ፣ለጨጓራ፣ለሆድ ውስጥ ጥገኛ ህዋሳት ፈዋሽ እንደሆነ ይነገራል ፡፡በዚህም ምክንያት መጠኑ ሰፊ የሆነ ህዝብ በየአመቱ በጳጉሜ ወቅት ከተለያዩ ቦታዎች ከአጎራባች ወረዳዎች እና የወረዳው ህዝብም ከህመሙ ለመፈመስ ወደዚሁ ፍል ውሃ ይመጣል ፡፡ሌላው የዖማ ፍል ውሀ ማራኪ ገጽታ አለው፡፡(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶ ግራፍ አንድ  የዎማን ፍል ውሀ ሰዎች ሲጠመቁ

### 2.1.1.2.የአንገሪቤተ- መንግስት

የአንገሪ ቤተ-መንግስት የሚገኘው በየም ልዩ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ከልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ከሣጃ ከተማ በ32 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከፎፋ ከተማ ደግሞ 3.2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በግሩምና አንገሪ ቀበሌ ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ ቤተ-መንግስትም የተለያዩ  ነገስታት ተፈራርቀው ይመሩ እንደነበር መረጃዎች ተገልጿል፡፡ (የየም ህግሥርዓት፤ አምባሳደር ምትኩ ነጋሽ፤ (2005፣ገጽ34-35 )



ፎቶ ግራፍ ሁለትየአንገሪ ቤተ መንግስት

## 2.1.1.3ትክልድንጋዮች

### ሀ. የዞፍካርትክልድንጋዮች

ድንጋዮቹ ከየት መጡ? መቼ ተተከሉ ? ለሚለው በቂ መረጃ ባይገኝም፤ ቦታው የመቃብር ቦታ መሆኑና ከአህመድ ግራኝ ወረራ ጊዜ በፊት እንደተተከሉ በአባቶች ይነገራል፡፡በሂደት ይህ ቦታ ታላቅ የየም አምልኮ ቦታ /በአካባቢው አጠራር «ኦያካም»/ ሆኖ እስከ ደርግ ዘመን ድረስ መቆየቱን የአካበቢው ታሪክ አዋቂዎች ይገልፃሉ፡፡ የተለያዩ ርዝመት ያላቸው ድንጋዮች ሲኖሩ ትልቅ የሚባለው ቁመቱ 2.63 ሜትር ሲሆን ትንሹ 51 ሴ.ሜትር ነው፡፡ ይህ ትክል ድንጋይ በፎፍ ከተማ ቀበሌ አስተዳር ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ከወረዳው ፎፉ ከተማ 1.5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምሥራቅ አቅጣጫ ይገኛል።(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶ ግራፍ ሦሥትየዞፍካር ትክል ድንጋዮች

## ለ.የመሊሳትክልድንጋዮች

እነዚህ ትክል ድንጋዮች የሚገኙት በኢዲያ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡ትልቁ 2.6 ሜትር የሆነው ድንጋይ የተተከለው በሼ ድንቡል/የመጀመሪያው የጋማ ንጉስ/ መካነ መቃብር ላይ ሲሆን ሌሎቹ ድንጋዮች በዚህ በሼ ደንቡል መቃብር አጠገብ /ዙሪያ/ የሌሎች ሰዎች መቃብሮች እንዳሉ በማስመስል የተተከሉ መሆናቸውን አባቶች ይናገራሉ፡፡(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶግራፍ  አምስትየመሊሳ ትክል ድንጋዮች (የንጉሥ የሼህ ድንቡል መቃብር)

### 2.1.1.4 የተፈጥሮ ዋሻዎች

### ሀ. የመለካ የተፈጥሮ ኩሩሚኒ ጋው/ዋሻ/

ይህን የተፈጥሮ ዋሻ በጥንት ጊዜ የአከባቢው ሰዎች ለመኖሪያነት ይጠቀሙበት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ዋሻውበወረዳው ምስራቃዊ አቅጣጫ በመለካ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ከልዩ ወረዳው ፎፋከተማ  ያለው ርቀት ደግሞ 3.8 ኪ.ሜ ነዉ፡፡ ዋሻው የጎን ስፋቱ 8.5ሜ.፣ቁመቱ 1.5ሜ.ሲሆን፤ ጥልቀቱ ደግሞ 59ሜ.ነው፡፡ዋሻው በደን እና በተለያዩ ቁጥቋጦዎች የተከበበ ነው፡፡(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶ ግርፍ ስድስትመለካ የተፈጥሮ ኩሩሚኒ ጋው/ዋሻ/

## ለ. የአንገሪ የተፈጥሮ መሽ ጋው/ዋሻ/

መሽጋው (ዋሻ) የሚገኘው ጎሩምና አንገሪ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን በጥንት ጊዜ በነበሩት ጦርነቶች ጊዜ ሰዎች ከብቶቻቸውና ልጆቻቸውን በዚህ ዋሻ ውስጥ በመሸሸግ ከጠላት ጥቃት የሚያድኑበት እንደሆነ ይነገራል ፡፡ ይህ ዋሻ ከየም ልዩ ወረዳ  ፎፋ ከተማ ምሥራቃዊ አቅጣጫ በ3.867 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የዋሻው ጥልቀት 19 ሜትር፣ ቁመት 3 ሜትር ፣ ስፋት 8 ሜትር ነው፡፡ ይህ ዋሻ ከአንገሪ ቤተ መንግሥት 3.956 ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶግራፍ 7የአንገሪ የተፈጥሮ መሸጋው(ዋሻ)

## ሐ.የአንገሪየተፈጥሮቺላንጋው (ዋሻ)

ይህን ዋሻ የአካባቢው ሰዎች የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማለትም እህል የተለያዩ የእርሻና የአደን መሳሪያዎች እያኖሩባቸው ሲጠቀሙባቸው እንደነበር የተየያዩ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ይህ ዋሻ የሚገኘው በጉሩምና አንጋሪ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን ከየም ልዩ ወረዳው ከፎፋ ከተማ ሰሜናዊ አቅጣጫ በ3.7 ኪ.ሜ ላይ የሚገኝ ነው፡፡የዚህን ዋሻ ገጽታ በተመለከተ ጥልቀቱ 19.50ሜና ስፋቱ 8ሜ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳል፡፡ (የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶ ግራፍ ስምንትየአንገሪ የተፈጥሮ ችላን (ዋሻ)

## 2.1.1.5የዛቤወንዝብርብርሳፏፏቴ

ይህ ፏፏቴ ከልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ከሳጃ 3.3 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆንእርሱም ከጅማ አዲስ አበባ በሚወስደው ዋና መንገድ 658 ሜትር ርቀት በስተግራ ገባ ብሎ የሚገኝ ነው፡፡በወረዳው ሰሜናዊ አቅጣጫና በሳጃ ማረሚያ ቤት ግርጌ የሚገኝ የወረዳው ቀበሌ በሆኑት አሼና በሳጃ ላፍቴን መካከል ያለና ዙሪያው ለምለም በሆኑ ቁጥቋጦዎች የተከበበ ነው፡፡ወደ ፏፏቴ ጠጋ ሲሉ የተለያዩ ሳቢና ማራኪቁጥቋጦዎችና ከዚያም ወረድ ሲሉ ከረጅም ርቀት እየተወረወረ የሚወርደውን የዚህን ፏፏቴ ውሃ ነው፡፡እርሱም እጅግ ማራኪና ሳቢ የተፈጥሮ ሐብት ነው፡፡(የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ት ሚያዝያ 10/2011 ዓ.ም)



ፎቶ ግራፍዘጠኝየዛቤ ወንዝ ብርቡሳ ፏፏቴ ገጽታ

(ምንጭ፣[1] የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት፣የቱ/መ/ጥ/ል/ግ/ ዳይሬክቶሬት ሳጃ፡፡ሚያዝያ10/2011 ዓ.ም)

## 2.2የየም ብሂረሰብአመጣጥታሪክ

የየም ብሂረሰብ ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ በማያሻማ መልኩ የሚገልጽ የታሪክ ወይም የምርምር ሰነድ ማግኘት አልተቻለም ፡፡ ለዚህም የታሪክ ሊቅ በመባል የሚታወቁትጸሐፊ ተክለጻዲቅ የጃንጀሮ /የየም/ ታሪክ በውጭ የታሪክ መጻሕፍት ላይበሰፊው የተጻፈ ስለሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አልተካተተም፤በማለት የኢትዮጵያ ታሪክ የስድስት ነገዶች ታሪክ መሆኑን በመግለጽ አመላክተዋል፡፡የየም

[1] ‹‹ ጃንጀሮ ›› ይህ ስያሜ ሌሎች ብሂረሰቦች ለየም ብሂረሰብ የሰጡት ስያሜ ነው፡፡

ሕግ ሥርዓት፤ (2005፣13)፡፡ ነገር ግን በብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችንና የብሔረሰቡን ታሪክ አዋቂ አዛውንቶች ቃላዊ ትረካዎች መሰረት በማድረግ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲ አጥኚዎች ጥናት ላይ መሰረት ተደርጎ እንደቀረበው የብሄረሰቡ አመጣጥ ከየመን ወይም ከደቡብ ዓረቢያ ባልታወቀ ጊዜ ነው ይላሉ፡፡ለአብነትም ቀጣዩን ሃሳብ ብንመለከት

Various historians explains different ideas concerning to the origins of Yem people. Many historians agree in that the original homeland of the Yem people as Yemen and Saudi Arabia. The others also explain that the Yem people are indigenous people to their present day land who established their own political administration in the South Western part of Ethiopia. /S.N.N.P.R Bureau of Culture and Tourism 2017:9/ በማለት

ያስቀምጣል፡፡በሌላ መልኩ ደግሞ የዘጠነኛ ክፍል የታሪክ መጽሐፍ በ(2005፣26 )እንደ ተገለጸው ይህ ብሄረሰብ ባለበት አካባቢ ነባር የሆነና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የራሱን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስርዓት/መዋቅር /ለዘመናት ዘርግቶ የኖረ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የብሄረሰቡ ታሪክ ዓዋቂ አዛውንቶች ደግሞ ስለብሄረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡የየም ብሄረሰብ መጠሪያ «የም»ቋንቋቸውም «የምሳ»እንደሆነና የሰፈሩትም በአሁኑ ወቅት ጊቤ ወንዝ ዙሪያ እንደነበር፡፡የሚኖሩበትንም አካባቢ «የንጋር»/የየሞች ሃገር/ በማለት ሲጠሩት እንደነበረና ታሪካዊ የነገስታት ቤተ-መንግስት ማዕከል አድርገው ሲጠቀሙበት እንደኖሩ Getachew Fule. (1985). በተጨማሪም ታሪክ አዋቂዎች ለምሳሌ ሊቀ ስዩማን በቀለ ወ/ዮሐንስ ሊቃውንት ዘየም፣ አቶ ሀይሌ ቀልቢ፣ አቶ ማሞ ማና ፣ አቶ ባዩ ናኖ ወዘተ የሀገር ሽማግሌዎች በዚህ ሐሳብ እንደሚስማሙ የየም ሕግ ሥርዓት መጽሐፍ አዘጋጅ አምባሳደር ምትኩ ነጋሽ(2005 ዓ.ም) እና የየም ልዩ ወረዳ ማስታወቂያና ባህል ቱሪዝም ጽ/ቤት (2000 ዓ.ም) ሸኡ ቁጥር 1 መጽሔት ይገልጻሉ፡፡

ከመካከለኛው ምስራቅ ፈልሰው በደቡብ አረቢያ ወይም በየመን አድርገው በተለያየ ጊዜ ወደ አሁኑ መኖሪያ ስፍራቸው እንደመጡና በሌላም በኩል በጎንደር አደርገው

አሁን ወዳሉበት አካባቢም የመጡ እንዳሉም ዮሐንስ ወ/ማሪያም(2004፣17) ‹‹የዓለምታሪክ ከጂኦግራፊ ጋር›› የሚለውን ዋቢ በማድረግ (የየም ብሔረሰብ ታሪክ ያስረዳል፡፡

የመጀመሪያዎቹ በደቡብ ዓረቢያ ወይም በየመን አድርገው የመጡት የብሄረሰቡ መሪ የነበሩት ሼህ ድንቡል ከሶስት ወንድሞቻቸው፣ከእናታቸው፣ ከወታደሮቻቸው፣ከአማካሪዎቻቸውና አብሮ ተጓዥ ዎቻቸው ጋር እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ከሼህ ድንቡል ጋር የመጡት ሶስቱ ወንድቻቸው ሼህ መሃመድ ነጋሽ፣ሼህ አረጅና ሼህ በረካ ሲሆኑ እናታቸውም ኢሪ ሱዳን ይባላሉ፡፡በመቀጠል ሶስቱ ወንድማማቾች ወደተየያዩ አካባቢዎች ሲሄዱ ሼህ ድንቡልና እናታቸው ከወታደሮቻቸውና አማካሪዎቻቸው ጋር ሆነው በአሁኑ የየም ግዛት በመቅረት የመጨረሻው የጋማ ሥርወ- መንግስት ንጉስን ከስልጣን በማስወገድ የራሳቸውን አስተዳደር በየም መሰረቱ፡፡በዚህም መልኩ ራሳቸውን የመጀመሪያው «የጌመሎ»ሥርወ-መንግስት ንጉሥ አደረጉ፡፡

ሼህ ድንቡል ወደ አካባቢው ከመምጣታቸው በፊት «የጋማ»ጎሳ ንጉሥ ያስተዳድር እንደነበርና በሃይል ስልጣኑን እንደተነጠቀም ይገልጻሉ፡፡ሼህ ድንቡል ስልጣን ላይ የነበረውን የጋማ ንጉሥ ጥለው ስልጣን ሲረከቡ በወቅቱ እዚያ የነበሩና ከሳቸው ጋር በመሆን ሲታገሉ የነበሩት የጦር አባላት የቱን-ጋማ ፣የዋሳም፣የየሳም፣የካንሽሮ፣የካዝናሮ፣ የዲቻነጉና፣የዎን ጎሳ እንደነበሩና እነዚህ ጎሳዎች እስከዛሬ ድረስ የብሄረሰቡ የጎሳ አባላት መሆናቸው በሰፊው እንደሚታወቅ የየም ብሔረሰብ ታሪክ (2004፤16) ይገልጻል፡፡

በተጨማሪም ከእስራኤል በደቡብ አረቢያ/የመን/፣ከዚያም በጎንደር በኩል አድርገው ባለወልድ በተባሉ የሃይማኖት አስተማሪና የፖለቲካ መሪ የተመራና ሶስት ወንድሞቻቸውን፣አማካሪዎቻቸውንና ወታደሮቻቸውን የያዘው ሌላኛው ቡድን በጉራጌ አድርጎ፣የጊቤን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ ወደ አሁኑ የየም ግዛት እንደገባ ይነገራል፡፡እነዚህ አራት ወንድማማቾች ባለወልድ፣ዋዛም፣ጉልማሾና፣ፉጋ-ቴስቶ ሆነው በአካባቢው ከደረሱ በኋላ በወቅቱ የነበረውን አስተዳደር በመጣል ባለወልድን የየምመሪ በማድረግ ህዝቡን ገዝተዋል፡፡በዚህም ባለወልድ የመጀመሪያው የሞዋ ሥርወ-መንግስት ንጉስ በመሆንሥርወ-መንግስቱን መሰረቱ፡፡በሌላ በኩል ዮሃንስ ወ/ማሪያም(1936 ፤127-130 ) ላይ የየም ህዝብ ከእናሪያ ቤተሰብ ወይም ግዛት

ውስጥ ነበር ይሉና፣ህዝቡም የካም ነገድ ወገን መሆኑን ያብራራሉ፡፡በዚሁ መጽሃፋቸው በወቅቱ የእናሪያ ህዝብ የካም ነገድ እንደሆነና ኋላ የዩቅጣናውያን ነገድ ከአረብ የመን በመግባት በኃይል ወርረው የነገደ ኩሳንን መንግስት ወርሰው ፣ህዝቡን አጥፍተው ፣ቀሪውን አስገብረው እንደኖሩ ያብራራል፡፡ እንዲያም ሲል የእናሪያ ህዝብ በኢትዮጵያ ደቡብ ዳር ለዳር የወላይታ፣ የሲዳማ፣ የጻውሮ፣ የኮንታ የአማሮና በየም ህዝቦች እንደሆኑ ይዘረዝራል፡፡በመቀጠልም ይህ መጽሃፍ ሲያብራራ ኦሮሞዎች አስቀድሞ አካባቢውን ከመያዛቸው በፊት ሎቅማ፣ጅማ፣ ሰቃ፣ትቤ፣ካፋ ከተሞች የቤንያማዊ ንጉስ አቤል ያስተዳድራቸው እንደነበር ይገልጻል፡፡

የቤንያማዊ ንጉሥ ከእስራኤል ነገዶች መካከል አንዱ ሲሆን ይህ የቤንያም ንጉስ አቤል አገሩም እናሪያ ፣ዙፋኑም ከወርቅ የተሰራ ነበር፡፡ይህ ንጉስ በነገስታት ንጉስ ይገዛ እንደነበር ይገልጻል፡፡የእናሪያ ነገስታት ንጉሥ የሚመረጠውም ከዣንዠሮ /የም/ ነው፡፡ «ዣን» እና «ዠሮ»ከሚሉ ሁለት የአረብኛ ቃላት የተዋሃደ ቃል ሲሆን«ዣን»ማለት አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያለው ማለት ሲሆን «ዠሮ»ማለት ደግሞ የጥንት ፣ቀደምት ዮሐንስ ወ/ማሪያም(1936 ፣127-130) ይገልጻል፡፡በሌላ መልኩ ስለ የም ብሄረሰብ ታሪክ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ የተጠና ጥናት ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ዣንዠሮ ማለት የጥንት ግርማ ሞገስ ያለው አስፈሪ ንጉሥ ማለት ነው፡፡እ.ኤ.አ በ1929"coalbo" እና በ1814"World History" በሚል ርዕስ የታተሙት መጻህፍት ይገልጻሉ፡፡

## 2.2.1 የብሄረሰቡ ስያሜ፣ ቋንቋና አሰፋፈር

የየም ብሄረሰብ ራሱን«የም»ወይም«የማ» ብሎ ይጠራል፡፡የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥናት ተቋም አጎራባች ህዝቦች ለብሄረሰቡ የሚሰጡትን ስያሜ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ካፋዎች «ያነጋሮ» ብለው ሲጠሩት፣ጉራጌዎች ደግሞ«ዛንጌሮ»የሚለውን ስያሜ ለብሄረሰቡ መጠሪያነት ይጠቀሙበታል፡፡አጎራባች ህዝቦች እነዚህን ስያሜዎች ለመጠቀማቸው ምክንያት «የንጋር» የሚለው የአካባቢ መጠሪያ ቀጥተኛ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ይገመታል፡፡ይህ ተቋም በመቀጠልም ሲገልጽ ብሄረሰቡ ከየም/ከፖለቲካ ማዕከሉ/ በተጨማሪ በሰቃ ጨቆርሳ፣ በዴዶ፣ በሰኮሩ፣ በማና፣ በቀርሳ፣ በኦሞ ናዳ፣በጥሮ አፈታ፣በሊሙ ሰቃ፣ሸቤ፣በጅማ ከተማ፣በሃዲያና

በጉራጌ ዞኖችና በሌሎች አካባቢዎችም በብዛት እንደሚገኙ ይገልጻል፡፡የየም ብሄረሰብ *ታሪክ* (2004፣ 5 ዓ.ም)

በእርግጥም ብሄረሰቡ የሚታወቅበት «ጃንጅሮ»የሚለው ስያሜ ትርጉም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በብሄረሰቡ አባላት የሚታወቀው «የም»ወይም«የማ» በሚለው እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም የብሄረሰቡ አዛውንቶች እና የተጻፉ መረጃዎች እንደሚያስረዱት ብሄረሰቡ«ጃንጀሮ» እየተባለ የሚጠራው ከሶስት ምክንያቶች ጋር ሊገናኝ እንደሚችል ያሳያል፡፡በሄማት ስትራቤ እ.ኤ.አ (1954÷56) የጃንጀሮ ጎሳዎች ይህም በጥንት ከፍተኛ ዝና የነበረው አንድ «ጅሮ»የሚባል ሰው በጎንደር አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ ይህሰው ሶስት ልጆች ሲኖሩት ከልጆቹም መካከልም «ጃን»የሚባለው ከጎንደር ፈልሶ ወደ አሁኑ የየም ግዛት እንደገባ ይነገራል፡፡በየም ግዛት ለመታሰቢያነት የሚሆን ሰፋፊ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ ተክሎ እንደነበር ከቆይታ በኋላ ወደ ስልጣን ሲመጣ አካባቢውንም የራሱና የአባቱን ስም በማዋሃድ «ጃን ጅሮ»በማለት መሰየሙ ይነገራል፡፡በሌላ መልኩ የጃን ተክል ለአባቱ መታሰቢያነት በጎንደር ተክሎ ወደ አሁኑ የየም ግዛት እንደመጣ ይነገራል፡፡ከዚህም የተነሳ ብሄረሰቡ «ጃንጅሮ»ተብሎ እንደተጠራ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ የጥንት የእናሪያ መንግስት «ዣንዠሮ» የሚባል የንጉሶች ንጉስ ነበረው፤ በወቅቱ የኢናሪያ መንግስት መቀመጫው በአሁኑ የየም ግዛት ውስጥ እንደነበርና ከዚህም ተነስተው ብሄረሰቡን «ዣንዠሮ»በሚል ስያሜ እንደጠሩት ይነገራል፡፡በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ ዮሐንስ ወ/ማርያም፣የአለም ታሪክ ከጂኦግራፊ ጋር በሚለው መጽሃፋቸው«ዣንዠሮ» የሚለው ቃል የሁለት የአረቢኛ ቃላት ውህድ ሲሆን «ዣን»ማለት አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያለው ማለት ሲሆን«ዠሮ»ማለት ደግሞ የጥንት/ቀደምት/መሆኑንና የሁለቱ ቃላት ትርጉምም «የጥንት፣ቀደምት ግርማ ሞገስ ያለው ንጉስ ማለት ነው ይላሉ፡፡ብሔረሰቡ ከቀድሞ ከንጉሱ ሥርዓት እስከ ደርግ ሥርዓት ድረስ ጃንጅሮ በሚል ስያሜ ሲታወቅ የነበረ ቢሆንም የቃሉን መሰረታዊ ትርጉም ባለመረዳት እንደ ስድብ ጭምር በለሌሎችም የሚቆጠርና የሚገለጽ ስለሆነና ማህበረሰቡም ከጥንትም ጀምሮ እራሱን « የማ» ብሎ የሚጠራ በመሆኑ እና ጥናቶችም እንደሚያመለክቱት ጃንጀሮ የብሄረሰቡ ስያሜ ሳይሆን የአካባቢው ስያሜ እንደሆነ በመረጋገጡ ሊቀየር ችሏል ይላሉ፡፡

The Yem people were first mentioned in 1420 under the name Janjero in the victory songs of king Yishak (1412-1427) of the Christian kingdom of Ethiopia as paying tribute in the form of horses to the king (Huntingford, 1955:131) Janjero is the name of the land and not the people./S.N.N.P.R Bureau of Culture and Tourism 2017:2/

በተጨማሪም በአዲሱ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት (1987ዓ.ም) ላይም ተመዝግቦ የሚገኘው የብሄረሰቡ ስያሜ«ጃንጀሮ»ከሚለው ወደ‹‹የም›› በሚለው ተቀይሮ እንዲጸና ተደርጎዋል ፡፡(የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ሕገ መንግስት (አንቀጽ ፴፺ ፤1)
የየም ቋንቋን በተመለከተ G.W.B Habting ford (1995 G.C). የተሰኘው መጽሃፍ በመጥቀስ የብሄረሰቡን ቋንቋ «ከኦሞቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ክፍል የሚመደበው የጃንጀሮ ቋንቋ በስነ ምዕላድም ሆነ በስነ-ድምጽ ከሌሎች የኦሞቲክ ቋንቋዎች የተለየና የራሱ አመዳደብ አለው» በማለት ይገልጻል፡፡(የየም ህግ ሥርዓት 2004 ዓ.ም፣8)በተጨማሪምየየም ቋንቋ «የምሳ» የሚባል እንደሆነና ከምዕራብ ኦሞቲክ ቋንቋ ቤተሰብ ጊሞጃን ከሚባለው ንዑስ የቋንቋ ክፍል ውስጥ የሚካተት ንዑስ የቋንቋ ክፍል ከየም ቋንቋ በተጨማሪ ጊሚራና ኦሜቶ የተሰኙትን ቋንቋዎች ያካትታል ሲል( Bender 1976:311-312) ይገልጻል፡፡

### 2.2.2የሕዝብቁጥር

የየም ህዝብ በልዩ ወረዳው ካለው ይልቅ ከአስተዳደራዊ ክልሉ ውጭ ያለው ቁጥሩ እን ደሚልቅ ይነገራል፡፡ ለማ (1999፣22 ዓ.ም) የጌታቸው (1995፣እ.ኤ.አ)ን መረጃ በመጥቀስ እንዳመለከቱት የብሄረሰቡ አባላት በስነምህዳር ችግርና በመሬት ጥበት ምክንያት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ለስደት ስለተዳረጉ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሚኖሩት ከወረዳው ውጪ እንደሆነ ነው፡፡ በ1976 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት በየምና ባህሉ መጽሔት (1987 ዓ.ም.) የወረዳው ህዝብ ብዛት 340,949 እንደሆነ መገለጹንና በተመሳሳይ ወቅት የተካሄደውን የፌዴራል ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ በጌታቸው (1995. እ.ኤ.አ.) በሀገሪቱ 115,906 የብሄረሰቡ አባላት እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ደርብ (2004፣እ.ኤ.አ) በ1994 ዓ.ም. የፌደራል የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃን ዋቢ በማድረግ የብሄረሰቡ መረጃ

በጎሳ ደረጃ ወደ 267,570 እንደሚደርስ መግለጹንና እሱም ቢሆን በተመሳይ ወቅት ከተካሄደው ህዝብና ቤት ቆጠራ ቢሮ ያገኘው መረጃ በወረዳው ያለው የብሄረሰቡ ቁጥር 64,852 መሆኑን የገለጸበትን የተለያዩ አሃዛዊ መረጃዎችን ማግኘቱን ለማ (1999፣21) ያስገነዝባሉ፡፡

ከደቡብ ክልል መንግስት ስነ-ህዝብ ቢሮ የተገኘው የ1996 ዓ.ም መረጃ ደግሞ የብሄረሰቡ ቁጥር 87,009 መሆኑን እንደሚያስረዳ ይጠቁሟል፡፡ ለማ የአሃዞ ቹን መለያየት በተመለከተ ከመረጃ አቀባዮች ባገኘው መረጃ እንደገለጸው የብሄረሰቡአባላት በአጎራባች የኦሮሚያ ወረዳዎች በብዛትስለሚኖሩ ቁጥራቸውን በትክክል ለማወቅ ያስቸግራል የሚል ነው፡፡

በ1999ዓ.ም. በተካሄደው ብሄራዊ የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት ደግሞ የልዩ ወረዳው ህዝብ ብዛት 80,524 እንደሆነ ነው፡፡ ብሄረሰቡ በተባሉት ስነምህዳርም ሆነ በመሬት ጥበት አሊያም በሌላ ምክንያት በሰፈራ መልክ ወደ ሌላ አካባቢ የተሰደደበት ጊዜን የሚያመላክት መረጃ ግን አላገኘሁም፡፡ የሀገራችን የህዝብ ቁጥር ዕድገት በየዓመቱ የሚጨምር ሆኖ ሳለ የህዝቡ ቁጥር በነበረበት እንኳ ከመቆየት ይልቅ በከፍተኛ ቁጥር የሚቀንስ አሃዝ የማሳየቱን ምክንያት በትክክል ለማወቅ ጥናት የሚያሻው ይመስላል፡፡ (ደመቀ ጀንበሬ 2011 ዓ.ም)

የየምብሔረሰብየሕዝብቁጥርብዛትበ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብናቤቶችቆጠራመረጃመሠረትአጠቃላይየሕዝብብዛት 80687 መሆኑንያስረዳል፡፡ከዚህቁጥርዉስጥ 40566 ወንዶችሲሆኑ 40121 ሴቶችእንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ምንጭ(The 2007 population and housing censes of Ethiopia part one page 9)

### 2.2.3የየምብሔረሰብየኢኮኖሚመሠረት

የብሔረሰቡኢኮኖሚ በአብዛኛው የተመሠረተው በግብርናላይ ነው፡፡የግብርና ውጤቶች ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም ባሻገር በአርብቶ አደርነትም የሚተዳደር ማህበረሰብ ነው፡፡ እንሰት ለየም ማህበረሰብ ሁለንተናዊ የኑሮ መሰረት ነው፡፡ ከእንሰት ከሚዘጋጁ ምግቦች በብሄረሰቡ ቋንቋ (የምሳ) አጠራር ዎቶ፣ ናቱ፣ ዳኢ፣ ባራሳ(ባራሲኛ)፣ ኡዋ፣ ኬራ፣ እርካ፣ ይባላሉ፡፡ ከእንሰት ከሚሰሩ የቤት መገልገያ

ቁሳቁሶች እንደ ሾሮዶ(ባህላዊ የልብስ ሳጥን)፣ ኦፖ(ጂባ)፣ ጋዱ(ገመድ)፣ የመሳሰሉትን በመስራት ከማህበራዊ ጠቀሜታቸውም ባሻገር ብሔረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ያገኛል፡፡ ይህ ህዝብ የእንሰት ውጤቶችን ለምግብነት በመጠቀም ለገቢ ምንጭነት የተለያዩ የእህል፣የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን የሚያመርት ሲሆን እንደየሚኖርበትአካባቢ፣እንደአየርንብረቱሁኔታናየመሬትአቀማመጡየተለያዩየሰብልም ርቶችንያመርታል፡፡በደጋማው ክፍልጤፍ፣ስንዴ፣ገብስ፣አጃናባቄላሲያመርት በወይናደጋው ክፍልደግሞጤፍ፣ገብስ፣ማሽላ ፣የቅባትእህሎችይመረታሉ፡፡ከእነዚህበተጨማሪብሔረሰቡእንስሳትየማርባትናንብየማነብ ስራ በመስራት ይተዳደራል፡፡ ብሄረሰቡ በእንሰት ተክልም የታወቀ ነው፡፡ እንሰት ለየም ብሄረሰብ ሁለንተናዊ የኑሮ መሰረቱ ሲሆን የብሔረሰቡባህላዊምግቦችከእንሰትየሚዘጋጁ ሲሆን እንሰት ለምግብነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የቤት መገልገያ እቃዎች /ቁሶች/መስሪያነትም ያገለግላል፡፡ከነዚህም ለምሳሌ ሾሮዶ ( ሳጥን)፣ኦፖ (ንጣፍ)፣ኬፓ፣ጋዱ (ገመድ) ወዘተሲሆኑ በስጋጃ መልክ እንደ ሳጥን፣ትራስ፣ጂባ(ምንጣፍ)ገመድ የመሳሰሉትን በመስራት ከማህበራዊ ጠቀሜታቸው ባሻገር የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ያገኛሉ፡፡የየም ብሄረሰብ በሸክላ ሥራዎችም የሚታወቅ ነው፡፡በተጨማሪም በልዩ ወረዳዋ የተለያዩ የከበሩ ማእድናት የሚገኙባት ሲሆን እነሱምሴራሚክ፣የብረትማዕድን፣የከሰል ድንጋይ፣የእጣን ዛፎች፣እንዳሉ ይነገራል፡፡የየም ልዩ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት (2003 ዓ.ም) ‹‹ የመሬት አጠቃቀምመረጃ››

የየም ብሄረሰብ በመድሃኒት ቅመማም ይታወቃል፡፡መድሃኒቶቹም ለካንሰር፣ለወፍ በሽታ/ለጉበት በሽታ/፣ለጋንግሪን፣ለወባ በሽታ፣ ለእብድ ውሻ በሽታ፣ለአሜባ በሽታ ወዘተ የሚያገለግሉና ባህላዊ መድሃኒቶች በተለይ በአመት አንድ ጊዜ በጥቅምት 17ቀን የቅዱስ እስጢፋኖስ እለት ሁሉም ሰው በጋራ ወጥቶ የሚለቅመው መድሃኒት(ሳሞኤታ) ለሰውናለእንስሳት የሚሆን ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡በተጨማሪም የተለያዩ ስብራቶችን የሚጠግኑ ወጌሻዎችም የሚገኙበት ማህበረሰብ ነው፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ለየም ብሄረሰብ የኢኮኖሚ መሰረቶች ናቸው፡፡ (የየም ህግሥርዓት፣2005 ዓ.ም)

### 2.2.4የየምብሔረሰብሃይማኖት

በየም ብሔረሰብ ውስጥ የተለያዩ አምልኮዎች(እምነቶች)ይመለካሉ፡፡ የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ ፕሮቴስታንት፣የእስልምናናባህላዊ እምነቶች ተከታዮች ይኖራሉ፡፡ ስለ ክርስትና ወደ የም አመጣጥን በተመለከተዮሀንስ ወልደማሪያም (1936 ዓ.ም ገጽ 127-128) እና አለቃ ታዬ (1914 ዓ.ም ገጽ 37-40) የኢናሪያ እዝብ በአጼ አግብዓ ጺዮን ዘመን በ1270 ዓ.ም. በአቡነ ተክለኃማኖት ስብከት አምኖ ተቀብሎ ክርስቲያን ሆኖ እንደነበርና በኃላ ግን በክርስትና እምነት ላይ በተፈጸመው የወረራ ጥቃት ሞትና ውድመት እንደደረሰበት ገልጸዋል፡፡ ከሞት የተረፈውም የሚያስተ ምረው ሲያጣ እንደገና ተመልሶ አረማዊ በመሆን የክርስትና ሃይማኖትን አጥፍቶ በዘንዶና በዛር ማምለክ ውስጥ እንደገባ ነው፡፡ ክርስትና ከጠፋ ወዲህ የኢናሪያ ህዝብ በዘንዶና በዛር ወደማምለክ እንደገባ የሚያስረዳ ከዚያ ወዲህ የሚነግስ የጃንጀሮ ንጉስ ለዘንዶ ይገብራል ንጉሱም ባለብዙ ሚስት ነው በማለት ብሄረሰቡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ይከተል የነበረውን እምነት አመላክተዋል፡፡ከዚህ በኃላ ደግሞ የብሄረሰቡ ታሪክ አዋቂ መረጃ አቀባዮች እንደሚናገሩት ከጎንደር የመጣው የሞዋ ጎሳ ከእስራኤል ሆኖ ወደ ጎንደር ከገባ በኋላ በጎንደር የራሡን መንግስት መስርቶ ከቆየ በኋላ በጎንደር ውስጥ የመታሰቢያ ዛፍ በመትከል ወደ የም ምድር አንደመጣና ሌሎች ጎሳዎችም አብረውት እንደመጡ የሚነገር ሲሆን እነሱም «ዋዛም፣ ፋጋቴስቶ፣ጎሌማሽና ሞዋ ናቸው፡፡ ከሞዋ ጎሳ የመጡት የመጀመሪያው የሞዋ ንጉስ የነበሩት ባላም(ባለወልድ) እንደሆኑና እኚህ ሰው ከሶስት ወንድሞቻቸው ጋር 44 ታቦታትንና ክርስትናን ወደየም ምድር ያመጡና ያስፋፉ እንደነበርና የአንገሪን ቤተ-መንግስትንም የመሰረተው የሞዋ ስርወ መንግስት ነው፡፡ ስርወ መንግስቱን የመሰረቱት ንጉስ ባላም (ባለወልድ) የተባሉ ክርስትናንም ጭምር ይዘው መጥተው በ12ኛ መ/ከ/ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ህዝቡን ይመሩ እንደነበር የታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን የግራኝ አህመድ ሰራዊት አካባቢውን በወረረበትወቅትብዙ ቤተ-ክርስቲያናትንበማቃጠልክርስቲያኖቹንም በመጨፍጨፍ የእምነቱን ተከታዮችና እምነቱን እንዲጠፋ አድርጎ ነበር ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የብሄረሰቡ አባላት በአዞ፣ በወንዝ፣ በተራራ ወዘተ. ሲያመልኩ ቢቆዩም በአጼ ምኒልክ ዘመን የፊታውራሪ ገብረመድህን ጦር ወደ አካባቢው ሲመጣ በ1888 ዓ.ምታቦታትን ይዞ እንደመጣና የክርስትናን ሀይማኖት እንደገና እንዳስፋፉ

ይነገራል በማለት ለማ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም በ1890 ዓ.ም የተተከለው የፎፋ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ለአብነት ይጠቀሳል በማለት፡፡ ከክርስትና እምነት ጎን ብሄረሰቡ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በአዞና በቃልቻ ማመን የተለመደ እንደነበር ለማ በጥናት መረጃቸው አመልክተዋል፡፡ በ1999ዓ.ም በብሄራዊ መረጃና ስታስቲክስ ኤጀንሲ የተካሄደው ህዝብና ቤት ቆጣራ መረጃ እንደሚያመለክተው ከልዩ ወረዳው ህዝብ 80 በመቶው የኦርቶዶክስ፣ 5 በመቶው የፕሮቴስታንት ክርስትና እና 15 በመቶ የሚሆኑት የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደሆኑ «ለማ (1999 ዓ.ም ገጽ 22) ገልጸዋል፡፡

## 2.3ማህበራዊተቋማት

### 2.3.1ባህላዊዳኝነት

በየም ልዩ ወረዳም የባህላዊ ዳኝነትስርዓት ያለ ሲሆን ዓላማውም በአካባቢ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮች እንዲቀረፉና ሰላም እንዲሰፍን ሲሆን በየም ልዩ ወረዳ ውሰጥ ለዘመናት ቀጥሎ ያለው «የቻሎ» ባህላዊ ዳኝነት ስርዓት ነው፡፡ የዚህ ባህላዊ ዳኝነት መተዳደሪያ ደንብ አጀማመርሩ በአካባቢው ላይ በጥንት ጊዜ የጎርፍ፣የበረዶ፣የሕመም አደጋ ተደጋግሞ በመከሰት አስቸግሮ ስለነበረ ሕዝቡወደዚያ ቦታ ወጥቶ ሽሾካም/ለአማልክት የተሰጠ መጠሪያ ነው/በማለት ፀሎት በማደረጉ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተጠቀሱት ችግሮች በድጋሚ ባለመከሰታቸው ቦታውን «ቻሎቱና» ብሎ በመሰየም ስርዓቱ እንዲቀጥል ተደርጎ በዓመት ሁለት ጊዜ ማለትም ከሄቦ በዓል (መስቀል በዓል) ጋር ተያይዞ ከመስከረም 17-23 እና ሚያዚያ 27እና 28 የዳኝነት ስርዓቱ ይፈፀማል፡፡ባህላዊ ዳኝነቱ በሶስት ዳኞች የሚፈጸም ሲሆንየዳኝነቱየበላይጌታ "ጎርኖ" በመባልይታወቃሉ፡፡ስለዚህዳኞቹየፍርድስርዓቱንበሚያካሂዱበትጊዜየእነሱየበላይእንዳ ለናፍርድካዛቡየበላያቸውእንደሚቆጣናእንደሚቀስፋቸውበማመንያለምንምአድሎፍር ድይሰጣሉ፡፡ስለዳኝነትሂደቱንስንመለከትበደልየደረሰበት ግለሰብ ክሱን ያቀርብናበደል ያደረሰውግለሰበስብሰባውቦታካለየተጠቀሰውንወንጀልመፈፀምአለመፈፀሙንተጠይቆይ ጣራል፡፡በቦታውከሌለመልዕክተኛተልኮበቀጠሮእንዲቀርብይደረጋል፡፡ወንጀልፈፅሚል ተብሎየተገመተግለሰብተጠይቆወንጀሉንመፈፀሙንካመነላጠፋውጥፋትካሣእንዲከፍል

ውሳኔይተላለፋል፡፡በተቃራኒው የተጠየኩት ጉዳይ አይመለከተኝም ካለ ዳኞቹ ጉዳዩን ለ«ጎርኖ»አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡

በስተመጨረሻም በመስከረም 23 ዕለት የእርግማን ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፤ ወንጀል ሠርቶ ወንጀል ስለመስራቱ ተጠይቆ የካደ በአካባቢው አማልክት ስም ይረገማል፡፡እርግማኑም መሬት ጠብ ሣይል የተፈለገውን ውጤት ያስገኛል፤ያዋርደዋል፤ይገድላል ወይም እርግማኑ ለዘር ማንዘሩ ይተርፋል ተብሎ ይታመናል፡፡የቻሎባህላዊዳኝነትበማህበረሰቡ ውስጥየሚከሰቱወንጀሎችንእንደክህደት፣የደፈጣድብደባ፣ስርቆት፣ቤትማቃጠል፣ግዲያና ተጨባጭመረጃየሌላቸውንወንጀሎችጭምርበማጋለጥናወንጀሎችእንዳይከሰቱበማድረግ ሰላምንበማስፈንችግሮችከተከሰቱምብዙየገንዘብ፣የጊዜናየጉልበትብክነትሳይኖርፍትሃዊየ ሆነፍርድበማስገኘትየሚጫወተውሚናበቀላልዋጋየሚተመንአይደለም፡፡የቻሎ ባህላዊ ዳኝነት ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀመው በአመት ሁለት ጊዜ ሲሆን አንደኛው ከመስቀል ዳመራ ጋር ተያይዞ መስከረም 17 ጀምሮ ለተከታታይ ለ7 ቀናት ነውና። ሁለተኛው ሚያዚያ 27-28 የባህላዊ ዳኝነት ሥርዓቱ ይፈፀማል፡፡ ምንጭ (አያልነሽ ወንድሙ2006 ዓ.ም) ‹‹በየም ብሄረሰብ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ይዘት ትንተና»፣



ፎቶ ግራፍ አስር የቻሎ ባህላዊ ዳኘነት ሲካሄድ

## 2.3.2የባህላዊ የጋብቻ ሥርዓቶች

በየም ብሔረሰብ ባህል አምስት አይነት የጋብቻ ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነርሱም፦የቤተሰብስምምነት (ዛታጊሩ) ጋብቻ፣2ኛ.ድንገተኛ ጋብቻ (ራራግሩ)፣3. ጠለፋ (ቦኣጊሩ4ኛ.በደላላ/በአገናኝ (ዞክኛ) አማካይነት የሚደረግ ጋብቻ እና 5ኛ.የፍቅር/ወዶ ገብ/ (ሹኖ ግሩ)ጋብቻ ናቸው።

1 የቤተሰብ ስምምነት (ዛታ ጊሩ) ጋብቻበየም ብሄረሰብ የቀድሞ አባቶች ሚስት የሚያገቡት ወጣቱና ልጃገረዷቱ ሳይተዋወቁ ሁለቱ ወላጆች በመስማማት ከሁለት የማይበልጡ ሽማግሌዎች ከልጁ አባት ጋር ወደ ልጅቷ አባት በመላክና በመስማማት የሚደረግ የጋብቻ አይነት ነው፡፡

2. ድንገተኛ ጋብቻ (ራራ ጊሩ) የልጅቷ ቤተሰቦችና እሷ ሳይሰሙአግቢው በድንገት ደግሶ ፈረሱን ጭኖ ሰርገኛ አስከትሎ ወደ ሚፈልጋት ኮረዳ ቤተሰብ ቤት በመሄድና ለጋብቻ በመጠየቅ የሚደረግ የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡

3.የጠለፋ ጋብቻ (ቦኣ ጊሩ)ይህ የጋብቻ ዓይነት ልጅቷ ለሆነ ጉዳይ ብቻዋን ስትጓዝ አግቢው ወጣት ጓደኞቹን በማስተባበር በጉበት ልጅቷን በመጥለፍ ያለፍላጎቷ የሚደረግ የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡

4.የደላልነት ጋብቻ (ዞክኛ) ይህየጋብቻሥርዓት በብሔረሰቡ ዘንድ በጣም የቆየና አደገኘነት ያለው የጋብቻ ሥርዓት ነው። ብዙውን ጊዜ የሚፈፀመው ባላቸው በሞተባቸው ሴቶች እና አግብተው በፈቱት ላይ ነው፡፡ አንዳንዴም ልጃገረዶችም ይህ ዕዋ ይደርስባቸዋል። በደላላነት /በአገናኝነት /ተግባር የተሰማራችው ሴት ከወንድየው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘትበሚፈልጉ ደላሎች አማካይነት የሚፈጸም የጋብቻ አይነት ነው፡፡

5. የፍቅር ወይምወዶ ገብ (ሹኖግሩ)ጋብቻ፣-ወንዱና ሴቷ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቤተሰብ ፈቃድ ወጪ በፍቅር ተሳስረው የግብረ ስጋ ግንኙነት በድብቅ ሲፈፅሙ

ቆይተው ልጃቷ በሆዷ ፅንስ ሲፈጠር ፍቅረኛዋ ቢወድም ባይወድም በግድ ሄዳ ቤተሰቦቹቤት በግድ ገብታ የምትኖርበት የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ (ምንጭ የየም ልዩ ወ/ባ/ቱ/ስ ጽ/ቤት ሚያዝያ 2011 ዓ.ም)

### 2.3.3. «ሂቦ»(የየም ዘመን መለአወጫ በዓል)

በየም ብሄረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጎ በልዩ ትኩረት ከሚከበሩ በዓላት መካከል የ‹‹ሂቦ›› በዓል ዋነኛው ነው፡፡ የሂቦ በዓል አከባበር መቼ እንደተጀመረ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ እንደ ዘመን መለወጫነት የሚከበር የብሔረሰቡ ባህላዊ በዓል ነው፡፡ በወረዳው የሚገኙ ሁሉም የእምነት ተከታዩች ሂቦን እንደ ዘመን መለወጫ በዓል ያከብሩታል፡፡ በየም ብሄረሰብ ዘንድ የዘመን መለወጫ በዓል ትልቅ ግምት ተሰጥቶት የዓመት ዝግጅት የሚደረግበት፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ በአዲስ የሚተኩበት፣ አዲሱን ዓመት ለመቀበል ቅራኔ ተወግዶ አዲስ አስተሳሰብ የሚያዝበትና በአዲስ መንፈስ ወደ ሥራ የሚገባበት ትልቁ የብሔረሰቡ ክብረ በዓል ነ[2]ው፡፡ በዓሉ የሚከበረው ከመስከረም 14 እስከ 17 ሲሆን የአመት ዝግጅት ተደርጎበት(ቁጠባ ተገብቶ) የሚከበር የየብሄረሰቡ አባላት የሆኑት ከቅርብም ከሩቅም ያሉ ዘመዳሞች ተገናኝተው በደስታ የሚያከብሩት ታላቅ በዓል ነው፡፡

**ከኪነ ጥበብም አንጻርም**የተለያዩ በርካታየሙዚቃመሳሪያዎችይገኛሉ፡፡ እነዚህም በሦስት ይመደባሉ፡- የትንፋሽ ፣ የምት እና የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

የትንፋሽየሙዚቃ መሣሪያዎች የሚባሉት የሚከተሉት ሲሆኑ

1.ፊና ፡- አርኪ ፊና ሀቴ ፊና (ፌርፌኩ) በመባል ይታወቃል፡፡

2.ቱቱሩ ፣ (ቀንደ መለከት) ማርካታ እና

3.ጋውሎ ናቸው፡፡ሙዚቃ ለማጀብ የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያዎችናቸው፡፡



ትልቁ ፊና/አርኪፊና/ ትንሹ ፊና/ሀቱ ፊና/ ቱቱሩ/ቀንደመለከት

ፎቶ ግራፍ አስራ አንድ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች

(ምንጭ፣ [3] የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት፣የቱ/መ/ጥ/ል/ግ/ ዳይሬክቶሬት ሳጃ፡፡ሚያዝያ10/2011 ዓ.ም)

---

[3] «አርኪ ፊና» የሚባለው ከቀርከሃ የሚሰራ የትናፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን« አቴፊና» የሚባለው ደግሞ ከሸንበቆ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡«ቱቱሩ (ማርካታ)» የሚባለው ደግሞ ቀንደ መለከት ነው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## 3.ክለሳ ድርሳናት

### 3.1 ንድፈ-ሐሳባዊ ቅኝት

#### 3.1.1 የተረክንድፈሀሳብ

##### 3.1.1.1 ቃላዊዝርውተረክ (Oral prose narrative)

ተረክ ማለት አንድን ልምድ ወይም ተሞክሮ በቃል ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡ተረክ ሙሉ ለሙሉ የአንድን ማህበረሰብ መረጃ ወይም ልምድ የመለዋወጫ መሳሪያ ነው፡፡(Oring 1986:122) በተረክ ውስጥ ድርጊትና ሁነት የግድ የማይቀሩ ነገሮች ናቸው፡፡የድርጊቱና የሁነቱ ባለቤት ገጸ-ባህሪያት ድርጊቱንና ሁነቱ የሚፈጸምበትን ስፍራና ጊዜ ይዘው አብረው ይመጣሉ.ማለት ነው፡፡ተረክ«ታሪኩን» ትረካውና የሚቀርብበትን መንገድ(ሁኔታ)አጠቃሎ ይይዛል፡፡ ተረክ በቃል አሊያም በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል፤ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ሊተወን፣ሊደነስ፣ሊሳል፣ሊቀረጽ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችል ቅርጽ ነው፡፡(ቴዎድሮስ 2001፣259-260) ተረክ የያዘው ጽንሰ ሐሳብ በጣም ሰፊ ሲሆን ለዚህ ጥናት እንዲመች በማለት ለማጥበብ ተሞክሯል ፡፡ ይህ ማለት ይህ ጥናት በቃል የሚተላለፉትንና በዝርው የሚቀርቡትን ተረኮች ብቻ የሚመለከት ይሆናል፡፡ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከሰው ወደ ሰው በቃል የሚተላለፉ እንደሆኑና የቆይታ ጊዜያቸውምከአንድ ትውልድ በላይ የሚዘልቁ እንደሆኑ (Vansina 1985:101) ያስረዳሉ፡፡ Finnegan(1970፡380) በበኩላቸው በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ባለው ክዋኔና ከትውልድ ትውልድ በሚደረገው ቃላዊ ተስተላልፎ እንደሆነይገልጻሉ፡፡

Degh (1972፡58) በዝርው መልክ የሚቀርቡ ማናቸውም የስነ-ቃል ዓይነቶች ቃላዊ ተረክ ይባላሉ፡፡ሲሉ Bascom(1996:3) ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ

አፈ-ታሪክ፣ ተረትንና ሚትን አካቶ የያዘ የስነ-ቃል ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አንድ ማህበረሰብ ከየት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ እንደ ራሱ የዕውቀት አረዳድ ደረጃ መግለጹ አይቀርም፡፡አለምን የሚመለከትበት፣የሚረዳበትና የሚያስረዳበት የራሱ መንገድም ይኖረዋል፡፡ሰዎች ህይወታቸውን በተቃና መንገድ መምራት እንዲችሉ ቃላዊ ዝርው ተረኮች መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ሚትና (Myth) አፈ-ታሪኮች (Legend) ‹‹እውነት›› ናቸው የሚባሉት መረጃዎችን ስለሚይዙ ነው፡፡በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥርጣሬዎችንና ቅሬታዎችን ያሶግዳሉ፡፡ ስለዓለም፣ስለሰዎች፣ስለእንስሳት፣ስለዕጽዋት አፈጣጠር ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በቋንቋ የሚገለጹ፣በቃል የሚተላለፉ፣በጊዜ ቅደም ተከተል የተዋቀሩ ታሪክ ያላቸው፣በታሪኩ ውስጥ ያለውን ድርጊት የሚፈጽሙ ገጸ-ባህሪያት ያሏቸው የድርጊቶችና ሁነቶች ትረካ ናቸው፡፡በቃላዊ ዝርው ተረክ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ጥናት ካደረጉ ምሁራን መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት Jacob Grim እና ወንድሙ Wilhel Grim መሆናቸውን ኦክፔውሁ ጠቅሷል፡፡Okpewhu(1992፡5-7)እንደ ወንድማማቾቹ አገላለጽ ዝርው ተረኮች የጥንታዊያን ህንድ ፣ጀርመን ሚቶች ቅሪቶች ናቸው፡፡ስለ አማልክትና ጀግኖች የሚተረኩ ተረኮች ከእነዚህ ቅሪቶች በመነሳት እንደገና የተፈጠሩ ሲሆን የአስማት ተረቶችም ቢሆን በእነዚሁ ኢንዶ ጀርመኖች ተፈጥረው በስደትና በሌሎች የባህል ግንኙነቶች አማካይነት ወደ ተየያዩ ማህበረሰቦች የተሰራጩ ናቸው፡፡Dorson (1972:1 ) ከእነሱ በኋላ በአርያን ሚቶች ላይ ጥናቱን ያደረገው ደግሞ ተረኮች በኢርያኖች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የተፈጠሩ መሆናቸውን ሲገልጽ Langም የአርያኖችንና ክላሲካል ሚቶችን ከአውሮጳውያን ተረቶች‹‹ሞቲፍ››ጋር በማነጻጸር ተረኮቹ በቅድመ ታሪክ ወቅት ከነበሩ የሰው ልጆች ልማዶች እና እምነቶች የመነጩ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡Degh (1969:55)

Oring (1986:122) እንደሚገልጹትም ቃላዊ ተረኮች ቋንቋ ከተፈጠረ ጀምሮ የነበሩና እስከ አሁንም የሚገኙ እንዲሁም ሁሉም ማህበረሰብ በየትኛውም የስልጣኔ እርከን ውስጥ ቢሆን የሚጠቀምባቸው እንደሆነ ነው፡፡የጥንታዊ ኋላቀር እና አርሶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ የሚገኝ የስነ-ቃል ዘርፍም አይደለም፡፡ስለዚህ ቃላዊ ተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ የስነ-ቃል ዘርፍ ነው፡፡ይህን ሃሳብ በተመለከተ ፈቃደ (1999፣52) ተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለና በዕለታዊ ህይወት ውስጥ በተለያየ ሁኔታ የሚከወን ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡በተመሳሳይDegh (1972:54 ) ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሰው ልጅ ስልጣኔ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ የሚያረጅና ራሱን ከዘመኑ ሁኔታ ጋር በመቀያየር የሚኖር የስነ -ቃል ዘርፍ እንደሆነ ያብራራል፡፡

Oring (1986:121) ስለ ቃላዊ ተረክ ሲያስረዱ ተረክ የሰው ልጅ ያካበታቸውን ልምዶችቃላዊ በሆነ መልኩ የሚገልጽበት አንድ መንገድ ነው ይላሉ፡፡በዚህም ከተረክ ምንነት ጋር በተያያዘ Liws እና Sandara (2001:16) ሲያስረዱ Narrative is adiscourse with aclear sequential order that place events in ameaningful way for definite audience and thus gives in sight about the world and peoples experience of it. ከዚህ እንደምንረዳው ተረክ ለሁነቶች ትርጉም በሚሰጥ መልኩና ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ የምናቀርብበት ዲስኮርስ (ትረካ) ነው፡፡የራሱ ታዳሚዎች አሉት፡፡ተረክ ስለ ዓለምና ስለ ተረኩ ባለቤቶች ይገልጻል፡፡

Iranmanesh (2012:126-127) ደግሞ ተረክን ተረክ ካልሆኑ ድርሳናት እንዴት እንደሚለይ ሲገልጹ ተረክ ክስተቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ተቀናጅተው መተረካቸው እና የሚያስደንቁ እንዲሁም ያልተጠበቁ ክስተቶችን የያዙ ተረኮች ያሏቸው መሆናቸው ተረክ ካልሆኑ ሌሎች ድርሳናት ይለዩዋቸዋል ፡፡እነዚህ ያልተጠበቁ ታሪኮችና ክስተቶች ታሪኩ ከምን እንደሆነ፣ታሪኩ የት ቦታ እንደተፈጸመ፣የታሪኩ ዋና ሃሳብ ምን እንደሆነ ፣የታሪኩ ፍጻሜ ምን እንደሚመስል፣ እንዲሁም የተራኪውን የግል አስተያየትና ማብራሪያ ሁሉ ይይዛሉ፡፡

ስለ ቃላዊ ተረክ ምንነት Degh(1972:58) ጠቅለል አድርገው ሲገልጹ በዝርው መልክ የሚቀርብ ማንኛውም የስነ-ቃል ዓይነት ቃላዊ ዝርው ተረክ እንለዋለን ብለዋል፡፡

ተረክ(Narrative) ይህ ቃል በኢትዮጵያ የመስኩ አጥኚ ከሆኑት መካከል ፈቃደ (1991፡52) ተረት በሚል ሲተረጉሙት ዮናስ(1992፡84)ተረክ ብለውል፣ሰለሞን (2007፡83) ደግሞ ቃለ ተረክ ሲለው ይስተዋላል፡፡"አሥረኛንኩዋ?ሃዲስ አለማየሁ እና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው" በሚለው መጣጥፍ ውስጥ Narative የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ተረክ በሚል የተረጎሙትን ትርጉም ይገኛ እቀጥላለሁ፤ ከዚህም በመቀጠል የተለያዩ ምሁራን ስለ ተረክ የሰጧቸው ብያኔዎች በዝርዝር እናያለን፡፡

ፈቃደ (1991፣53) ሰዎች ተረትን እንዴት ይገለገሉባቸው እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም በጥንት ዘመን ሰዎች ተረት በመተረት ጊዜ ያሳልፉ፣ ይዝናኑ፣ ይደሰቱ፣ ይማሩ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በተመስጦ ያነቧቸዋል፤ ያዳምጧቸዋል፤ ስለ አማልክትም፤ ስለ ቅዱሳንም፤ ስለ ነቢያትም...ወዘተ እንዲሁ በተመስጦ ያነባሉ፤ ያዳምጣሉ፡፡ከነዚህ ክንዋኔዎች ደስታን፣ ትምህርትን፣ ምግባርን ወዘተ ይቀስማሉ፡፡በተመሳሳይ መልክ Deign (1972:54): Oral narratives በማንኛውም ማኅበረሰብ እንደሚቀርቡ ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማኅበራዊ ሁኔታ (Social condition or climate) ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡

በሌላም በኩል የአንድን ማኅበረሰብ ተረክ ለማጥናት ሲፈለግ ትኩረት መደረግ ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ Deign (1972፣54) ይገልጻሉ፡፡ እነርሱም በተረኮቹ አማካይነት የሚተላለፉት መልእክቶች ምንድን ናቸው? ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆኑት ምን እንደሆኑና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ተረድተው መልስ መስጠት እንደሚገባ ነው የገለጹት፡፡

ከእነዚህ ሃሳቦች በመነሣት ተረክ የአንድ ማኅበረሰብ መገለጫ የሆነ፣ በዝርው የሚቀርብ፣ የድርጊት ተሳታፊዎች ገጸ-ባህርያት ያሉት፣ድርጊቱ

የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት፣ረጅም ዘመን ያለው፣ለሰው ስሜት ቅርብ የሆነ፣ከነባራዊ ዓለም ጋራ በሚስማማ መልኩ የሚቀርብ የሥነ-ቃል አካል ነው ማለት ያስችላል፡፡Oring(1986፣135-142) በበኩላቸው ተረኮች በድርጊቶችና በሁነቶች የተዋቀሩ የአንድ ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ልማድ ለማስተላለፍ የሚጠቅሙ መሣሪያዎች ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ተረክለማኅበረሰብ ተከታታይ ድርጊት አመልካችነቱና ቃላዊነቱ እንዳለ ሆኖ በተለያየ ቅርጽ የሚቀርብበት ነው ማለት ያስችላል፡፡

### 3.1.1.2 የተረክዓይነቶች

በተረክ ዓይነቶች ዙሪያ በርከት ያሉ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሲያስቀምጡ ይስተዋላል፡፡ ከነዚህም መካከል Bascom(1965፣4) እና Okpewhu ይጠቀሣሉ፡፡ ፊቃደ Okpewhu በመጥቀስ የተረት ዓይነቶችን ሌጀንድ፣ ገላጭ ተረቶች እና ፌብልስ በማለት እንደሚከፈሉ ያስረዳሉ፡፡ እንደ Bascom (1965፣4) ገለጻ የተረክ ዓይነቶች ተብለው የሚታወቁት ሚት፣ አፈ ታሪክ እና ተረት ናቸው፡፡Bascom ለተረቶች ምደባ መሠረት ያደረጋቸውን ነገሮች ሲገልጹ አካባቢያዊ እንድምታ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በቀጣይም እነዚህን ሦስት ነጥቦች ከተለያየ ምልከታ አንጻር እንቃኛለን፡፡

#### 3.1.1.2.1ሚት

"የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት እየተመሰቃቀለ በሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርአት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ሚት የማህበረሰቡን የዕሴት ሥርዓትም ነው፡፡ "ቴዎዶሮስ፣XII፡፡ Finnagane (1992፣138) ሚት በማህበረሰቡ ዘንድ ከረጅም ዓመታት በፊት የተከሰቱና እውነት ናቸው፣ ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶች የሚነገሩበት የቃል ትረካ ዓይነት እንደሆነ ትገልጻለች፡፡

ሚት ማኅበረሰቡ በአካባቢው የሚያስተውላቸው ተፈጥሯዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህርይ፣ አፈጣጠራዊ ሂደት፣ከየት-መጣነት መልስ ለማግኘት የሚጥርበት

ነው፡፡ የአካባቢውን የባህል ዕሴት፣ መሠረት በማድረግ ለራሱ የአስተሳሰብ አድማስ ለዓለም ያለውንግንዛቤ የሚገልጽበት የተረት ዓይነት ነው፡፡

ስለ ሚት ምንነት ከማጠቃለላችን በፊት የሚት ዓይነቶች ተብለው በተለያዩ ምሁራን ተመድበው ከምናገኛቸው መካከል ጥቂቱን ቀጥለን እናያለን፡፡ ዘፍጥረታዊ ሚት (creation myth) ፣መንፈሳዊ ሚት (Deity myth)፣የባህል ታጋይ ሚት (myth of culture heroes and esoteriological)፣ ጊዜያዊና የዘላለማዊ ሚት (Myth of time and eternity)፣የዘመናዊ ማኅበረሰብ ሚት (Myth of modern society), ጂኦሚቲዮልጂ(geomethology) ወዘተ ይጠቀሣሉ፡፡ ሰለሞን (2007፣101)፡፡

### 3.1.1.2.2 አፈ-ታሪክ

ባለፈ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታ በመውሰድ ሥነ-ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ እንደዘሪሁን አገላለጽ የአፈ ታሪክ ዓላማ አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ በታሪክ የተፈጸመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ለምን ተፈጸመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሡ በአፈ ታሪክ መልስ ይሰጣሉ፡፡

አፈ-ታሪክ በማኅበረሰብ ውስጥ የተከሠተ እውነተኛ ታሪክ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ተስተላልፎው በአንድ ትውልድ ያልተገታ ነው፡፡ አፈ ታሪክ ቃላዊ በሆነው ተስተላልፎው አድማጩን በማስተማር፣ በማንቃት፣ወይም ለአድማጩ መረጃ በመስጠት፣ ታሪክ በማሳወቅ ወዘተ... ረገድ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

እንደ Bascom (1965፣6) ገለጻ አፈ ታሪክ በእውነት ላይ የሚመሠረት፣ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚመረመሩበት፣ ገጸ ባህርያቱ ሰዎች የሆኑ፣ በእራሳቸው የሚቆሙ ሳይሆኑ እራሳቸውን አሳልፈው ሰዎችን ነጻ የማውጣት ባህርይን የተላበሱ፣ ገጸ ባሕርያቱ የሚተውኑበትን መንፈሳዊ፣ሥጋዊ ጉዳይም የሚያነሣ፣ በዚህኛው ዓለም የተፈጸመ የቅርብ ኀላፊ ጊዜ ያለው፣ መቼቱ

አንዳንዴ የሚታወቅ፣ እውነትነት ያለው፣ ስለ ሰዎች፣ ስለ ቦታዎች፣ ስለ ታሪኮች እና የተለያዩክስተቶችን የሚተርክ ማለት ነው፡፡

### 3.1.1.2.3. ተረት

ተረቶች በሳይንሳዊ መንገድ ሊረጋገጡ የማይችሉና በሰዎች አእምሮ ውስጥ ተአማኒነት የሌላቸውፈጠራዊ ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ፍሰታቸውን ጠብቀው የሚቀርቡበት የተረክ ዓይነት ነው፡፡ ተረት በሴራ ያልተወሳሰቡ ልማድና ቀጥተኛ የሆኑ ታሪኮችን፣ ዓለም ዓቀፋዊ ባህርይ ያላቸውን ታሪኮች የሚገልጽና በውስጡም የሚገኙትን ገጸ ባህርያት፣ አጋጣሚዎች፣ ዋና ዋና ፍሬ ሃሳቦችና የድርጊቱ ገጽታዎች እንደ ዋና መሠረታዊ ጭብጥ የሚወስድ ነው፡፡

ተረት የመተረት ጥበብ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ የፈጠራ ውጤት እንደሆነ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራንይገልጻሉ፡፡(Thompson፡1946 እና Fischer፡1963) ይህንሐሳብበተረት ላይ ጥናት በማድርግ ቀዳሚ የሆነውን(Thompson፡1946፣3)"When we confine our view to our own world, we see that for least three or four thousand years, and doubtless for ages before› the art of the storyteller has been cultivated in every society "በማለት ገልጾታል፡፡ተረት የሰው ልጅ የሚኖርበትን ዓለም፣የራሱን ማንነትና አሉኝ የሚላቸውን ማህበራዊ ዕሴቶች ለመረዳትና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማለት የሚፈጥረው ከትውልድወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የስነ ቃል ዘውግ ነው፡፡

እንደ Thompson (1946፡ 4) እና Leach (1949፡ 404) ተረቶች አለም አቀፋዊ ባህሪ የስነ-ቃል ዘውጎች ናቸው፡፡የአተራረክ ስልቱና የሚተረክበት አጋጣሚ እንደየ ባህሉ የሚለያይ ቢሆንም ተረት የሌለው ማህበረሰብ የለም፡፡ተረት ከስነ-ቃል ቅርጾች መካከል የሚመደብ በዝርው ከሚቀርቡት መካከል የሚመደብ ሲሆን በውስጡም ለተዝናኖት ከሚቀርቡት ድራማዊ ባህርይ ካላቸው እስከ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች የሚያስተናግዱበት ሚቶሎጂያዊ ጉዳይ የሚያጠቃልል ነው፡፡ (Fischer, 1963፣263) ተረት

በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊተረት ይችላል፡፡ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር ፣ለማዝናናት፣የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ ሐዘንተኞችን ለመጽናናት ወዘተ እንደዓውዱ አመቺነት ይተረካል፡፡

ተረትን ከየአቅጣጫው በመሰብሰብ የማሳተምና ትንተና የማድረግ ስራ ይበልጥ ትኩረት ያገኘው በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ (Thompson 1946፣ Fischer 1963) የፎክሎር፣የስነ ልቦና ፣የስነነ-ልሳን እንዲሁም የፖለቲካ ምሁራን በተለያዩ የዓለማችን ስፍራዎች የሚተረቱ ተረቶችን በመሰብሰብ ፋይዳቸውን፣ቅርጻቸውን፣ተስተላልፏቸውን ወዘተ በተመለከተ ጥናት አድርገዋል፡፡

በተረቶች ውስጥ የአንድ ማህበረሰብ ታሪክ፣አኗኗር ፣የዓለም አመለካከት፣የህይወት ፍልስፍና ወዘተ ይንጸባረቃል፡፡በዚህም ተረቶችን በመሰብሰብ ንድፈ ሐሳቡን ቃኝቶ፣ምደባና የይዘት ትንተና ማድረግ ይቻላል፡፡ይህንንም እንደመነሻነት በመያዝ ይህ ጥናት «የየም ብሄረሰብንባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ የሚገልጹ ተረኮች ይዘት ትንተና» ላይ ትኩረት አድርጎ የሚጠና ጥናት ነው፡፡

ከዚሁ ጋራ በተያያዘ Bascom (1965፣6) ተረቶች ብዙውን ጊዜ የራሳቸው የአቀራረብ ሥርዓቶች እንዳላቸውና በሚተገበሩበት ጊዜም በተረቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መመሪያዎችን በማምጣት አድማጩም ተረቶቹ ተጀምረው እስኪጨረሱ ድረስ ሥርዓት ባለው መልኩ እንደሚከታተሉ ያስረዳሉ እንደ ባስኮም አገላለጽ የተረቶች በአንድ ምድብ መመደብ ይዘትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

በተረቶች ላይ አጀማመርና አጨራረስ መኖርን ካነሣን ፈቃደ (1991፣63-65) የተረቶች ዋና ዋና ውጫዊ ቅርጾች ብሎ ያነሣቸውን ነጥቦች ቀጥሎ እንመልከት፡፡

የተረት መግቢያ፣ የተረት አጀማመር፣ የተረት አጨራረስ፣ የተረት መዝጊያ እና የተረት ክዋኔ (ትረታ) ይጠቀሣሉ፡፡ ዓይነቶቹን በዝርዝር ማየቱ ከእኔ ጥናት ጋራ የሚያቆራኘው ነገር ስለሌለአልፈዋለሁ፡፡ ተረቶች በሚተረቱበት

ወቅት ታሪኩ ውስጥ የሚቀርቡ ድርጊቶች የተከሠቱበትን ጊዜና ቦታ በግለጽ የማያሳዩ በሞራል የምንፈጥራቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ተረቶች እንደ እውነተኛ ታሪክ ከመውሰድ ይልቅ በሚፈጥሩትደስታ የምንዝናናባቸው ናቸው፡፡ በማለት Marvate (1973፡95) እና Benemos (1992፡102) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የዘረዘርናቸውን ሦስት ነጥቦች ስንመለከት ተረቶች ተቀራራቢ ባህርይ እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡ ይህም የሆነበትን ምክንያት Finnegan (1970፣363) ስትገልጽ በአንድ ማኅበረሰብ አፈ ታሪክ ወይም ተረት ናቸው ተብለው የሚነገሩት በሌላ ማኅበረሰብ ሚት ወይም ተረት ተብለው መነገራቸው ነው፡፡

### 3.1.1.2የኦክፔውሁየተረክአከፋፈል

የዚህ ጥናት የተረክ  አሰባሰብም የዚህን የኦክፔውሁን የተረክ አከፋፈል መሰረት አድርጎ የተከናወነ ነው፡፡

#### 3.1.1.2.1አፈ-ታሪክ

ይህንን ቃል፣ ታዋቂ ግለሰቦችን እና ታዋቂ ድርጊቶችን፣ ሁኔታዎችን በማመልከት ተደጋግመውለሚተረኩ ተረቶች ብቻ መጠሪያነት Okpewhu መርጠውታል Okpewhu ሌጀንድን ታሪካዊ አፈ ታሪክ እና ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ ታሪክ በማለት በሁለትይከፍሏቸዋል፡፡ በተጨማሪም ታሪካዊ አፈ ታሪክ እና ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ ታሪክ በማለት Okpewhu (1941-2016)ን ጠቅሶ ፈቃደ፣ (1991፣56)ገልጸዋል፡፡

ታሪካዊ አፈ ታሪክ በዚህ ክፍል ውስጥ ማኅበረሰቡ በቀላሉ ሊያስታውሳቸው የሚችላቸውን ድርጊቶችና ግለሰቦችን አስመልክቶ የሚተርታቸውን ይመድባሉ፡፡ ትኩረቱ ህይወት ቀመስ ዝርዝሮችን እውነታዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው፡፡ ጊዜው፣ ተራቹና አድማጮች የሚኖሩበት የአሁን ጊዜ ወይም በቅርብ ያለፈ ጊዜ ስለሆነ፤አድማጮችም ሊተቹት ስለሚችሉ፤ ተራቹ የምናቡን ልጓም እንዳሻው ሊለቅ አይችልም፡፡ሮማንቲክ ወይም ሚቲካል አፈ ታሪክ ይኼኛው ለተራቹ ምናብ ሰፊ ነጻነት ይሰጣል፡፡ ድርጊቶቹም ሆኑ

ግለሰቦቹ የጥንት የሚባሉ ስለሆኑ ተራቹን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ የሚደቅንበትም ሰው ብዙ ጊዜ አይገኝም፤ ቢገኝም ተራቹ የማምለጫ ቃላትን በመጠቀም ያመልጣል፡፡ ሌላው የዚህ የተረት ዓይነት ተራቹ ተረቱን ለእራሱ እንዲስማማ አድርጎ የሚተርትባቸው አጋጣሚዎች የሰፉ ናቸው በማለት Okpewhu ን ጠቅሶ ፈቃደ (1991፣57) ያስረዳል፡፡

ከእነዚህ ሁለት ሃሳቦች የምንረዳው ምንም እንኳን የአፈታሪክ ተናጋሪዎች የሚናገሩባቸው መንገዶች ቢለያዩም መነሻቸው ግን እውነታን የያዘ ታሪክ መሆኑን ነው፡፡

3.1.1.2.2ገላጭተረቶች

Okpewhu በዚህ ክፍል የመደቧቸውን ተረቶች ሌሎች ምሁራን Origin story, Natursage, Pourquoistory,etiological tales በመሳሰሉ መጠሪያዎች እነ Thompson (1965)፣Arewa (1980) እና Finnegan (1970) ሲጠሯቸው ይገኛሉ፡፡ ገላጭ ተረቶች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚታዩትን ተፈጥሯዊ እና ህይወታዊ ክሥተቶችና ሃሳቦች ከየት-መጣነት(ኦሪጅን) ለመግለጽናለማብራራት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ እነዚህንም በአራት ንኡሳን ክፍሎች መድቦ መመርመር እንደሚቻልፈቃደ ኦክፔውሁን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡ ገላጭ ተረቶች የዓለምን አፈጣጠርና ከዚያ ጋራ የተያያዘውን የሰው ልጅ ገጠመኝ የሚገልጹናቸው፡፡ በአካባቢው የሚገኙትን የልዩ ልዩ ነገሮችና ፍጥረቶች ባህርይ የሚገልጹ ትረካዎችን ያካትታሉ፡፡

የማኅበረሰብን ልዩልዩ ጠባዮች፣ ዕሴቶችና እምነቶች ለመመርመር የሚተረቱትን በውስጡ ይይዛል፡፡ በተጨማሪም የሰዎችን አነጋገር፣ አለባበስ እና የልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች ከየት-መጣነት እና የመጡበትን ምክንያቶች እና ምንጮች ለመግለጽ የሚተረኩትን የሚያካትት ነው በማለት Okpewhu ን ጠቅሶፈቃደ(1991፣56-61) ይገልጻሉ፡፡

### 3.1.1.2.3ፋቡላ (fable)

ከላይ እንደተገለጹት ሁለት የተረት ዓይነቶች ተራች ብዙ ጊዜ የራሱን የግል አስተያየትና መልእክት በተለያየ መንገድ ይጠቁማል ብሎ ያምናል ብዘዎቹ የአፍሪካ ተረቶች ግን ከነዚህ የበለጠ ክፍት ወይም ነጻ ናቸው፡፡ አድማጭ የራሱን አስተያየትና መልእክት እንዲቀርጽ ተራቹና ትረካዎቹ ይፈቅድለታል ማለት ነው፡፡ Okpewhu ምክንያታቸውን ሲገልጹ ብዘዎቹ የአፍሪካ ተረቶች እንደሌጀንድ እውነተኛም ይሁን ለሃሰተኛ ታሪክ ለመዘገብ ሆነ የማኅበራዊ ልምድን ኬትጣነት በመመርመር የታለሙ ስለሆነ ነው በማለት Okpewhu ን ጠቅሶ ፈቃደ(1991፣62) ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የተረት ዓይነቶችን ኦሌሪክ አክሰሌ፡ ላይ፣ ሳጋ እና ተረት በሚል ሲከፍላቸው፡፡Finnegan (1992፣137) ደግሞ ሚት፣ አፈታሪክ፣አድባሬ ተረት፣ የቤት ተረት፣ ተረት፣ ሚሞሬት፣ ግለሰባዊ ትረካ፣ ኤፒክ እንደሆኑይገልጻሉ፡፡

### 3.1.1.3ተረክንየማጥናትጠቀሜታናየአጠናንሥልት

አንድ አጥኚ የተረክ ጥናት ለማድረግ ሲነሣ ሊከተላቸው የሚገቡ ነገሮች እንዳሉ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Oring (1986፣135-142) አንዱ ናቸው፡፡ እንደ ኦሪንግ ገለጻ በተረክ ላይ ጥናት የሚያደርግ አጥኚ ስለ ታሪኮቹ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖረው እና በተረኮቹም ላይ ከዕውቀትየዘለለ ትርጓሜን ለመስጠት እንዲያስችለው እዚህን አራት ዓውዶች መረዳት እንደሚጠበቅበት ይገልጻል፡፡ እነርሱም ባህላዊ ዓውድ፣ ማኅበራዊ ዓውድ፣ ግላዊ ዓውድ እና ኢንተር ቴክስቿልዓውድ ናቸው፡፡

ባህላዊ ዓውድ፡- ይህ የዓውድአይነት በተረኮች ውስጥ ያሉ ሃሳቦችን፣ ትእምርቶችን እና በተረኩ የሚገለገሉትን ቡድኖች ባህርይ የምንለይበት ነው፡፡

ማኅበራዊ ዓውድ፡- ተረኩን ማኅበረሰቡ እንዴት እንደሚገለገሉበት፣ በተረኩና በብሔሂረሰቡ መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል የምናይበት ነው፡፡

ግላዊ ዓውድ፡-ተረኮች ከአንድ ግለሰባዊ ታሪክ ጀምረው እስከ ሰፊው ማኅበረሰብ ጉዳይ ድረስ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ግላዊ ዓውድም የአንድን ግለሰብ ግላዊ ብቃትና የህይወት ልምድ ልናውቅበትና ልንገመግምበት እንችላለን፡፡ ይህንንም ስናደርግ በግለሰቡ በአብዛኛው የሚተረክልን ተረክ የትኛው ነው? ለምንስ ነው ይህን የመረጠው? የተራኪው ማንነትስ ከተረኩ ጋራ ያለው ግንኙነት ምንድነው? የሚሉትን ነገሮች በጥልቀት የሚያሳይ ነው፡፡

ኢንተር ቴክስቿል ዓውድ፡- ይህኛው ዓውድ ከላይ ከጠቀስናቸው ከሦስቱ የዓውድአይነቶች በተወሰነ ደረጃ የሚለይ ነው፡፡ ይኸውም ኢንተር ቴክስቿል ዓውድ የዓለምን የፎክሎር ተረክ የሚያነሣ እና በትረካው ላይ ከሚታዩ ሁነቶች ውጪ በመውጣት ተረኩ ሌላ ተረክን የሚጠራ መሆኑን የምንቃኝበት ነው፡፡ ይህ ሲባልግን በሁሉም የተረክ አይነት ላይ ትንታኔ ለመስጠትና ትርጓሜ ለማምጣት ይረዳል ማለት አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ የተረኮቹን መዋቅርና ተምሳሌት በማየት ከሌላ ተረክ ጋራ ሊዛመድ የሚችል ከሆነ በማዛመድ መጠቀም የሚያስችል ነው፡፡ Oring (1986 135-42) ፡፡ ይህንን ሃሳብ ሲያብራሩ ከኢንተር ቴክስቿል ዓውድአንጻር ትንታኔ ለመስጠት የመጽሀፍ ቅዱስን ታሪኮች ማንሣት አንዱ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

### 3.1.2ባህል

ባህል በጣም ሰፊና ውስብስብ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡በዚህም የተነሳ የተለያዩ የማህበራዊ ሳይንስና የሥነ-ሰብ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች የሰጡ ሲሆን አንድ ወጥ የባህል ትርጉም ማግኘት ግን ያስቸግራል፡፡ሆኖም እ.ኤ.አ በ1982 ዩኔስኮ በሜክሲኮ ባካሄደው ጉባኤ ባህልን በማስመልከት የሰጠውን ብያኔ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡‹‹ ባህል አንድ ህብረተሰብ ወይም የማህበረሰብ ቡድን ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበትመንፈሳዊ፣ቁሳዊ፣ምሁራዊና ስሜታዊ ባህሪያት ከሁለንተናዊ ምሉዕነታቸው ያካትታል፡፡ ባህል ሥነ-ጥበብና ሥነ-ጽሑፍ የአኗኗር

ዘይቤን፣ዕሴቶቸን፣እምነትና ልማዶችን ጭምር የሚይዝ ነው›› ሲል እንደ ሚከተለው ይገልጻል፡፡

Culture is a term that has various meanings. The modern anthropological understanding of culture has its origins in the 19th century with German Anthropologist Adolt Bastian and British anthropologist Edward Burnett Taylor. In 1874, Taylor described culture in the following way:"culture or civilization, taken in its wide ethnographic sense, is that complex whole which includes knowledge, belief, art, morals, law, custom, and any other capabilities and habits acquired by man as a member of society" (Taylor, E.B 1974). S.N.N.P.R Bureau of Culture and Tourism 2017:2/

እንዲሁም ባህል ከአካባቢያዊ ሁነቶች ሰው ሰራሽ ክፍሉ ሲሆን አንድ ሰው በአጠቃላይ በማህበረሰብ አባልነቱ የሚያገኘው ባህሪ፣እውቀትና ክህሎትነው፡፡(የኢንታንጀብልባህላዊ ቅርሶች የኢንቬንተሪ ማኑዋል፡፡2002 ዓ.ም)በመሆኑም ከላይ በተገለጸው መሰረት የትኛውም ማህበረሰብ መንፈሳዊ ፣ቁሳዊና ስሜታዊ ባህሪያት ያጠቃልላል፡፡በእነዚህ ማህበራዊ እሴቶች አማካይነትምታሪኩን፣ማንነቱንይገልጽበታል፤ህልውናውንያስጠብቅበታል፤አመ ለካከቱን፣አንዲሁም የህይወት ፍልስፍናውን ያንጸባርቅበታል፡፡የሰው ልጅ አሁን ካለበት ለመድረስ ረጂም ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡በርካታ የህይወት ውጣውረዶችን አሳልፏል፡፡በዚህ በህይወት ጉዞው ለሚያጋጥሙት ችግሮች በራሱ የዕውቀት ደረጃ መፍትሄ አየሰጠ ከአጋጣሚዎች አየተማረ አንድ የህይወት ስርዓት አበጅቷል፡፡ከዚህ ከአኗኗር ስርዓቱ ጋር የሚሰምር ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቋም ገንብቷል፡፡የአስተዳደር፣የእምነት፣የልማት ወ.ዘ.ተ ስርዓቶችን መስርቷል፡፡በአጭሩ የሰው ልጅ ከዚህ በቴክኖሎጂ ከተራቀቀው ዓለም የደረሰው ከአኗኗር ስርዓቱና ከህይወት ገጠመኙ ባገኘው ዕውቀት ተጠቅሞ ለራሱ በሚስማማው መልክ እየለወጠ ፣እያሻሻለ በመጓዝ

ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቁሳዊውና መንፈሳዊ ህይወቱ እየተደጋገፈ የህይወት ሂደቱ ቀስ በቀስ እየተለወጠ ነው፡፡አሁን ካለበት የደረሰው ፊቃደ(1991፤47-48) ይህ ሁሉ ሲጠቃለል ለሰው ልጅ ለአሁንነቱ ጥንታዊነቱ መሰረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ወይም ለአሁኖቹ  ዘመናዊ ፖለቲካዊና የእምነት ስርዓቶች ጥንታዊ ወይም ባህላዊው የአስተዳደርና የእምነት ስርዓቶች ጠንካራ መሰረት ነበሩማለት ይቻላል፡፡እዚህ ላይም የየምን ባህላዊ የንግስና አስተዳደር ስርዓት መጥቀስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ የሞች በአካባቢያቸው ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ከመዘርጋቱ በፊት ከህይወት ልምዳቸው ባገኙት ዕውቀት ላይ ተመስርተው ያበጁት ባህላዊ ኅሳዊ የንግስና አስተዳደር ስርዓት ነበራቸው፡፡የየምን ብሄረሰብ ባህላዊ አስተዳደር (የንግስና ስርዓት የተረዳ ሰው በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ውስጥ የሚተገበረው ፓርላሜንታዊ ስርዓት ምንጬ(መሰረቱ) የየም ባህላዊ የንግስና አስተዳደር ስርዓት ይሆንን? ብሎ ማሰቡ አይቀርም፡፡

### 3.1.3 ባህላዊአስተዳደር

በመጀመሪያ ስለ ባህላዊ አስተዳደር ፈረንጆች (Local Government ወይም Traditional Government ወይም Native Government) ብለው ስለሚጠሩት ማለት ነው፡፡ምሁራን የሰነዘሯቸውን ሀሳቦችና ፤የሰጧቸውን ብያኔዎች ብንመለከት ወንድወሰን አውላቸው(1998 ዓ.ም) Nsarkoh (1964፡13 ) ጠቅሶ እንደገለጸው ባህላዊ አስተዳደር ከማዕከላዊ መንግስት (Central Government)አስቀድሞ የነበረ እንደሆነና በልማዳዊ ህግ እና በአካባቢያዊ ደንብ  የሚመራ ስርዓትነው በማለት ገልጿል፡፡

Harris (1957) የተባለው ጸሃፊ ናይጄሪያን ዋቢ አድርጎ እንደ አንድ ልዑላዊ ሀገር ወይም መንግስት ከመቆጠሯ አስቀድሞ ቢያንስ ቢያንስ በመንደር ደረጃ ወይም ከዚህ ሰፋ ያለ አስተዳደራዊ ስርዓት በናይጄሪያ ውስጥ ሲተገበር የነበረ መሆኑን በመጥቀስ የ«Nsarkoh»ንሐሳብ ይጋራል፡፡

አሜሪካና ታላቋ ብሪታንያም ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓትን በተመለከተ የራሳቸው አመለካከትና ግምት አላቸው፡፡አሜሪካውያን ለባህላዊ አስተዳደር

ያላቸው አመለካከትና ግምት ላቅ ያለ ነው፡፡ለዚህ በጎ አመለካከት መሰረታዊ ምንጩ ደግሞ ‹‹The less government the better» የሚለውና ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረው የሃገሪቱ መሰረታዊ መርህ ነው፡፡ በታላቋ ብሪታንያበስፋት በብሪታኒያ የጋራ ብልጽግና ሃገሮች ዘንድ ደግሞ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት እንደ አንድ ታላቅ የፖለቲካ ትምህርት ቤት፣የአኗኗር (የህይወት) እና የባህርይ ማነጺያ ተቋም ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡ (Nsarkoh 1964:13)::

እነዚህ ቀደምት አባታዊ ስርዓቶች (Paternal government) ጊዜው ያለፈባቸው ፣ የተረሱና ለመጪዎቹ ስርዓቶች የሚያበረክቱት (ያበረከቱት አንዳች ፋይዳ የሌላቸው) ተደርገው ቀርበው አያውቁም፡፡በጸሐፊው እምነት በባህላዊ አስተዳደር ውስጥ በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሹማምንት ፣በሙስና የዘቀጡ፣ ለቦታው ብቃት የሌላቸውና ተገቢ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡በመሆኑም ይህ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት እንደዚህ ዓይነቶች አላስፈላጊ ሰዎች ባለስልጣናት በስልጣናቸው ላይ እስከ ወዲያኛው እንዲቆዩ ወይም ስልጣናቸው ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ የክፉ ስርዓት ተምሳሌት ነው ሲል ገልጿል፡፡(Wraith 1953:33)ን በመጥቀስ ግርማ ቡኬ(2003 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ Sklar (1999:117-118) እና Bahru (2006:18) ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓቶች ጊዜ ያለፈባቸውና ረብ የለሾች ሳይሆኑ ዛሬም ድረስ በበርካታ ወገኖች የሚፈለጉ፣ቀደም ሲልም ለዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት መሰረት የሆኑ መሆናቸውን በመጥቀስ የ Wraith ን ሐሳብ ያጣጥሉታል፡፡ ለዚህ የመከራከሪያ ሃሳባቸውም የተለያዩ የአፍሪካ ሕዝቦችን ተሞክሮ በዋቢነት ይጠቅሳሉ፡፡ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአፍሪካ ውስጥ የተካሄዱትየጸረ-ቅኝ አገዛዝ ትግሎችና ንቅናቅዎች በእነርሱም የተገኙ ውጤቶች ፣በባህላዊው የፖለቲካ ስርዓት የታገዙ ነበሩ፡፡ ከነጻነት በኋላም ቢሆን ከበፊል ባልተሻለ ወታደራዊ አገዛዝ ስር የወደቁና በሙስና የተዘፈቁ የአፍሪካ አገሮች ከዚህ ከብልሹ ስርዓት ለመላቀቅ ሲሉ ወደ ኋላቸው ተመልሰው ከቅኝ  የአገዛዝ ስርዓት በፊት የነበረውን ባህላዊ የፖለቲካ

ስርዓታቸውን መልሰው ለማደስና በስራ ላይ ለማዋል ተገደው እንደነበር እነዚህ ጸሐፍት ያትታሉ፡፡

የምዕራብ አፍሪካን ባህላዊ አስተዳደር ስርዓት ያጠኑት Fortes እና Earns (1940፡6-7) የምዕራብ አፍሪካ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓቶችሶስት መልኮች እንደነበራቸው እንደሚከተለው ጽፈዋል፡፡

«The indigenous political systems of the parts of west Africa…Would appear tofall into one or another of the three types…In which the political structure and kinship organization are completely fused; those in which lineage structure is the framework of political system and finally, those to be found in largergroup in which an administrative organization is the frameworkof the political structur»

Cowan (1995፡4-5) የተባለው ጸሐፊ ደግሞ የአፍሪካ ህዝቦች አገር በቀል የአስተዳደር ስርዓቶች የሚጋሯቸው ወይም ተለይተውየሚታወቁባቸው ባህርያት እንዳሏቸዉ ያስረዳሉ፡፡ከእነዚህ መለያ ባህርያት መካከልም በባህላዊ ንጉስ ወይም በባለአባት የሚመሩ መሆናቸው አንዱ መሆኑን ይጠቅሳሉ ፡፡የአፍርካ ማሕበረሰቦች ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓቶች ውስጥ ቁንጮ ላይ የተቀመጡ ባህላዊ መሪዎቸ ምንም እንኳን በአማካሪዎች እየታገዙ የሚሰሩ ቢሆንም ጥቂቶቹ የለየላቸው አንባገነኖች (Complete autocrats) መሆናቸውን ይሄው ጸሐፊ ያስረዳል፡፡በአማካሪነት የሚመደቡላቸው ደግሞ ከባህላዊ ነገስታቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት (የስጋ ዝምድና የሌላቸው) ታዋቂ አዛውንቶቸ አሊያም የጎሳ መሪዎች ናቸው፡፡የአማካሪዎቻቸውን ምክር የማይቀበሉ መሪዎች ደግሞ በስልጣናቸው ላይ ብዙ እንደ ማይቆዩ ብዙ የአፍሪካ ህዝቦች የማህበረሰቡን ልማድ ወይም ደንብ የሚጥሱትን ባህላዊ መሪዎቻቸውን የሚቆጣጠሩበት ባህላዊ ስርዓት ያላቸው መሆኑን እንዲህ በማለት ያስረዳል፡፡ግርማ ቡኬ(2003፣18)

by acouncil.so few traditional chiefs in the political systems of Afirica could be considered competeAutocrats.In almost every case they were assisted me times made upOfelders or of the heads of other lineages within the group.while the chief was notObliged to accept the advice of his council,no chief who expected to remain long Inoffice wouldbe un wise enough to ignore his council consistently.many tribes hadClearly defind traditional procedures for getting rid of a chif who had overstepped the Bounds of tribal mores (Cowan,1995:5-6 )

ይህም የሚያሰው የአንድን ህዝብ ታሪክ ፣ወግና ስርዓት በሚገባ ለማወቅ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል አንዱ የባህሉ ባለቤቶች የሆኑትን ህዝቦች ቃላዊ ተረኮች በሚገባ ማጥናት ተገቢ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚሰበሰብ መረጃ ደግሞ የታሪኩ ባለቤት የሆነውን ህዝብ ይገልጻል፡፡ቃለ ትረካ በመነገር፣በመተረት፣በመተረክና በመዜም የሚተላለፉትን እንደ ተረቶች ፣ቀልዶች፣ዘር ቆጠራዎች፣አፈ-ታሪኮች፣ሀተታ ተፈጥሮዎች፣ዜና መዋዕሎች ፣ገድሎች የመሳሉት የስነ-ቃል ዓይነቶች የሚመለከት ነው፡፡(ዘሪሁን 1996፣27) ቃለ-ተረክ በልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ዘንድ የሚስተዋል የሰው ልጆች ሁሉ ባህል ነው ሊባል የሚችል አንድ የስነ-ቃል ቅርጽ ሲሆን የሰው ልጆች ያለፈ ታሪካቸውን፣ገጠመኞቻቸውን፣እውቀታቸውን ፣እምነታቸውን፣ፍልስፍናቸውን የሚገልጹበት መሆኑን (ሜሩካ 1994፡76)ን በመጥቀስ ግዛቸው ኪዳኔ(2007 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡

ቃላዊ ዝርው ተረክ የአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚ ፣ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ እሴቶች የሚንጸባረቅበትና የማህበረሰቡ አጠቃላይ የማንነት መገለጫ አሻራ ነው፡፡ቃላዊ ዝርው ተረክ በማንኛውም በተለይ ደግሞ ቃላዊ በሆኑ ህብረተሰቦች ውስጥ የታሪክ ማህደር ነው፡፡አንድ ህዝብ ያለፈ ታሪኩን

፣ባህሉን፣ወግና ልማዱን ጠብቆ ያኖረበት፤ለቀጣዩ ትውልድም ያስተላልፍበታል፡፡ስለ ህይወት ያለውን ግንዛቤ፣አተያይ፣ይበል ይበል የሚለውና የሚያነውረውን እሴቶቹን አጠንክሮ እየገለጸ ትውልድን ያስተምርበታል፣ይቀርጽበታል፡፡ውስጣዊ ስሜቱን ቀርጾያሳይበታል፡፡(ዝኒ ከማሁን 1994፣76) በመጥቀስ ግዛቸው ኪዳኔ(2007 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡

ወደ አራቱ ተግባራቶች ስንመለስም የማስተማር፣ የማምለጥ፣ የመቆጣጠር እና የማረጋገጥ ወይም የማጽደቅ የሚሉትይጠቀሣሉ፡፡

**የማስተማር**፡- ይህ የተግባር ዓይነት ሰዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ማኅበረሰቡን መስለውና ሥርዓት ይዘው እንዲቆዩ ያደርጋቸው ዘንድ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚከናወኑትን እያንዳንዳቸውን ድርጊቶች የሚማሩበት ነው፡፡ ለምሳሌ ያቀማመጥ፣ ያለባበስ፣ ያወራር፣ ያመጋገብ፣ ያጠጣጥ ወዘተ፡፡

**የማምለጥ**፡- እንደ Smith (2005፡176)፡፡ ገለጻ የማምለጥ ተግባር ባህልና ልማድ በሰው ልጅ ላይ ከጫነበት ደንብ እንዲቀሰቀስ ከወሰነበት ባህላዊ ቁስ ድንበር በተለያዩ ፎክሎሮች በመዝናናት የሚያመልጥበት ነው፡፡ የማምለጥን ተግባር በጂኦግራፊ ከተተከለበት ከጠባብ መንደሩ፣ በጥቅሉም ከምድራዊው ቁሳዊ አጥርና ድንበር በምናቡ ያመልጣል፡፡ ባዮሎጂያዊ ባህርይ አልፈቅድ ብሎ ሊያደርግ የሚፈልጋቸውን፣ ግን ሊያደርግ የማይችላቸውን ድርጊቶች የሚፈጽምባቸው ሥነ ቃሎች አሉ፡፡ ፈቃደ(1991፡19)

በመሆኑም የሰው ልጅ በፎክሎሩ አማካይነት ውስጡ ያለውን ስሜት ለመግለጽ ያስችለው ዘንድ ለማምለጥ ይጠቀምበታል፡፡ ለምሳሌ ቅኔ ዘራፊው ስሜቱን በቅኔው ይገልጻል፤ የውስጡን ስሜትም በዚያ ውስጥ ይተነፍሳል፤ የማምለጫ መንገዱን በዚያ ትንሽ ቀዳዳ ውስጥ ይጠቀምበታል፡፡

**የመጠበቅ**፡- ይህ የመጠበቅ ተግባር ዓላማው አንድ ጎሳ ወይም ማኅበረሰብ በተለምዶ የሚከተላቸውን የአኗኗር ልምዶችና ባህሎች ግለሰቡ እንዲከተል በማድረግ  ማኅበሩ ምስጉንና ድንቅ ከሚላቸው ዕሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳርዳር የሚሉትን “በአርፈህ ተቀመጥ” ግሣጼ ወደ ብዘኃኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው (ፈቃደ1991፣20)፡፡ ይህ ተግባርም ማኅበረሰቡ በሥሩ ላሉት ትክክል አይደለም ለሚላቸው ተግባራቶች

እንዳይዳረጉ ማኅበረሰቡ የነበረውን ሥርዓት እንዳያጣ፣ ያለውንም ለማስጠበቅ እንዲረዳው የሚጠቀምበት የተግባር ዓይነት ነው፡፡

**የማረጋገጥ**፡-Dorsen (1972፣22) ቡድናዊ ፎክሎር በሐተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶችን፣ሥርዓቶችንና ባሕርያት የማጽደቅ ተግባር አለው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ፈቃደም(1991፣18) ይህንኑ ሐሳብ ሲያጠናክሩ ሰዎች ራሳቸውንና ቁሳዊውን ዓለም ለመግለጽና፣ በጊዜው በነበራቸው ዓቅምም ለመረዳት እንደሞከሩ ይጠቁማል፡፡ ይህንኑ ፈር ተከትለው ማኅበራዊ ድርጊቶቻቸውን እና ልዩ ልዩ ባህሎቻቸውን በሥነ-ቃል አማካኝነት ያጠናክራሉ፡፡ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነትእያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ይላሉ፡፡ ይሁንእንጂበዚህጥናትውስጥአራቱምተግባራትየማይካተቱመሆኑንልጠቁምእወዳለሁ፡፡

## 3.2 የተዛማጅጥናቶችቅኝት

ይህ ክፍል ከዚህጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ቀደምት የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች የተዳሰሱበት ሲሆን በባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና ዙሪያ በቀጥታ የሚገናኙ ስራዎች እስከ አሁን ባደረኩት ፍተሻ ላገኝ አልቻልኩ፡፡ ነገር ግን በባህላዊ አስተዳደርና በሌሎች ማህበረ ባህላዊ እንድምታ ተረኮች ዙሪያ የተጠኑ ጥናታዊ ጽሑፎችን ለመዳሰስ የተሞከረበት ክፍል ነው፡፡

ወንድወሰን አውላቸው /1998 ዓ.ም/ ‹‹የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት››፡፡በሚል ርዕስ ለኤምኤ.ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓላማ የሰባት ቤት ጉራጌን ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት አመሰራረት፣አወቃቀርና አሰራር ማሳየት፣በማህበረሰቡ የሚታዩ ግጭቶችን፣የግጭት ማስወገጃ ስልቶችን መተንተን ሲሆን የጥናቱ ግኝትም ብሄረሰቡ የተለያዩ የግጭት መፍቻ ተቋማት (ሴራዎች) ያሉት እንደሆኑና እነሱም የዛሬ ሶስት መቶ አመታት አካባቢ ሲገለገሉባቸው እንደነበር

፤ዓይነታቸውም የባሪያ አስተዳደር ህግ (የኬት ሴራ)፣ የጋብቻ ሕግ (የአንቂት ሴራ ) የወንጀልና የፍታብሄር ሕጎችን አጣምሮ የያዘ የአስተዳደርና የፍትህ ስርዓት (ቂጫ) እንደሆነ የገለጸ ሲሆን የግጭቶቹ መንስኤዎች ስልጣን ፣ወሰን፣የተፈጥሮ ሐብቶችን፣እሴቶችን ወይም ማህበራዊ ደረጃዎችን ለመቆጣጠር በሚኖር ፍላጎት ወይም በተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት እንደሆነ አሳውቋል፡፡እነዚህም የግጭት ዓይነትቶች ሲያጋጥሙ ከላይ በተዘረዘሩት የግጭት መፍቻ ተቋማት(ሴራዎች) አማካኝነት እንደሚፈቱ ገልጿል፡፡የዚህ ጥናት ድክመት ነው ብዬ ያየሁት ስለ ባህላዊ አስተዳደር ሚና፣የማስተዳደሪያ ስልት ወ.ዘ.ተ ግኝቱን በግልጽ አለማቅረቡ ነው፡፡

አበበ ኃይሉ/1999 ዓ.ም/ ‹‹ሀገረሰባዊ የአስተደደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሄረሰብ››፡፡በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ ማሟያ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ የጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው በአኝዋ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓት ተቋማዊ አደረጃጀት ስለ መሪዎቹ የመመዘኛ መስፈርት፣የበዓለ ሹመት ስነ-ስርዓቶችና ክዋኔዎች፤ስለሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ፎክሎራዊ ገጽታዎችን መግለጽና ማብራራት ሲሆን በጥናቱ ያገኘው ግኝትም አኝዋዎች ሁለት አይነት ባህላዊ የአስተዳር ስርዓቶች እንዳላቸውና እነሱም በኚያና (ንጉስ) ኳሮ (የቀበሌ ሹም) እንደሚተዳደሩና ሁለቱም ባህላዊ አስተዳደሮች ተመሳሳይ አወቃቀርና አደረጃጀት እንዳላቸው፤በክልሉ ካሉት 10 ወረዳዎች መካከል የአበቦና የጆሮ ወረዳዎች አሁንም በከፊል እንደሚተዳደሩበት ስልጣኑም በዘር ሐረግ እንደሚያዝና ሁለቱም የአስተዳደር ስርዓቶች መሪዎቻቸው ማለትም ‹‹ኚያና ኳሮ›› ሲሞት በአባቱ ኑዛዜ መሰረት የተመረጠ ልጅ ስልጣኑን እንደሚወርስና ለሴቶች ግን ስለሰጣኑ እንደማይፈቀድላቸው ፤ሌላው የያዘው ክፍል ህዝባዊ ድጋፍ ከሌለው በሰላማዊ መንገድ እንደሚለቅ ካልሆነም በሃይል እንደሚያስለቅቋቸው ፤ሌላው በአኝዋ የህይወት ፍልስፍና ለስልጣን የሚያበቃ ህዝብ እንደሆነ ፣በተጨማሪም በብሄረሰቡ የግጭት መፍቻ ተቋም ስርዓትና ልማዳዊ ህጎቻቸው መሰረት በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈታ ገልጿል፡፡

ግርማ ቡኤ /2003 ዓ.ም/‹‹የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር እና እምነት››፡፡በሚልርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ላይየጥናቱ ዓላማ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ከአስተዳደር ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ እምነታዊ ድርጊቶችን በገለጻ ማሳየት የሚል ሲሆን የጥናቱ ዘዴ ኳሊቴቲቭ ሪሰርች(QulitativeResearch Methodlogy) ይከተላል፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ሲሆኑ በጥናቱ ግኝትም ቡርጂዎች ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓትን የሚከተሉና የጎሳ፣የህግና ክልላዊ የሚባሉ ሶስት ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት ያሏቸው መሆኑን አመልክቷል፡፡ሌላው በቡርጂ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ጠንካራውና ወሳኙ የጎሳ አስተዳደር ተቋምመሆኑን አመልክቷል፡፡ በተጨማሪም የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች ተቀዳሚ ተግባር ስለህዝቡና አካባቢው መጻኢ.ሁኔታ በማስጠንቀልና በመስተንበይ ህዝቡን፣የህዝቡን ንብረትና ህዝቡ የሚኖርበትን አካባቢ ወደፊት ይደርሳሉ ከሚባሉ ክፉ አጋጣሚዎች ማለትም ከበሽታ፣ከጦርነት፣ከረሃብ ወዘተ መከላከል መሆኑን መሪዎቹ በራሳቸው ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ሃይል የሌላቸው ነገርግን ተግባራትን በጠንቋዮች (Magico religion) በተንባዮች እና«ጋን»(gann) የሚባሉ ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ሃይል ያላቸው ተብለው በሚታመኑ ባህላዊ የእምነት መሪዎች በመታገዝ መሆኑን በግኝቱ አስመልክቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪም በጥናቱ እንዳሳወቀው የቡርጂ ህዝቦች በሙታን ሰዎች የሚያምኑ መሆናቸውንና በሙታን ሰዎች የሚያምኑት ሙታን ወገኖች ለቡርጂዎች ለፈጣሪ የቀረቡ ፣ከፈጣሪ የሚያማልዱ በህያዋን ወገኖቻቸው ላይ ያሻቸውን ማድረግ የሚያስችላቸው ልዩ ሃይል ያላቸው ናቸው ብለው ማመናቸውና የሙታን ወገኖች እርግማንና ምርቃት ለአካባቢው እድገትና ልማት ጭምር ወሳኝ መሆኑን፣በቡርጂ ሃገረሰባዊ ሃይማኖት ውስጥአንዱ የበላይ ሌላው የበታች ወይም አዛዥና ታዛዥ ያለበት አሰራር እንደሌለ በጥናቱ ያሳየ ሲሆን ይህንን የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት የአሰራር ስርዓት በተለያዩ የዓለም ሃገሮች ውስጥ እየተተገበረ ያለውንየዲሞክረሰሲያዊ ስርዓት በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥም

እንደሚታይና ባህላዊ ስርዓቱም ሙሉለሙሉ የወንዶችን የበላይነት የሚያንጸባርቅ መሆኑን በጥናቱ አሳውቋል፡፡

የግርማ ቡኤና የእኔ ጥናት የሚያመሳስላቸው በሁለታችንም ጥናቶች ውስጥባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች የተዳሰሱበትና እነዚህም ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች በባዕድ አምልኮዎች ላይ የተንጠለጠሉ መሆናቸውና በሁለታችንም የጥናት ብሄረሰቦች ውስጥ ባህላዊ አስተዳደርናአምልኮኣዊ ስርዓቶች ውስጥ የወንዶች ተሳትፎ ሙሉበሙሉ መታየቱ ሲሆን ልዩነታችን ከጥናት ርዕስ ጀምሮ እስከ አካባቢያዊ ዳራችን ድረስ ልዩነት አለን፡፡

ሳምራዊት ዘውዱ/2002 ዓ.ም/ ‹‹በጎንደር ከተማ ውስጥ ስለሚገኙ የነገስታት ግንቦች የሚነገሩ አፈ ታሪኮችና ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና››በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ያቀረበች ሲሆን የጥናቷ ዓላማ በጎንደር ከተማ ውስጥ ስለሚገኙ የነገስታት ግንቦች የሚነገሩ አፈ ታሪኮችና ቃል ግጥሞች ይዘታቸውን ለመተንተን ሲሆን የጥናቷ ግኝት ደግሞ አፈ ታሪኮቹ ከነገስታቱ ግንቦች ከግንባታ በፊት፣በግንባታ ጊዜና ከግንባታ በኋላ የተከናወኑ ድርጊቶችን ፣ሁነቶችንና እንቅስቃሴዎችን የሚያሳዩ እንደሆነ ቃል ግጥሞቹ ደግሞ ስለ ግንቦቹ ዘላለማዊ ቅርስነት፣ውበትና ማራኪነት በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ዜጎች የሚናፈቁ መሆናቸውን ስለተሰሩበት ጥሬ ዕቃዎች ወ.ዘ.ተ የሚገልጹ እንደሆኑ ገልጻለች፡፡

ለማ ንጋቱ / 1999ዓ.ም/ "በየም ብሄረሰብ ያታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና" በሚል ርእስ ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በየም ብሄረሰብ የሚተረኩ ያታ ተኮር ተረቶችን ሰብስቦ በተረቶቹ ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ መተንተን ነው፡፡ ተረቶቹን በዘር መመደብ፣ ተረቶቹን ያታዊ ምስልን የሚያንፀባርቁባቸው መንገዶች መለየት እና ያታ ተኮር ተረቶችን ከነ አውዳቸው አደራጅቶመሰነድየሚልዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ እነዚህ አላማዎችን ለማሳካትምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ከ23 የብሄረሰቡ አባላት 104 ተረቶቸን እንደሰበሰበ በመግለፅ፣ከነዚህ ውስጥም ያታዊ ምስልጎልቶ ይታይባቸዋልያላቸውን 66 ተረቶች መርጦ ትንተና አካሂዷል፡፡ በጥናቱ ግኝትም ተረቶቹ በብሄረሰቡ አጠራር "ቶቾ"

እና “ኤሻ” ተብለው እንደሚጠሩገልጿዋል፡፡ “ቶቾ” የሚባለት እውነት ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ሲሆኑ “ኤሻ” የሚባለት የግሞ የፈጠራ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው እንደ ሆኑ አጥኚው ገልጿል፡፡ተረቶቹን ከአካባቢያዊ አመዳደብ ባሻገር አፈ ታሪክ፣ ሚታዊ አፈ ታሪክ እና ገላጭበማለትሊመደቡ እንደሚችሉገልጸዋል፡፡ የለማ ጥናት በግኝቱ እንደሚያሳየው በአፈ ታሪክ እና በገላጭ ተረቶች ላይ ወንዶች በአዎንታዊ መንገድ ማለትም ንፁህ እና የበላይ፣ ሴቶች ደግሞበአሉታዊ መንገድ ማለትም የጎደፉ እና የበታች ሆነው እንደተሳሉገልጸዋል፡፡

የእኔ የጥናትና የለማ ጥናት በተመሳሳይ ብሂረሰብና በተረኮች ዙሪያ መሆኑ የሚያመሳስለን ሲሆን ልዩነታችን የለማ ጥናት ርዕስ‹‹ በየም ብሂረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና›› በሚል ሲሆን ዓላማውም በብሂረሰቡ በሚተረኩ ተረቶች ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ ማሳየት ነው፡፡የእኔ ጥናት ርዕሰ ደግሞ ‹‹የየም ብሂረሰብ የአንገሪ ቤተ መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር ተረኮች ይዘት ትንተና›› ሆኖ የጥናቴ አላማም በየም ብሂረሰብ የአንገሪ ቤተ መንግስት ባህላዊ የንግስና ሽግግር አመጣጥ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ማህበረ ባህላዊ አንድምታ መመርመር ነው፡፡

ማንያለው አባተ/1999ዓ.ም/‹‹የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው››በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ጥናት ያቀረበ ሲሆን የጥናቱ አላማ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቦ ማህበራዊ ፊይዳቸውን በተመለከተ ትንተና ማድረግ እና በብሂረሰቡ ዘንዴ ተለይተው ሚታወቁ ተረኮችን በመለየት ባህርያቸውን ማሳየት ነው፡፡ ማንያለው የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ዘዴዎችምልከታና ቃለ መጠይቅ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች ተጠቅሞ 97 ዝርው ተረኮችን ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡትን ተረኮች ምደባ የተደረገባቸው ሲሆን፣ በአካባቢያዊ ምደባ “ቶስ” እና “ኤሽ” ተብለው እንደሚከፈሉ ገልጸዋል፡፡ “ቶስ” በመባል የሚታወቁት እውነት ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ሲሆኑ “ኤሽ” የሚባለት ደግሞ የፈጠራ እንደሆኑትገልጸዋል፡፡

የማንያለው ጥናት  የቤንች ዝርው ተረኮች የማዝናናት እና የማስተማር፣ የብሄረሰቡን አመጣጥ ማሳየት፣ አንድ ግለሰብከአካባቢው ነዋሪ ጋራ ተስማምቶ እንዴት መኖር እንዳለበት የማሳየት ፋይዳእንዳቸው አሳይቷል፡፡

ከሁሉም በላይ /2004 ዓ.ም / ‹‹የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት››በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ማሟያ ጥናት ያደረገ ሲሆን አላማ አድርጎ የተነሳውም በተረኮቹ አማካይነት የማህበረሰቡን ስያሜ አመጣጥ ፣አምልኮ፣የስራ ፈጠራ ወይም ባህል እርግማንና ከውሃ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሳየት ሲሆን ተረኮቹንምእንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በተመሳሳይ በይዘት ለመመደብ ጥረት ያደረገ ሲሆን ባህላዊ ስርዓቶቹም የማህበረሰቡ አምልኮታዊ ስርዓቶች (የአቢዝና) የግርዛትና የሰርግ በማለት ከፋፍሎ አሳይቷል፡፡በጥናቱ ግኝትም ለማሳየት የሞከረው ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የማህበረሰቡን ስያሜ አመጣጥ፣አምልኮ፣የስራ ባህልና እና ደህንነታቸውን አስመልክቶ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሚያደርስባቸው ተጽእኖ ወይም መገለል ምላሽ የሚሰጡ ፣የማህበረሰቡ አባላት በማንነታቸው የሚኮሩና በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያደርጉ እንደሆኑ አብራርቷል፡፡በተጨማሪም የግርዛት ስርዓት የሚፈጸመው ተገራዡ ልጅ ጀግና፣አዳኝ፣መከታ ወይም ደም መላሽ ከሚል አስተሳሰብና የሠርግ ስርዓቱ ደግሞ በማህበረሰቡ መካከል መረዳዳትና መተጋገዝ ባህላቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

ትግስት አለማየሁ /2004 ዓ.ም/ ‹‹ የአገው (አዊ) ብሄረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፋይዳ››በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ባቀረበችው ጥናታዊ ጽሑፍ የጥናቷ አላማ በዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ አባላት የሚተርኳቸውን የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፋይዳ መመርመር ነው፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቿ ቃለ መጠይቅ፣ምልከታና የቡድን ውይይት ሲሆኑ የጥናቷ ግኝት ደግሞ የአዊ ብሄረሰብ አባላት የሚተርኳቸውን የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ጥንተ አመጣጣቸውን ለመግለጽ፣አሰፋፈራቸውን ለማሳየት፣ ሌሎችማህበረሰቦች ከሚያሳድሩባቸው ስነ-ልቦናዊ ጫና ለማምለጥና ታዋቂ ግለሰቦች ከእነርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመግለጽ እንደሆነ አሳይታለች፡፡

መሪማ መሀመድ/2009 ዓ.ም/ የእንጦጦ ሐመረ ኖህ ኪዳነ-ምህረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፡፡በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሚያ ባቀረበችው ጥናት ላይ ዋና ዓላማ አድርጋ የተነሳችው ከእንጦጦ ሐመረ ኖህ ኪዳነ-ምህረት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ለገዳማውያኑና ለገዳማዊ ህይወት የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ላይ ሲሆን ግኝቷም ከገዳሚ አመሰራረት ጋር በተያያዙ በርካታ ልዩ ልዩ ተረኮች እንደሚነገሩ፣ እነዚህም ተረኮች የገዳሚን ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተልና በማስረጃነት እንደሚቀርቡና ቁሳዊ ባህሎቹም የተረኮቹን ማስረጃዎች ለማጎልበት በተጨማሪ ታሪክን የመንገር ዐቅም ያላቸው እንደሆኑ ያሳያል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4.የአጠናን ዘዴ

### 4.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የተሰራው ነው፡፡ ዓይነታዊ ምርምር በተወሰኑ ተለዋዋጮች ላይ የሚያተኩር ሳይሆን ተመራማሪው አንድን ችግር ይወስድና ውስን የሆኑ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያለውን ችግር በጥልቀትና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመዳሰስ መረጃዎችን የሚሰበሰብበትና የሚተነትንበት ሲሆን በንሞና ሂደትም የጠነከረና የዳበረ ሳይንሳዊ ሂደት አይከተልም ይህም ማለት በተለዋዋጮች፣ በቤተ ሙከራ የማይደገፉ፣ መረጃዎች በስታቲስቲካዊ ዘዴ የማይተነተኑ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ በዚህ የምርምር ዘዴ ተመራማሪው መረጃዎችን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢው የሚያቀርበው ትረካዊ (ገለጣዊ) መንገድን ተከትሎ ነው፡፡ያለው እንዳወቀ(2006፣19)፡፡

በመሆኑምይህንን የጥናት ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት ጥናቴ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ባህላዊ ንግስና ታሪካዊ አመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና ላይስለሆነየሰበሰብኳቸው መረጃዎች በስታስቲካዊ ዘዴና በቤተ ሙከራ የማይደገፉ በመሆናቸው ምክንያት ገለጣዊ በሆነ መንገድ የማቀርብ በመሆኑ ነው፡፡

### 4.2የንሞና ዘዴና የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት ዓላማ ተኮር (Purposive Sampling )የናሙና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ዓላማ ተኮር የተመረጠበት ምክንያት በጥናቱ ወሰን እንደተገለጸው በተጠቀሰው ቦታ ትክክለኛ መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን ማግኘት እንድችል ስለሚረዳኝ ነው፡፡ አንድ የመስክ ጥናት አጥኚ ወደ መስክ ሲወጣ መረጃዎችን በምን ሁኔታና ከነማን ማግኘት እንደሚችል ዓላማ ይዞ መውጣት እንዳለበት (Purposive Sampling)መጠቀም ደግሞ አላማውን ከግብ ለማድረስ እንደሚረዳው (Kumar 1991፣62) ይገልጻል፡፡ በዚህም

መሰረት ተጠኚዎቼ የየም ብሄረሰብ አባላት ሲሆኑበልዩወረዳውውስጥከሚገኙ 35 ቀበሌዎችመካከል አራት ቀበሌዎችን ማለትም አንገሪ ቀበሌ፣አያ ቀበሌ፣ኢዲያ ቀበሌና ፎፋ ከተማን በዋናነት በመያዝ በተጨማሪም በሌሎች በልዩ ወረዳዋ ቀበሌያት ዉስጥ የሚገኙ ታሪክ አዋቂ አዛውንቶችንና ሌሎች መረጃ በመስጠት የጥናቴን ዓላማ ለማሳካት ይረዱኛል ብዬ ያመንኩባቸውን 27 ሰዎች በመምረጥ ያሳተፍኩ ሲሆን ከጾታ አንጻር 25 ወንዶችና 2 ሴቶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በማህበረሰቡ ተረት መተረትና አፈ-ታሪክ ያውቃሉ የተባሉትን ሰዎችበማፈላለግ 84 ተረኮችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 4.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የጥናቴን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስናየምርምር ጥያቄዎቼን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮቼ ደግሞ በመስክ ከመረጃ አቀባዮቼ በአካል በመገኘት ሰብስቤያለሁ፡፡ በመስክ ላይ ተገኝቶ የሚደረግ የስነ-ቃል አሰባሰብ ተግባር በሶስት መንገዶች ሊከናወን እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ (Goldstien1964፣እናፈቃደ 1991)፡፡እነዚህ ዘዴዎች ተፈጥሮአዊ መቼት፣አርቴፊሻል መቼት እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት ናቸው፡፡እኔም በቃለመጠይቅና በምልከታ ተፈጥሮአዊ መቼትን ተጠቅሜ የመሰብሰብ አጋጣሚ አላገኘሁም ምክንያቱም ያባህላዊ ስርዓት ጥንታዊናአሁን የማይፈጸም ስለሆነ መረጃዎቼን አርቴፊሻል መቼትተጠቅሜ ሰብስቤያለሁ፡፡ተረክ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚተረክ በመሆኑ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ተገኝቶ መሰብሰብ አዳጋች በመሆኑ ነው፤አርተፊሻል መቼትን የመረጥኩት፡፡ፈቃደ(1991፣123)« በአርተፊሻል መቼት ተመራማሪው አንድን የስነ-ቃል ዘውግ ከአውዱ ውጪ በማንኛውም አቀባይ በተገኘበት ጊዜና ቦታ ሊሰበስብ ይችላል፡፡»በማለት እንደገለጸው እኔም ተረኮቹን በአርቴፊሻል መቼት ሰብስቤያለሁ፡፡እንግዲህ አርተፊሻል መቼትን በመጠቀም ተረት በመተረትም ሆነ በአፈ-ታሪክ ዕውቀታቸው ከታወቁ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡በካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቴ ጋር ተዛማጅነት ያላችውን የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፎች ሰብስቤ

ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት ተጠቅሚያለሁ፡፡ አንድ አጥኚ ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት ስለሚያጠናው አካባቢና ህዝብ በቤተ- መጻህፍት ጥልቅ ንባብ ማካሄድ አለበት፡፡በማለት Donald (1972፤407) እንደሚመክሩት የየም ብሄረሰብ ስለሚኖርበት አካባቢ፤ስለ ብሄረሰቡ አመጣጥ ታሪክ፤ስለ አካባቢያዊና ማህበራዊ ዳራው ፤ የባህላዊ ዳኝነት ስርዓት ወዘተ የተጻፉ ጽሑፎችን በማንበብ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡

## 4.4 የመረጃመሰብሰቢያዘዴዎች

ለአይነታዊ የምርምር ዘዴ መረጃ መሰብሰቢያነት የሚያስፈልጉዘዴዎችቃለ መጠይቅ፤የሰነድ ፍተሻና የተተኳሪ ቡድን ውይይት እንደሆኑና አስተማማኝ መረጃ ሊያስገኙ እንደሚችሉ(LisaM.Given፡volumes 1and2) እንደሚከተለው ይገጻሉ፡፡ ለአይነታዊ የምርምር ዘዴ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ግለሰባዊ ቃለ መጠይቅና ሰነድ (መዛግብት) ፍተሻ ናቸው፡፡ በግለሰባዊ ቃለ መጠይቅ መረጃ ሲሰበሰብ ጠቃሚ ዋጋ ያለው መረጃ ለማግኘት መረጃ ሰብሳቢው ከመረጃ ሰጪዎች አንደበት ከሚወጡ ቃላት መሰብሰብ አለበት፡፡ሌላው ከሰነድ ፍተሻ (መዛግብት)መረጃ ሲሰበሰብ ከህጋዊ ሰነዶች፣ ከግለሰቦች የውሎ ማስታወሻዎች፣ ከጋዜጦችና በተጨማሪም ከሌሎች ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ለምሳሌ ከፎቶ ግራፎች፣ ከተቀረጹ የቪዲዮ ምስሎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ ይላል፡፡በዚህም የተነሳ አጥኚዋ ለጥናቷ የሚሆኗትን ግብዓቶች በዋናነት በነጻ ቃለ መጠይቅ፣ በደጋፊነት በሰነድ(መዛግብት) ፍተሻና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡(Lisa M.Given EditoR;The SAGE Encyclopeia of Qualitative Research Methods.volumes 1and2)

### 4.4.1 ቃለ መጠይቅ

ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በተለይ ደግሞ ስነ-ቃሎችን ለመሰብሰብ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይልቅ ቃለ መጠይቅ ተመራጭነትና ተገቢነት እንዳለው ፈቃደ (1991፤96-97)፤Goldstein (1974:104) ይገልጻሉ፡፡በብልሃት ከተያዘ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ይልቅ ብዙ እውነታዎችን

ለማግኘት የሚያስችል መሳሪያ እንደሆነም አለም(1997፣69 )እና ዳንኤል እና ሌሎች (1994፣89)ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ይህንጥናትበማካሂድበት ወቅት የተጠቀምኩባቸው ስልቶች፤ ቀድመው በተዘጋጁነጻ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችእና ቀድመው ባልተዘጋጁነጻየቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ነው፡፡ ምክንያቱም ነጻ ቃለ መጠይቅ ለመረጃ ሰጪው ሙሉ ነጻነት የሚሰጥና ሰፋ ያለ መረጃ ለማግኘትም ጠቃሚ በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህም ሲከናወኑ በመቅረጸ ድምጽ በመቅዳት ፣በቪዲዮ ካሜራ በማንሳትና በማስታወሻ ደብተር በመመዝገብለጥናቴ ግብዓት የሆኑኝን መረጃዎች ሰብስቤያለሁ፡፡ ምክንያቱም ከመስክበቃለ መጠይቅ፣በምልከታና በሌሎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች ማለትም በፎቶ ካሜራ፣በመቅረጸ ድምጽና በቪዲዮ ካሜራ ሊታገዙ እንደሚገባቸው Dorson (1972:434-435); Goldstein(1974:9799)፤ Okpewho(1992:336-337 ፈቃደ(1991፣133-134)፣ያለውእንዳወቀ(2009፣186-187)እናLisa M.ያጠናክራሉ፡፡

4.4.2 የሰነድ/ መዛግብት/ ፍተሻ (Documents)

ምርምር በሚካሄድበት ወቅት እንደምርምሩ ባህሪና ዓይነት ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚያስችሉት ዘዴዎች አንዱ መዛግብት ፍተሻ ነው፡፡ ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ መዛግብት ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው ጠቃሚ መረጃዎች እንደሆኑ ያለው እንዳወቀ(2009፣55-56) ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ለጥናቴ አጋዥ ይሆኑኛል ያልኳቸውን የተያዩ የታተሙና ያልታተሙ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ፣ የየም ብሄረሰብ ታሪክ፣ የየም ህግ ስርዓት፣ የተለያዩ በልዩ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ስፖርት ጽ/ቤት የሚታተሙ መጽሄቶች፣ብሮሽሮች ፣በተለያዩ ምሁራን የተካሄዱ የጥናትና ምርምር ጽሁፎች፣ ካርታወ.ዘ.ተከመሳሰሉት የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን የሰበሰብኩ ሲሆን የትንተናዬም አካል አድርጌ ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡ምክንያቱም ጥናቴያለፈ ጥንታዊ ባህላዊ የንግስና ስርዓት አመጣጥ ተረኮች ላይ ያተኮረ በመሆኑና የስነ ቃል ዘውጎች ደግሞበተለዋዋጭነት ባህሪ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ የመለወጥና

የመጥፋት፣ሁኔታዎች ስለሚከሰቱባቸው ያለውንየመረጃውን ክፍተት የተሟላ ለማድረግ ስለሚረዳኝ ነው፡፡

4.4.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በችግሩ ዙሪያ በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ሲሆን ተሳታፊዎቹም ከ6 እስከ 12 ሰዎችሊደርሱ ይችላሉ፡፡ይህ ዘዴ ከቃለ መጠይቅ የሚለየው ዋናው ነጥብ በርካታ ሰዎች በአንድ ጊዜ መሳተፋቸውና የጠያቂው ሚና ግድብ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ያለው(2009፣197)

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከአንድ በላይ የሆኑ መረጃ አቀባዮች የሚሳተፉበት ሲሆን በተለይ በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች (መረጃዎች) በቡድን ስለመደገፋቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ በዚህ ዘዴ በመገልገልየንግስናውን ታሪክ በተገቢው ያውቃሉ ተብሎ የተመሰከረላቸውን8 ወንድ አዛውንት ሰዎችን ያቀፈ ቡድንበሁለት ዙር በማወያየት በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በቡድን ስለመደገፋቸው አረጋግጣለች፡፡

4.5የመረጃአደረጃጀትዘዴ

ከመረጃ ስብስባ በኋላም ከመስክ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ‹‹በየምሳ›› የተሰበሰቡትን መረጃዎች የማስተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡ፈቃደ (1991፣135) እንደሚመክሩት ከመስክ መልስ፤ከመስክ በፊት የተሰበሰቡት መረጃዎች መተርጎም አለባቸው፡፡ ለማ(1999 ፣5) Fine (1984:150 እ.ኤ.አ)ን ዋቢ በማድረግ እንደሚያስረዳው፡፡ ምንም እንኳን የመደበኛ አቻዊነት(Formal equivalence) እና የፍጹም አቻዊነት(Dynamic equivalence) የትርጉም ስልቶች ለፎክሎር ትርጉም የተለየ ጠቀሜታ እንዳላቸው ቢገለጸም ለዚህ ጥናት የሚስማማው የመደበኛ አቻዊነት የትርጉም ስልት ትኩረት የሚሰጠው በቅርጽምሆነ በይዘት የመገኛ ቋንቋውን መልዕክት ለመረዳት ነው፡፡ስለሆነም የመገኛ ቋንቋው(Target text) ጽንሰ ሐሳብ ጋር ከመመለሻ

ቋንቋው ጽንሰ ሃሳብ ጋር እንዲመሳሰል ወይም እንዲስማማ ጥረት ተደርጓል፡፡በአጭሩየመተርጎሚያው ቋንቋ መልዕክት በተቻለ መጠን ከመገኛ ቋንቋው የተለያዩ ክፍሎች ጋር መቀራረብ አለበት ይባላል፡፡በተጨማሪም Newmark (1998 እ.ኤ.አ) ዋቢ በማድረግ Okombo (1994:22) እንደሚያስገነዝበው የተለያዩ የትርጉም ዓይነቶች ቢኖሩም ከነዚህ መካከል አንዱ ከሌላው ተሽሎ ተመራጭ የሚሆነው ከሚተረጎምበት ጋር ተስማሚነት ሲኖረው ነው፡፡ስለሆነም የዚህ ጥናት ትኩረት በተረኮቹ መገኛ ቋንቋና ባህል የቀረቡበትን ሃተታዎች ቅርጽና ይዘት በመመርመር ለትንታኔው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ማውጣት ስለሆነ ለእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር የመደበኛ አቻዊነት የትርጉም ስልት ተስማሚና ተገቢ ነው፡፡ ለማ ንጋቱ(1999 ዓ.ም)፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ የትርጉም ስራ ሶስት ግለሰቦች የተሳተፉ ሲሆን የተመረጡበት ምክንያትም የብሄረሰቡ አባል የሆኑ፣ ባህሉን፣ ቋንቋውን (የምሳን) ጠንቅቀው የሚያውቁና የመተርጎሚያ ቋንቋውን(አማርኛን) በአንጻሩ በደንብ የሚችሉ በመሆናቸው ነው፡፡

በቃለ መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሜ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለየብቻቸው አደራጀሁ፡፡በመቀጠልም ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ የእርማት ተግባር አከናወንኩ፣እርማት ያደረኩባቸውን መረጃዎች መለያ እያደረኩባቸው በየርዕሰ ጉዳዩ ስር እንዲገቡ አሰናዳሁ፣ከዚያም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለየብቻቸው የመለየትና የእርማት ተግባር ከሰራሁ በኋላ ተመሳሳይነት ያላቸውን ይዘቶች ለየሁ፡፡ በማስቀጠልም ርዕስ ሰጠኋቸው፣ ከዚያም በእያንዳንዱ ርዕስ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ሃሳቦችን በመለየት የሃሳብ ቅደም ተከተላቸውን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ሰጥቻለሁ፡፡የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በሚከተሉት ርዕሶች የመደብኳቸው ሲሆን እነሱም የንግስናውን ታሪካዊ አመጣጥ የሚያሳዩ፣ ከየትኞቹ ጎሳዎች በምን መስፈርት ነገስታቱ እንደሚመረጡ የሚያሳዩ ፣ የንግስናውን አሰጣጡ ባሕላዊ ስርዓቶች የሚያሳዩ፣ በአንገሪ ቤተ መንግስት አመሰራረትና በነገስታቱ አመራር ዙሪያ የተነገሩ

አፈ ታሪኮችና የነገስታቱን የአመራር ጥበብ የሚያሳዩ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ነው፡፡

## 4.6 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

አንድ የፎክሎር ተመራማሪ በመስክ ተገኝቶ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ ጥናቱን ለማስኬድ የሚበጅ ቲዎሪ ማዕቀፍ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ምርጫውም ምክንያታዊና ቴክስቶቹን በሚገባ ለመተንተን የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡ የእኔ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በተረኮች ትንተና ላይ ስለሆነ የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሐሳብ (Functionalism Theory) ለመረጃዎቹ መተንተኛነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

ምክንያቱም የጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈ ሐሳብ ሎሮች ለአንድ ማህበረሰብ ወይም ለፎክ ቡድን የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ ነው፡፡የንድፈ ሐሳቡ አራማጆችም ተረቶች፣ ሚቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፣እምነቶችና ሌሎች ማናቸውም ነገሮች ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊ፣ ባህላዊ ስነ-ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሲሆን ‹‹ፎክሎር›› በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ዓይነት ትርጓሜና ጠቀሜታ አለው? የሚለውን የሚያጠኑበት ነው፡፡

ማርክ ግላዘር (1997፣386)እና(2007፣75-76)በተጨማሪም (Smith 2005፣176) ተግባራዊንድፈሐሳብፎክሎርበቡድንአባላትመካከልዋጋየሚሰጧቸውዕሴቶችመ ረጃዎችየመለዋወጫመንገዶችመሆናቸውንየሚያሳይነውሲሉይገልጹታል፡፡

በዚህ ምክንያት እኔም የባህላዊ ንግስናው ታሪካዊ አመጣጥ ዙሪያ የተነገሩት ተረኮች ማህበረሰቡን ከማስተማር፣ ከመትከል ፣ከመግታት(መቆጣጠር)፣ ከማስመለጥ ወዘተ ተግባራት አንጻርያላቸውን ማህበራዊናባህላዊ ፋይዳ ለማሳየትና ለመተንተን ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን የመተንተኛ መሳሪያዬ አድርጌ መርጫለሁ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## 5.የመረጃ ትንተናና ፍከራ

ይህጥናትየሚያተኩረውየየምብሄረሰብየአንገሪቤተ-መንግስትባህላዊየንግስናሽግግርተረኮችይዘትትንተናላይሲሆንበዚህክፍልበቃለመጠይቅ፣በመዛግብትፍተሻናበተተኳሪቡድንውይይትየተሰበሰቡመረጃዎችተተንትነውየቀረቡበትክፍልነው፡፡በመሆኑምበምዕራፍአራትበተለምኩትየመተንተኛዘዴናባበጀሁትንድፈሐሳባዊማዕቀፍአማካኝነትየተረኮቹንይዘትለመተንተንጥረትየማደርግበትክፍልሲሆንበመጀመሪያከመስክየሰበሰብኳቸውንተረኮችጥልቅንባብበማድረግናፍሬሐሳባቸውንበመመርመርበተረኮቹአማካኝነትየቀረቡይዘቶችንለማሳየትየምሞክርበትነው፤ይህንለማድረግምበመጀመሪያተቀራራቢይዘትያላቸውንበአንድምድብየመደብኳቸውሲሆንበአንድተረክውስጥከአንድይዘትበላይበሚኖርበትአጋጣሚጎልቶየታየውንይዘትመሰረትበማድረግምደባአካሂጃለሁ፡፡በዚህምመሰረትከመስክከሰበሰብኳቸውተረኮችመካከልለትንታኔየለየኋቸውን 61 ተረኮችበአምስትዋናዋናይዘቶችተመድበውበሰንጠረዥመልክየቀረቡሲሆንከመረጃብዛትአንጻርከብዙቁጥርወደጥቂትተደርድረውቀርበዋል፡፡ነገርግንትንታኔውየተሰጠውየንግስናውታሪካዊአመጣጥከሚያሳዩትጀምሮበቅደምተከተልእስከነገስታቱየአመራርጥበብድረስነው፡፡

| ተ.ቁ | የተረኩ ይዘት | የተረኩ መለያ ቁጥር | የተረክ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1. | የነገስታቱን የአመራር ጥበብ የሚያሳዩ | 33,34,35,37,38,45,46,47,48,49,51,52 53,54,55,56,57,58, | 18 |
| 2. | ባህላዊ የንግስና አመጣጡን የሚያሳዩ | 2,4,5,6,8,11,12,16,18,19,22,24, 26,29,36,39,60,61 | 17 |
| 3 | ከየትኞቹጎሳዎች በምንመስፈርትነገስታቱ እንደ ሚመረጡ የሚሳዩ | 1,3,7,9,13,20,21,22,23,25,27,28 30 | 13 |
| 4. | በአንገሪና በነገስታቱ ዙሪያ የተነገሩ ተረኮች | 10,17,40,41,42,43,44 | 7 |
| 5. | የንግስና አሰጣጡን ባህላዊ ሥርዓቶች የሚያሳዩ | 14,15,19,31,32,59 | 6 |
| | ጠቅላላ ብዛት | | 61 |

## 5.1 የባህላዊ ንግስና ሽግግር ታሪካዊ አመጣጥን የሚያሳዩ

በየም ብሄረሰብ ባህላዊ የንግስና ሽግግር ታሪክን በተመለከተ ሶስት ሥርወ መንግስታት እንዳለፉ ይነገራል፤እነዚህም የጋማ፣የጌመሎና የሞዋ ሥርወ መንግስታት ሲሆኑ በአንገሪ ቤተ-መንግስት ነገስታት የሞዋ ጎሳ አባላት ብቻ ይነግሱ እንደነበር፡፡የንግስና ሽግግሩ የሚደረገው ቀድሞ የነበረው ንጉስ በተለያዩ ምክንያቶች ሲለቅ ማለትም በሞት ወይም በዚያ ንጉስ የንግስና ዘመን ለህዝቡ የማይመቹ ሁኔታዎች ለምስሌ ረሃብ፣ድርቅ፣በሽታ፣ግጭት ወ.ዘ.ተ ሲከሰቱ የንጉሱ አማካሪዎች [4] (አስተሰሮች) ከህዝቡ ጋር ምክክር በማድረግ ያንጉስ እንዲለቅና ሌላ መሾም እንዳለበት ሲስማሙ ነው፤ ከተስማሙ በኋላ ለዚያ ንጉስ ስልጣኑን እንዲለቅ ይነግሩታል ፣እሺ ብሎ ከለቀቀ ለቀቀ ካልሆነ ግን በኃይል በጦርነት ያስለቅቁትና ከንጉሱ ልጆች የመጨረሻ ወንድ ልጅ ካለው ያነግሳሉ ከሌለውም ከወንድሙ ልጆች ለንግስና ብቁ የሆነውን ያነግሳሉ፡፡እናም የንግስና ሽግግሩ ከአባት ወደ ልጅ በዘር ሐረግ ሆኖ ጎሳንም መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በየም ብሄረሰብ ሶስት ጎሳዊ ሥርወ መንግስታት ህዝቡን ያስተዳደሩ ሲሆን የመጀመሪያው የጋማ ጎሳ ነገስታት ሲሆኑ የንግስና መቀመጫቸውም «ዝማርኣማ»በሚባል የኦያቀበሌ ውስጥ ነበር፡፡ ሁለተኛው ሥርወ መንግስት የጌመሎ ሥርወ መንግስት ሲሆን የጋማን ሥርወ በንግስት በማስወገድ ስልጣን ተረከበ፡፡የመጀመሪያው የጌመሎ ጎሳ ንጉስ ሼህ ድንቡል የሚባሉና ከየመን ፈልሰው ከመጡ ጎሳ እንደሆኑና የእስልምናን እምነትም ወደ የም እንዳመጡ ይነገራል፡፡ የእነዚህ ነገስታት መናገሻም «ካንፎቻ»በልዩ ወረዳው የሚገኝ በፎፋ ከተማ ዙሪያ የሚገኝ ቦታ ወይም የአሁኑ የፎፋ መድሃኒዓለም ቤ/ክ ጀርባ የሚገኝ ቦታ ላይ ነበር፡፡የመሊሳ ትክል ድንጋዮች በእኚህ በሼህ ድንቡል መቃብር ዙሪያ እንደተተከሉ ይነገራል፡፡

---

[4] አስተሰር የሚባሉት የንጉሱ አማካሪዎች ሲሆኑ የሚመረጡት ከ12 ጎሳዎች ነው፡፡ እነሱም ከሞዋ፣ከጋማ፣ከየሱ፣ከጌመሎ፣ከካማ፣ከአቦማ፣ከአብካማ፣ከሶኣላ፣ከካንከኑ፣ከጋዜው፣ከካንሽሮና፣ከካው ምናናቸው፡፡እነዚህ ከ300ው ጎሳዎች መካከል በመምራትና ሕዝብን በማስተባበር ብቁ ናቸው ተብሎ ታምኖባቸው የሚመረጡ ናቸው፡፡

በመጨረሻም የሞዋ ስርወ መንግስት የነገሰ ሲሆን የዚህ መንግስት መስራቾች የሆኑት ከደቡብ ዓረቢያ(ከየመን) ተነስተው በጎንደር አድርገው ወደአሁኑ የየም ምድር ከመጡት ጎሳዎች መካከል ሲሆኑ የክርስትናን እምነትና ታቦታትን ከጎንደር ይዘው በመምጣት በየም ምድር የክርስትና እምነትን ያስፋፉ እንደሆኑም ይነገራል፣ የንግስናውን ስልጣንም ከጌመሎ ጎሳ በመረከብ የንግስና መቀመጫቸውን በአንገሪ ቤተ-መንግስት በመቆርቆር በዚያ አድርገው ህዝቡን ሲያስተዳደሩ እንደነበርና የሥልጣን ሽግግሩም ከአባት ወደ ልጅ በመተላለፍ ከ12ኛው እስከ 19ኛው መ/ክ/ዘመን ማለትም እስከ ዓጼ ምኒልክየኢትዮጵያን ህዝብ አንድ አድርገው እስኪገዙ ጊዜ ድረስ የዘለቀ ጎሳዊ ሥርወ መንግስት እንደሆነ መረጃ አቀባዬ ሊቀ ስዩማን በቀለ ወ/ዮሐንስ በተረክ 4 እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፤በተጨማሪም ተረክ6 እና8ን ይህንኑ ይገልጻሉ፡፡

*ሲነገርእንደሰማሁትበመጀመሪያከጋማጎሳቀጥሎከጌመሎበመጨረሻም ከሞዋጎሳሆኖወደስልጣንይመጡየነበረበትሁኔታልክእንደፌውዳልስርዓ ትከአባትወደልጅሆኖነገርግንአስራሁለትሰዎች (አስተሰሮች) ልክእንደሚኒስተሮችያሉየንጉስአማካሪየሆኑሰዎችነበሩይባላል፡፡እነዚህ በየምብሔረሰብካሉትከ300 መቶበላይጎሳዎችመካከልበመምራትሰዎችንበማስተባበርየተሻሉናቸው የተባሉአስራሁለትጎሳዎችተመርጠውከዚያምከአስራሁለቱጎሳዎችደግ ሞከየጎሳውየጎሳውአባላትየሚመርጧቸውናቸው፡፡አስተሰር (የንጉሱአማካሪ) ሆነውየሚያገለግሉእነዚህከማማከርያለፈምስልጣንአላቸውይባላልእና ምንጉስየሚተካከሆነምእነዚሁአስተሰሮችበሚገባመክረው«ማንቢመርጥ ይሰራል?»የሚለውንተወያይተውለዛርአምልኮተፀልዮና፤ልክእንደብሉ ይኪዳንስርዓትመስዕዋትለአዞከቀረበበኋላመስዋቱንከተቀበለከሚመረጠ ውጎሳለቤተሰቡአንድወንድየሆነናሴትየማያውቅድንግል [5] ልጅተመርጦ ይነግሳል፡፡*



[5] ድንግል የሆነ ልጅ የሚመረጥበት ምክንያት ንግስናው በዛር መንፈስ የሚሾም በመሆኑ የዛር መንፈሱ ቅድስናን ስለሚፈልግ ከትዳር ውጭ ድንግልናን ማፍረስን ስለማይፈቅድ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 12 ሊቀ ስዩማን በቀለ ወ/ዮሐንስ፣ስለ ባህላዊ የንግስና አመጣጡ ማብራሪያ ሲሰጡ

በተረክ አራትእንደተገለጸው ሁሉ በተረክ ስድስትም ስለ ባህላዊ ንግስናው አመጣጥ አቶ ሃይሌ ቀልቢ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

*በጥንትዘመንበመጀመሪያንጉስየነበረውየጋማጎሳነበር፣ከዚምበጋማንግስ ናዘመንድርቅተፈጥሮስለነበርናሕዝቡበረሃብናበመሳሰሉት፣ችግሮችበጊ ዜውበመቸገራቸውየጋማጎሳንጉስንወግተውገድለው በማስወገድበምትኩ፣የሞዋጎሳዘርተፈልጎ “ በከኖሲ“ ፉጋወይም “ላምነው“ የሚባልፉጋአማካኝነት፣አስፈልገውየሞዋዘርበማግኘትመክረውበማሳመ ንአንግሰውከዚያምጊዜጀምሮየሞዋንጉስመንገስጀመረ፡፡ከዚያምጊዜጀም ሮየመጀመሪያውንጉስበሞትሲለይከዚያውጎሳሌላኢያሳመኑበማንገስቀጠ ሉበሞዋንጉስዘመንበጋማንጉስዘመንየነበረውረሀብችግርበሽታወ.ዘ.ተአ ልተከሰተምበተቃራኒውጥጋብ፣ጤናሰላማዊኑሮበመፈጠሩከኋላንግስናው በሞዋጎሳ*

*ፀንቶኖረ፡፡*

ከላይ ከቀረቡት ተረኮች እንደምንረዳው በሶስቱም ስርወ መንግስታት የንግስና አመጣጥ ስርዓታቸው ተመሳሳይ መሆኑና በሁሉም የንግስና አመጣጡ በጎሳና በዘር ሃረግ የተወሰነ መሆኑ፣ በተጨማሪም በ5.2 ስር ቀጥሎ እንደምናየው ባህላዊ የንግስና ሹመቱ የሚቀባው በዛር መንፈስ መሆኑና ማህበረሰቡ ያለው ባህላዊ እምነትና አመለካከት ተደምሮ በስልጣን ላይ ያለውን ጎሳ ብቻ ለንግስና እንደተመረጠ አድርጎ እንዲያስብና የስልጣን(የንግስና ሹመትን) እንዳይመኝ የሚያደርግ ስለሆነ የነገስታቱን የንግስና መብት የማስቀጠልና የማስጠበቅ፤የሌሎችን ጎሳዎች የስልጣን

ምኞት ብሎም እንዳያስ[6] ቡት የመግታት ተግባርን ይወጣሉ፡፡ቀጣዩ ተረክ 8ም ከንግስናው አመጣጥ በተጨማሪ የቤት መንግስቱን አመጣጥ ያሳያል

> *በየምብሂረሰብየንግስናአመጣጥታሪክበመጀመሪያየጋማ፣ከዚያየገሜሎበመ ጨረሻምየሞዋስርውመንግስትተያይዞየመጣሲሆንቀድሞከነበሩትበመተላ ለፍየሞዋስርውመንግስትትልቅቦታየነበረውናየመጨረሻዎቹናቸው፣ተብ ሎይነገራል፡፡በአንገሪቤተ-መንግስትከመመሰረቱበፊትየጋማየንግስናመቀመጫየነበረው "በዝማርአማ" በኢያቀበሌውስጥእንደነበረናየአንገሪንቤተ-መንግስትየመሰረቱትየሞዋነገስታትእንደነበሩየባህላዊንግስናስርዓቱንግን የወረሱትከቀድሞውከጋማ "ከዝማርአማ" ቤተ-መንግስትነገስታትነውተብሎይነገራል፡፡ሲሉአቶኪዳኔከበደየገለጹልኝሲሆ ንበተጨማሪምእንደጸሐፊውተክለጻድቅአገላለጽ* (1966፣163)

የየም አንገሪ ቤተ-መንግስት የተመሰረተውበጻድቁ ንጉሥ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት በ435ዓ.ም እንደነበር ነው፡፡ስለ አመሰራረቱም ጸሐፊው እንዲህ ብለዋል፡፡«ጻዲቁ ዮሐንስ ከባለቤታቸውና ከነፍስ አባታቸው ጋር አብረው ሆነው የተጠበሰ ዓሣ እየበሉ እርስ በርሳቸው ይወራረዳሉ፤ውርርዱም እንዲህ በሚል ነው «ዛሬ በዚህ ሰዓት እውነት የተናገረ ሰው ከተገኘ ይህ የተጠበሰ ዓሳ ነፍስ ዘርቶ ወደ ባሕሩም ተጥሎ ይኖራል፡፡አሉና ውርርዱን ከባለቤታቸው ጀመሩ ባለቤታቸው ግን ለንስሃ አባታቸው ቅድሚያ ሰጡ፡፡ እሳቸውም እንዲህ አሉ እኔ እሜቴን በጣም አፈቅራታለሁ የነፍስ አባትነት ክብሩ ቀርቶብኝ እሜቴን አግብቼ በደስታ በኖርኩ አሉ፡፡እሜቴም በተራዋ እኔም የንግስትነት ክብሩ ቀርቶብኝ የሚወደኝን ሰው አግብቼ በፍቅርና በደስታ በኖርኩ አለች፡፡ጻድቁ ዮሐንስም በተራቸው ይህ ሁሉ የዓለም

---

[6] ከሲኖ፣ላምነው የሚባሉት ፉጋ የሚባል ጎሳ ንዑስ ጎሳዎች ነው፤ይህ ማለት ለምሳሌ የሞዋ ጎሳ በተለያዩ ቦታዎች እንደመገኘታቸው የተለያዩ ስያሜዎች ተሰጥቷቸው የጎሳው ንዑስ ጎሳ ተብለው ይጠራሉ፤እነሱም አንገሪ ሞዋ (የነገስታቱ ቤተሰቦች)፣ ቱንታ ሞዋ፣ ኬጶ ሞዋ፣ ቶባ ሞዋ ወዘተ እየተባሉ አስራ ሁለት አይነት አንዳሉ ይነገራል፡፡

ዝባዝንኬ ክብሩ፣ሀብቱ፣ሥልጣኑ ሁሉ ቀርቶብኝ እጅግ አስፈሪ ወደ ሆነው ወደ ጊቤ ወርጄ የአንበሳ፣ የነብር፣ የተኩላና የልዩ ልዩ አራዊት መኖሪያ ውስጥ በስጋትና በሰቀቀን በኖርኩ አለ» ሁሉም እውነት እውነቱን ይናገሩ ነበርና  ዓሣውን ሲመለከቱ መንቀሳቀስ ጀመረ ንጉሱም ዓሣውን አንስተው በእንጨት ገበቴ ውስጥ ውሃ ሞልተው አስቀመጡትና ወደ ሐይቅ እንዲጣል አደረጉት፤ከዚያም ንጉሱ ወደ ጊቤ አራዊት መኖሪያ ገብተው መንነው መኖር ጀመሩ ቦታው ሰው የማይደርስበት ቦታ ስለነበር እንደ ገዳምም እንደ ቤተ-መንግስትም አድርገው ኖሩበት፡፡»ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የንጉሱ ዘሮች ዓሣን አይበሉም እንደ  አምላክም ያመልኩት ነበረ፤ ዓዞንም የዓሳ ዘር ነው ብለው ያመልኩት ነበር፡፡

ንጉሱም መጀመሪያ በነበሩበት በጎንደር እስከ ዛሬ ድረስም ጎኑ የተጠበሰ የሚመስል ዓሣ አጥማጆች ሲያገኙ የጻድቁ ዮሃንስ ዓሣ ብለው መልሰው ወደ ሐይቁ ይወረውሩታል ይባላል፡፡ በወቅቱ የንጉሱ ምክትል የነበረው ሰው «ጊዮርጊስ ሐንገሪ» ተብሎ ይጠራ ነበር ይባላል፡፡ የቤተሰቦቹ መጠሪያም የሐንገሪ ንጉሳዊ ቤተሰቦች (Hungarians Royal Family) ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ከጻድቅ ዮሐንስ ሞት በኋላ በነገሰው ንጉስ ሥያሜ ያ ቦታ ሐንጋሪ ተብሎ ተጠራ ይባላል፡፡እስከ ዛሬ ድረስም ቦታው ሐንገሪ ተብሎ ሲጠራ የአካባቢውም ሆነ የቀበሌው መጠሪያ «አንገሪ» ይባላል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች መነሻነት የአንገሪ ቤተ-መንግስት ስያሜውምበዚሁ ጸንቶ ቀረ፡፡ ባህላዊ ቤተ-መንግስትነቱንም ይዞ እስካሁን  ሊዘልቅ ችሏል፡፡የአንገሪ ቤተ-መንግስት የሚገኘው በየም ልዩ ወረዳ ውስጥነው፡፡ከልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ከሣጃ ከተማ በ32 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከፎፋ ከተማ ደግሞ 3.2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በግሩምና አንገሪ ቀበሌ ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ ቤተ-መንግስቱም የተለያዩ የሞዋ ጎሳ ነገስታት ተፈራርቀው ይመሩ እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ፡፡ (የየም ህግሥርዓት፤ አንባሳደር ምትኩ ነጋሽ፤ (2005፣34-35)



*ፎቶ ግራፍ  አስራ ሶስትየአንገሪቤተ መንግስት የሞዋ ጎሳ ነገስታት መቀመጫ*

## 5.2 ከየትኞቹ ጎሳዎች በምን መስፈርት ለንግስና ይመረጡ እንደነበር የሚያሳዩ ተረኮች

በየም ብሄረሰብ ውስጥ ከ300 በላይ (ከሶስት መቶ በላይ) ጎሳዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ከነዚህም ጎሳዎች መካከል ወደ ንግሥና የመጡት ከሶስት ጎሳዎች ብቻ እንደሆነ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ እነሱም የጋማ፣ የጌመሎና የሞዋ ጎሳዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጎሳዎች ወደ ንግስና የመጡበት ምክንያት(መስፈርት) የመጀመሪያው በጎሳ አባላት ብዛት ብዙ የህዝብ ቁጥር ያላቸው እንደሆነና፤ ብዙ የህዝብ ቁጥር ያለው ቢያስተዳድር መልካም ነው ተብሎ በብሄረሰቡ ዘንድስለሚታመን ነው፡፡ሌላው መስፈርት ደግሞ ተቀባይነት፣ ተሰሚነት፣

በሳል አስተሳሰብ፣ ንቁነት፣ፈጣንውሳኔ ሰጪነትና አርበኝነት(ጀግንነት) አላቸው ተብሎ ከሚታመን ኅሳ ነው፡፡

በየም ብሄረሰብ ውስጥ ከሚገኙ ኅሳዎች በህዝብ ብዛት ከሌሎቹ ኅሳዎች የበለጠ ቁጥርበቅደም ተከተል ቀዳሚው ጋማ፣ ቀጥሎ ጌመሎና ሶስተኛው ሞዋ በመሆናቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ ለአብነት ተረክ1፣11፣ና19 ያስረዳሉ፡፡በተጨማሪምወንድማገኝ ብዙአየሁና ሌሎች፤(2004ዓ.ምገጽ32-38) ያስረዳሉ፡፡ተረክ 1 ም የቀረበው ይህንኑ የሚገልጽ ነው፡፡

ለንግስናከተመረጠውጎሳወደንግስናየሚመጣውወጣትበቤተሰቡአንድወንድልጅየሆነሲሆንእህቶችቢኖሩትምችግርየለውም፡፡በወቅቱለንግስናተመራጭከሆነውጎሳማለትምከጌመሎምይሁንከጋማምይሁንከሞዋምብቻመስፈርቱአንድወንድልጅመሆንነው፡፡ምክንያቱደግሞብዙወንዶችካሉበትቤተሰብከሆነለስልጣንሽሚያናግጭትእንዳይኖርነው፡፡በተረክ 11ምእንደተገለጸው

*የታሪክአዋቂዎችእንደሚናገሩትየየምብሔረሰብጥንተአመጣጡከየመንበጎን ደርአድርገውእንደመጡየሚነገርሲሆንከየመንየመጣውየጌሜሎጎሳእንደነበርናስርወመንግስቱንምየመሰረቱትሼህድንቡልእንደሆኑናየንግስናመቀመጫቸውሊላቦታእንደነበርይናገራል፡፡ከጎንደርየመጣውየሞዋጎሳሲሆንየሞዋስርወመንግስትመቀመጫውንበአንገሪቤተ-መንግስትቆርቁሮሲመራእንደነበርየሚነገርሲሆን፤የመጀመሪያውየሞዋንጉስባላም (ባለወልድ) ተብለውሲጠሩሁለተኛውደግሞዋዛምቀጣዩገልማሽቀጣዩፋጋብቶ ወዘተእናየመጨረሻውፊትአውራሪገ/መድህንእንደነበሩይናገራሉ፡፡መስፈርታቸውካሉትጎሳዎችመካከልብዙየሕዝብቁጥርያላቸውናተሰሚነትናተጽዕኖፈጣሪነትያላቸውጎሳዎችነበርይመረጡናይመሩየነበረው፡፡አሁንምባለውተጨባጭሁኔታብናይበመሪነትሚናየተሻለተብሎየሚታሰብናበወቅቱ አብዛኛውየተሳካለትመሪየሆነውየሞዋጎሳነውተብሎይነገራል፡፡*[7]የሚከተለው ተረክ 22ም ይህንኑ ሐሳብ የሚያጠናክር ሁኖ ተገኝታል፡፡

*አቶ ተ/ማርያም ገሮ እንደ ገለጹልኝ ለንግስናሲመረጥየነበረውከሞዋ፣ከጋማናከጌመሎጎሳሲሆንመስፈርቱምበማስተዳደርብቃታቸውናበህዝብብዛትጫናማሳደርየሚችልጎሳተመርጦከነገሰበኋላበቤተዘመድከአባትወደልጅበዘርሐረግእየተላለፈስልጣኑይሄድእንደነበርይነገራል፡፡በመጀመሪያከጋማጎሳነግሶለሰባትአመታትከመራበኋላበእርሱየአመራርዘመንዝናብጠፋ፣ሳርእንኳንመብቀልእንቢአለ፣ህዝቡምተጨነቀከዚያ*

---

[7] አስራ ሁለቱ የሞዋ ጎሳ ነገስታት ባላም (ባለወልድ) ፣አዛግኖ፣ ቶኪኖ፣ ስልባብኖ፣ ማውዳንኖ፣ ኮኬኖ፣ ኖዲኖ፣ ዘርማዲኖ፣ ዲጋምኖ፣ አደሎ፣ቦጊቦና ጌራኖ(ፊት አውራሪ ገ/መድህን) ከ12ው መ/ክ/ዘ እስከ 19ኛው መ/ክ/ዘ ብሄረሰቡን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡

*ምህዝቡወጥቶስብሰባተደረጎከጌመሎጎሳነገሰ፤እሱም የተወሰኑ ዘመናት ከመራ በኋላበመጨረሻምየጌመሎንንጉስበማስወገድሞዋየሚባለውጎሳ ቢነግስየተሻለእንደሆነተስማምተውወሰኑናየሞዋጎሳየሆነወጣትፈልገውአነገ ሱ፡፡*

ከላይ ከቀረቡት ተረኮች እንደምንረዳው ለንግስና የሚመረጠው ጎሳ በህዝብ ቁጥር ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያለውበማስተዳደርችሎታ፣በጀግንነት፣ በተጽዕኖ ፈጣሪነትና የመሳሰሉትን መስፈርቶች በቅድሚያ የሚያሟላው ጎሳ ከተመረጠ በኋላ ፣ቀጣዩ ከዚሁ ጎሳ የሚሾመው ወጣት ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች ያሉ ሲሆ አነሱም ለንግስና የሚታጨው ወጣት ያላገባና ድንግል መሆን፣ለቤተሰቡ አንድ ወንድ ልጅ (የመጨረሻ ልጅ) መሆን እንደነበር ነው፡፡የማይገኝ ከሆነ ደግሞ ከንጉሱ የወንድምልጆች መካከል መስፈርቱን የሚያሟላ ከተገኘ ይነግሳል፡፡እንጂ ንግስናው ለሌላ ጎሳም ይሁን ከንጉሱ በተሰብ ውጭ ተላልፎ አይሰጥም፡፡

ከእነዚህ መረጃዎች እንዳየነውመስፈርቶቹን የሚያሟላ ጎሳ ለምን ይመረጥ እንደነበር መረጃ ሰጪዎቹ ሲያስረዱ በብሄረሰቡ ከ300 በላይ ጎሳዎች በመኖራቸው እነዚህን በሙሉ በብልሃትና በጥበብ አዋህዶ ለመምራት የአመራር ጥበብ ያስፈልጋል፡፡በተጨማሪም የህዝቡን ደህንነት ለማስጠበቅም ጀግንነት ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ባሻገርም ብዙ የህዘብ ቁጥር ካለው ጎሳ መመረጡየብዙሃንን ፍላጎት ለማሟላት አንደሆነና በተቃራኒው ደግሞ የስልጣን ዘላቂነትንም ለማስቀጠል ነው፤ይህም ሲባል ብዙ አባላት ያሉት ጎሳ ስልጣን መያዝ በጥቂቶቹ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የማህበረሰቡን የውስጥ ጥንካሬ እንዳይናጋ ይረዳል፡፡ ግጭትን ያሶግዳል፣የማህበረሰቡን አንድነት በማስቀጠል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

## 5.3 የንግስና አሰጣጡን ባህላዊ ስነ-ስርዓቶች የሚያሳዩ

መረጃ አቀባዬ አቶ ንጉሴ ዘበን እንደገለጹትበአንገሪ ቤተ-መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገሥታት ይነግሱ የነበሩት የሞዋ ጎሳ አባላት ሲሆኑ ከ12ኛው

መ/ቶ/ክ/ዘመን እስከ 19ኛው መ/ቶ/ክ/ዘመን ድረስ የየምን ህዝብ አስተዳድረዋል፡፡ ወደ ንግሥና ለመምጣት ባህላዊ ስነ-ስርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡እነዚህም በመጀመሪያ ለንግሥና የታጨው ወጣት የመጀመሪያውን መስፈርት ማለትም ድንግልናውን የጠበቀ መሆን ሲሆን ቀጣዩ ያ ወጣት ታዝሎ ወይም ሁለት ሰዎች «የሰከኩ ጎሳና የመለቆ» ጎሳ አባላት የሆኑ ሰዎች ግራና ቀኝ ክንዱን በመያዝ እንሰት በሚፍቁ ሰዎች ፊት ለፊት ያልፋሉ፡፡ተረክ 15 እንደሚያስረደው ከዚያም ሴቶቹ ያዩትና ከነሱም አንዷቱ «ይሄ ንጉስ ይመስላል» ብላ ከተናገረች ከዚያን ጀምሮ «ንጉስ ነህ» ተብሎ ስያሜ ይሰጠውና ከዚያም እነዚያ ሰዎች በየተራ እያዘሉ ወደ ጫካ ይወስዱትና ለ8ት ቀናት እዚያ እንዲያድ ይደረጋል፤በዚያ ጫካ ውስጥም ነብር፣ዘንዶ፣እባብና የመሳሰሉ አውሬዎች ሳይተናኮሉት ተሻሽተውት(ታክከውት) ከሄዱ የመጀመሪያውን መስፈርት አልፏል ተብሎ ወደ ቀጣዩ ባህላዊ ስነ ሥርዓት ይሄዳል፤ካላለፈ ማለትም የዱር እንስሳቱ ከተተናኮሉት ግን የዛር መንፈሱ አልተቀበለውም ይባልና አስተሰሮቹ(የንጉሱ አማካሪዎች) ሌላ ወጣት ማለትም የዚያ ወጣት ወንድም ካለ እሱን፤ ከሌለ የንጉሱ የወንድም ልጆች ካሉ መስፈርቱን የሚያሟላ ተፈልጎ የመጀመሪያውን መስፈረት ሲያሟላ ወደቀጣዩ ስርዓት ያልፋል፡፡

ቀጣዩ በዛር የመቀባት ሥርዓት ይህም የሚፈጸመው ሥርዓተ ንግስናውን በሚመሩት ማግ «ሶኣላንጎ»በሚባሉ ሰዎች አማካኝነት ወደ ጊቤ ወንዝ ይወሰድና «ምማ(ሆራ)»ፍል ውሃ እንዲታጠብ ይደረጋል፤ይህ የሚደረግበት ምክንያት ውሃው የተቀደሰ ነው ተብሎ ስለሚታመንና እጩው ንጉሥ በዚያ ፍል ውሃ እንዲታጠብ የሚደረግበት ምክንያት የቀድሞ ህይወቱን ትቶ አዲስና የተቀደሰ ህይወት ይጀምራል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ከዚያም ቀጣዩ ሥርዓት በጊቤ ዳር የእድል ትንበያ ይደረጋል፣ ትንበያውም የሚደረገው ለዚሁ ተብለው የተዘጋጁ 12 የድንጋይ መቀመጫዎች ያሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው በንጉሱ የአገዛዝ ዘመን ለሚፈጠሩ ክስተቶች ለምሳሌ ረሃብ፣ጦርነት፣ድርቅ፣በሽታ፣ጥጋብ፣ስደት ወ.ዘ.ተ ወካይ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ የእያንዳዳቸውን ውክልና የሚያውቁ «ማግ» የሚባሉት

መስዕዋት አቅራቢዎቹና ሌሎች የንግስና አስፈጻሚዎችና «አስተሰሮች»ብቻ ናቸው፡፡ የድንጋዮቹን ውክልና የሚያውቁት ሲሆን ያ ንጉስም አያውቅም፣ እነዚህም ንጉሱን ከመቀመጫዎቹ አንዱ ላይ እንዲቀመጥ ያዙትና ይቀመጣል፣ ከዚያም በጎ ውክልና ያለው ላይ ከተቀመጠ የዚያ ንጉሥ የንግስና ዘመን መልካም ነው ይባላል፡፡መጥፎ ውክልና ለምሳሌ የረሃብ ወካይ ላይ ቢቀመጥ በንግሥና ዘመኑ ረሃብ ይከሰታል ተብሎ ይታመናል፡፡ይሁን እንጂ ንጉሱን ከንግስና የሚያግደው ነገር አይኖርም፡፡ ለጊዜው ይነግስና ድርጊቶቹ ሲከሰቱ በጊዜው እንዲለቅ ይደረግና ሌላ ይሾማል፡፡(የየም ብሄረሰብ ታሪክ፣ ወንወድማገኝ ብዙአየሁና ሌሎች፣2005፣ገጽ42-43) ተረክ14 ይህንኑ ሐሳብያረጋግጣል፡፡

*በየም ብሔረሰብ ነገስታት ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የነበረው ንጉስ በሞት ሲለይ የንጉሱን ወንድ ልጆች ወይም ከሌላቸው የቅርብ ዘመድ ወንድ ልጆች ተሰብስበው ወደ በርሃ ይወሰዱና ባንድ ቦታ ያስቀምጧቸዋል፣ ብዙ ከብትም በዓይነት ይታረዳል፡፡ ህዝብ ይሰበሰብና ከልጆቹ 2 ሺህ ክንድ የሚሆን ርቆ ቆሞ ከልቡ እየጮኸ በልዩ ልዩ ዜማ እየዘፈነ ይጨፍራል፡፡ ጩኸቱ ዘፈኑንና ማቅራራቱ ደምቆ በተሰማ ጊዜ ዘንዶው ከጎሬው መዘዝ ብሎ ይወጣና ከታረደው ከብት ከደሙ ከላሰ (ከቀመሰ) በኋላ በልጆቹ ዙሪያ ይዞርና አንዱ ላይ ይጠመጠማል፡፡ የቀሩት ወንድሞቹ ተነስተው በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ፡፡ ከሩቅ ያለው ሕዝብም ማለትም ዘፋኙና ጨፋሪውም ሕዝብ እየሮጡ ይቀርቡና እየተደፉ ይሰግዳሉ፡፡ ከዚያም በኋላ ስልጣን ቀቢ ተብሎ የሚታመነው ዘንዶ ወደ ጎሬው ተመልሶ ይገባል፡፡ ይህ የተቀባ ንጉስ ይነሳና ህዝቡም ይሰግድለታል፡፡ የቀሩት ወንድሞቹም ይሰግዱለታል ግን ከዚያ ቀን ጀምሮ እንደ ሌሎቹ ህዝቦች ናቸው እንጂ ከንጉስ ዘር ቁጥር የላቸውም ይህም ሲባል ወንድሞቹ እንደሌሎች የብሄረሰቡ አባላት ተቆጥረው ለንጉሱ ወንድማቸው ይገዙለታል ማለት ነው፡፡ ይህ የማንገሱ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ እንደ ግብር ይቆጠርና ያ የታረደው ከብት ሥጋ*

*ይበላል፡፡ ተበልቶ የተረፈ ሥጋ ካለ ወደ ቤት መጥቶ አይገባም እዚያው ጥለውት ነው የሚመጡት ይህ ባህላዊ ስርዓት ነው፣ ከዚያው ንጉሱን አጅበው ወደ ቤተ-መንግስቱ ያገቡታል፡፡*

ቀጣዩ መረጃ የዓዞ አምልኮ አጀማመር በየም ብሄረሰብ እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፤የዓዞ አምልኮ ስርዓት መጀመር መንስኤ የሆኑት የተለያዩ አበይት ምክንያቶች ናቸው፡፡ የየም ህዝብ የእናሪያ ነገድ ነው፡፡ የእናሪያ ህዝብ በ1270 ዓ.ም ክርስትና ሃይማኖት ተቀብሎ ብዙ አቢያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት መሪዎች ነበሩት፡፡ በ1515 ዓ.ም በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜ በወቅቱ የነበሩት ቤተመቅደሶች፣ቅዱሳት መጻህፍት እንዳልነበሩ ሆነዋል፣ተዘርፈዋል፣ተቃጥለዋል፣የሃይማኖት መሪዎችም እየታደኑ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የየም ብሔረሰብ አረማዊ (ሃይማኖት አልባ) በመሆን በዓዞ፣ በዛፍ፣ በተራራ፣ በወንዝ፣ በደን፣ በፀሐይና በጨረቃ ማምለክ ጀመረ፡፡ የየም ብሔረሰብ በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በግልና በቡድን የጊቤን ወንዝ ተሻግሮ በመምጣት እንደሰፈረ ይነገራል፡፡

በመሆኑም በአንድ ወቅት ባላም፣ዋዛም፣ ፋጋተስቶና ሶኦላ የተባሉ ዘሮች አብረው የጊቤን ወንዝ ሲሻገሩ የሶኦላ ዘር/ጎሳ/አባል ደክሞት ስለነበር የጊቤ ወንዝ ወሰደውና በውሃ ውስጥ በነበሩ ዓዞዎች ወይም ዘንዶዎች ይበላአይበላ ሳይታወቅ ዱካው ስለጠፋ ብቻ የቀሩት ሰዎች የእህል መስዕዋት ወደ ወንዙ ቢጥሉምየሚቀበላቸው ጠፋ፡፡ከዚያ በኋላ የከብት ስጋ እንስጥናቢቀበለን በሚል ሲሞክሩዓዞው ወጥቶ ያን ስጋ በመብላቱ (በመቀበሉ) ለሶኦላ፣ ለዲቻንጉ፣ለገበና፣ ለገመሎ፣ለካንሽሮ፣ለከሞሶ....ጎሳዎች የአምልኮ ጣዖት ሆነ ይባላል፡፡

ሌላው ምክንያትባለወልድ ከነጓደኞቻቸው ከጎንደር ሲመጡ እንብርታቸዉንና እንብርታቸው የተቆረጠበትን ምላጭ ኦና ከሚባል እንጨት በተሰራ ሳጥን ውስጥ ጨምረው ያቆዩትን አሸክመው የጊቤን ወንዝ ሲሻገሩ በእንብርቱ በውስጥ ትል ይፈጠርና ከውሃ ውስጥ ይወድቃል፡፡ ባለወልድም ወንድሜ በውሃ ውስጥ ስለወደቀ በየወሩና በየዓመቱ የከብት ግብር መሰጠት አለበት አሉ ይባላል፡፡ ስለዚህምበአካባቢው አፈ ታሪካዊ አመለካከት ባላምና ዓዞ

ወንድማቾች ናቸው ይባላል፡፡ያ የወደቀው ትል ዓዞ ሆነ ብሎ በማመን፤ በሳጥኑ ውስጥ የነበረውምላጭም ናቲሲ በሚባል ቦታ ላይ ተቀብሯል ይባላል፡፡ ባለወልድ ከመምጣቱ በፊት የዓዞ አምልኮ በብሔረሰቡ ዘንድ አልነበረም ይባላል፡፡

ሌላው ምክንያት የሚባለውለዓዞ አምልኮ ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በብሔረሰቡ ዘንድ አደን የተለመደ በመሆኑበህብረት ወጥተው በማደን ይመለሱ ነበር፡፡ በህዝቡ ባህላዊ የአደን ስርዓት መሰረት መጀመሪያ አልሞ የወጋ ነቀላ፤ ሁለተኛ የወጋ ሽንጥ፤ ተከታትሎ የደረሰ እንደየ አመጣጡ ስጋ ስለሚወስዱ ለዚሁ በሚደረገውየውጊያ እሽቅድድም ላይ እኔ ነኝ መጀመሪያ የምወጋው በሚሉ በሁለት ሰዎች መካከል በሚፈጠረው አለመስማማት የአዳኞች ክስ ሰሚ ዳኛ ዘንድ ቀርበው መተማመን ካልቻሉ የተወጋውን የእንስሳት ስጋ ሁለቱ ባለጉዳዮች የየራሳቸውን የአምልኮ ጣዖት እየጠሩ ዓዞ ወዳለበት ውሃ ውስጥ ተራ በተራ ይጥላሉ፡፡ ስጋውበውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ከሄደ ዓዞው ተቀብሎ አልበላምና የመጀመሪያው ወጊ አይደለም፤ ስጋው ሲወረወር ውሃ ውስጥ የጠለቀ ከሆነ ዓዞውበውሃ ውስጥ ሆኖ ተቀብሎታልና ክሱን በመርታት የኋላ ነቀላ ስጋ ይወስዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አዳኞች የጊቤን ወንዝ ተሻግረው ስለሚያድኑ ያገኙትን የእንስሳት ስጋ ልቡን፣ ኩላሊቱን ወ.ዘ.ተ በማውጣት ለዓዞ ከምስጋና ጋር ይሰጣሉ፡፡ ይህም የሚያደርጉት ምክንያት በረሃውን እያቋረጡ ሲያድኑ ከመጥፎ አደጋ ሁሉ ጠብቆን ብዙ ስጋ እንድናገኝ የረዳን እሱ ነው ይላሉ፡፡ በተለይ ከጊቤ ማዶ የሚገኙ የጉራጌና የሃዲያ ብሔረሰቦች የጊቤን ወንዝተሻግረውወደ የም ምድር እየተመላለሱ ስለሚነግዱ በጓደኛሞች መካከል የተካካዱና መሃላን ያፈረሱ ቂመኞች አብረው የጊቤን ወንዝ ለመሻገር ከዳርቻው ሲደርሱ ዓዞውበውሃ ላይ እየተንሳፈፈ መሻገር ስለሚከለክላቸው የቃል ኪዳን ጓደኛሞች በአንድነት ተሰብስበው ይህ ጥፋት ከማን እንደሆነ ተጠይቆ ጥፋተኛው ጥፋቱን አምኖ የበደለውን ጓደኛውን ክሶ ወይም ለመካስ ቃል ከገባ በኋላ እያዩት ዓዞውከአካባቢው እየተንሳፈፈ ይሄድላቸውና መሻገር ይጀምራሉ፡፡ነገር ግን ጥፋተኛው ጥፋቱን ባለማመን

በውሃ ውስጥ ሊሻገር ከገባ ዓዞው እግሩን ወይም እጁን ሰብሮ ይጥለዋል፡፡ ይህ ሰው ከውሃ ወጥቶ ሰፈሩ ደርሶ ጥፋቱን ካመነ ይድናል፡፡ ከባለጋራውም ጋር ይቅርታ ተጠያይቆ የበደለውንም ክሶ ከታረቀበኋላወንዙን እንደገና ይሻገራል፡፡ቂም ያለባቸው ሰዎች ቅራኔያቸውን ሳይፈቱ አምነው በወንዙ ውስጥ ገብተው አይሻገሩም፡፡የአካባቢው ሰዎችም እነዚህን ድርጊቶች በማየት እውነተኛ ፈራጅ አምላክ በውሃ ውስጥ እንዳለ በማመን በማንኛውም ማህበራዊ ኑሮአቸዉ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የተባሉትን ጥጃ ወስደው መስዕዋት በማቅረብ በማስፈታት አምልኮውን እንደጀመሩ ይነገራል፡፡ወርቂ ካብቱ፡፡ ያልታተመ፡፡(ምንጭ የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/የመ/ኮ/ጽ/ቤት፡፡)

መረጃአቀባዬመምህርአዲሱ ሙሳ በተረክ14 እንደገለጹት

*የሥርዓቱአስፈጻሚዎችአዲሱንንጉሥበዛርመንፈስቅባቅድስናቀብተውያነግሱታል፤ይህምየሚከናወነውእነዚህሰዎችአዲሱንንጉስከሌሎችልጆችጋርቀላቅለውያስቀምጡታልከዚምጊደርይታረዳል፡፡ከነዚህልጆች 200 ክንድርቀውብዙሰዎችባህላዊዘፈንእየዘፈኑይጨፍራሉበዚህጊዜዘንዶከጉድጓዱወጥቶበመምጣትከታረደውጊደርደምይልስናመጥቶከልጆቹመካከልለይቶበዚያእጨንጉሥላይተጠምጥሞወርዶይሄዳል፤ይህነውበዛርመቀባትየሚባለውበዚህጊዜየተሰበሰቡትሁሉይሰግዱለታል፣ወንድሞችእንኳንቢኖሩትከዚያንቀንጀምሮእንደሌሎችሰዎችነውየሚቆጠሩት፡፡በዚህምየንግስናሥርዓቱይፈጸምናየዚያየታረደውከብትሥጋይበላል ተበልቶየተረፈካለምእዚያውይጣላልአንጂወደቤትአይወሰድም፡፡በመጨረሻምሁሉምንጉሱንእጅበውትወደቤተ-መንግስትያስገቡታልከዚያምበአስተሰሮችምርጫየተዘጋጀችቆንጆናባለሙያሴትአምጥተውየጋብቻቃልኪዳንአስገብተውያጋቡታል፡፡ኪዚያምየንግሥናስራውንይጀምራል፤ዕድሉመጥፎሆኖለህዝቡየማይመችከሆነየተወሰነአመትካስተዳደረበኋላእንዲለቅይደረጋል፡፡*

እንግዲህ ከዚህ መረጃዎች የምንገነዘበው የየም ብሄረሰብ የራሱ የሆነ ባህላዊ የንግስና ስርዓት እንደነበረውና ይህምንግስና የባህላዊ አምልኮ ሥርዓትን ተከትሎ የሚፈጸምና ያም ንግስና የሚጸናው በዛር መንፈስ በመቀባት

እንደሆነ ያሳያል፡፡ንጉሱም የንግስና ዘመኑ የተሳካ እንዲሆንና ሃገሩ የሰላም፣የጥጋብ፣የበረከትና የደስታ እንዲሆን በማለት ወደጊቤ ወንዝ ይወርድና ለዓዞ /የዛር መንፈስ ተሸካሚ/ ጊደር ወይም ወይፈን ይሰዋል፡፡ የመስዕዋት አሰጣጥ ስነ ስርዓቱም በመጀመሪያ የጊደሯ ወይም የወይፈኑን ሰኮና በጦር ይወጋል ከዚያም ከጬኧች/ከጬኸ/ ዓዞው መስዕዋቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ነው ተብሎ ይሰዋል ካልሆነ ይቀራል፡፡ፈቃደኛ ሆኖ ከብቱ ከታረደም ስጋው እኩል ቦታ ይካፈላል፡፡ ለዓዞውና ለንጉሱ እኩል ካልተካፈለ ዓዞው ስጋው ሲጣልለት አይበላውም፡፡ ስለዚህ እኩል መካፈል አለበት፡፡ዓዞው መስዕዋቱን ከተቀበለ ሃገሩ ሰላም፣ጥጋብ፣ጤና፣በረከት ይሆናል የንጉሱም የንግስና ዘመን የተሳካ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ባሕላዊ መስፈርቶች ያላሟላ ንጉስ መሆንና ህዝቡን ማስተዳደር አይችልም፡፡ቀጣዮቹን ተረኮች ተረክ15ና31 እነዚህን ሐሳቦች ያስረዳሉ፡፡




ፎቶ ግራፍ አስራ አራትለዓዞ መስዕዋት ይቀርብበት የነበረ ገበቴ



**ፎቶ ግራፍ አስራ አምስት የባህላዊ ንግስናው ይፈጸምበት የነበረው የጊቤ ወንዝ ዳር**

*በተረክ15እንደቀረበው ንጉሱ ከሚመረጥ በጎሳለንግስናየታጨውንሰውአዝለውለንግስናእንዲቀባየሚወስዱትሁለት ጎሳዎችነበሩይባላል፡፡አንዱ«የመለቆ»ጎሳሲሆንሌላውደግሞ«የሰከኩ»ጎሳ ናቸው፡፡እነዚህሰዎችለንግስናየተመረጠውንወጣትየግራናየቀኝክንዱንበ መያዝሲሄዱእንስትከሚፍቁሴቶችመካከልአንዷ«ይህንጉስይመስላል»ብ ላከተናገረችከዚያንቀንጀምሮ«ንጉስነህተብሎ»ስያሜይሰጠውናከዚያም*

*ታዝሎይሂድናውጭጫካውስጥለ8ቀናትያድራል;
ጠባቂዎቹምነብር፣እባብናየመሳሰሉትአራዊትሲጠበቁትከቆየበኋላመልሰ
ውወደቤተመንግስትያመጡትናእንዲቀመጥይደረጋል፡፡ከዚያበኋላበይፋ
ንጉስመሆኑይታወጅናማስተዳደርይጀምራል፡፡*

በአንገሪ ቤተ መንግስት ለንግስና የሚመ[8] ረጠው «ከሞዋ»ጎሳ ነው፡፡ምክንያቱም «ከባላም»የመጣ ዘር ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፣ባላም ማለት የፈጣሪ ዘር ለማለት ነው ብለው ያምኑ ነበር ይላሉ፡፡ለንግስና የሚመረጠው የሞዋ ጎሳ ሆኖ ሌሎች ጎሳዎች እንደ ድጋፍ ሰጪ በመሆን ያገለግላሉ፣በየም ብሄረሰብ የሞዋ ጎሳ የ«ባላም» ዘር ነው ብለው ስለሚያምኑ አሁንም ድረስ ለጎሳው ልዩ አክብሮት ይሰጣሉ፡፡አሁንም ቢሆን በተለያዩ ባህላዊ ተቋማት ማለትም በመንደር መሪነት፣ በሃገር ሽምግልና ወዘተ. የሚመርጡት ከሞዋ ጎሳ አባላትን ነው፡፡ተረክ 31.ም ይህንን የሚያረጋግጥ ሃሳብ ይዟል፡፡

*ሰውሰዎችበየተራእያዘሉትከርዋቀበሌ (ኤንኪ)
ወደሚባልቦታይዘውትይሄዳሉ፡፡እዛምንጉስቀብቶየሚያነግስታዋቂሰውነ
በር፡፡ከዚያምሰዎችለንጉሱከብትስጠውይሉታል፡፡ያምሰውይቆጣና«ጡሩ
ንባእያስነፋህየመጣኸውንጉስነኝብለህአይደልከብትእኔንልትጠይቅነው?
»ብሎይቆጣል፡፡ከዚያምሰዎችእንዲረጋጋያደርጉትናከራሱከብትአውጥ
ቶያርድናንጉሱንለንግስናይቀባል፡፡ከዚያምንጉሱከተቀባበኋላወደቤተ-
መንግስቱመልሰውይወስዱትናአዋጅተነግሮህዝቡንጉስመንገሱንእንዲያ
ወቅይደረጋል፡፡*

---

[8] ባላም ማለት የፈጣሪ ዘር ማለት ሲሆን(ለሞዋ ጎሳ) የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ማግ ማለት ካህን ማለት ሲሆን በዚያን ዘመን ለዓዞ መስዕዋት የሚያቀርቡት ሲሆኑ ከ3ት ጎሳዎች ብቻ የሚመረጡ ናቸው፡፡እነሱም « ከየሱ ጎሳ፣ ከሀማ ጎሳና ከሶኣላ »ጎሳ ናቸው፡፡መስዕዋቱ የሚቀርብ እንደየ ጎሳው ድንጋጌ ነው፡፡ለምሳሌ ኮርቦ የበግ ጠቦት፣ሞዋ ላም፣ጊደር፣ወይፈን፣ሲሆን መስዕዋቱ የሚቀርበው ንጉስ ሲሾም ብቻ ሳይሆን ሰዎች በደል ሲፈጽሙ ለመካሻም ይሰዋል(መስዕዋት) ይቀርባል፡፡

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች እንደምንረዳው የአንገሪ ቤተ መንግስትን ባህላዊ ንግስና የሚይዙት የሞዋ ጎሳዎች ብቻ እንደሆኑና፣ ከእነሱም የንጉሱ ልጅ ወይም የቅርብ ዘመድ( የወንድም ልጅ) እነደሆነ፣ ብሎም ያላገባና ድንግል (ሴት ያላወቀ) የሆነ ሆኖመገኘት ፣ በተጨማሪም በነብር ወይም በዘንዶ የተመረጠና በዛር መንፈስ የተቀባ መሆን ያለው ማህበረ ባህላዊ ፈይዳ ለተመራጩ ጎሳና ለንጉሱ ቤተሰቦች የንግስና ስልጣናቸውን የማስቀጠያ መሳሪያ ሲሆን ከአምልኮ ጋር የተያያዘ መሆኑ ሌሎች ጎሳዎችን የዛር መንፈሱ ባለመምረጡ ምክንያት ተነስተው ንጉስልሁን ቢሉ የማይቻል መሆኑ፤ ይህ ደግሞ ለነገስታቱ ቤተሰቦች በትረ ንግስናውን ማስጠበቂያ በመሆን ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ሌላው ህዝብ ደግሞ ነገስታቱን ከፈጣሪ እንደተሾሙላቸው በመቁጠር ያለምንም ቅራኔና ተቃውሞ መገዛቱ ማህበረሰቡ ምንም እንኳን ከ300 በላይ ጎሳዎች ቢኖሩትም በሰላምና በመተሳሰብ ማህበራዊ (ውስጣዊ አንድነቱን )እና ባህላዊ እሴቶቹን ጠብቆ እንዲዘልቅ ረድቶታል፡፡በተረክ 40 የቀረበው የለቅሶ ቃል ግጥምም ይህንን ሃሳብ የሚያጠናክር ሲሆን ህዝቡ ምን ያህል ለንጉሡ ፍቅርና አክብሮት እንደ ነበራቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ሕዝቡነገስታቱንከፈጣሪየተሰጡናቸው፡፡በማለትአምነውተቀብለውበቅንነትይታ ዘዙላቸዋል፤ይወዷቸዋል፡፡[9]በዚህምምክንያትንጉስሲሞትበቃልግጥምእያወዳደሱ ያለቅሱነበር፡፡

*ህዝቡንጉስሲሞት ሙሾእያወረዱእንዲህይላሉ፡-*

በየምሳ ቋንቋ ትርጉምበአማርኛ

---

[9] « መለቆና»እና« ሰከኩ» የጎሳ ስያሜዎች ሲሆኑ በጊዜው ንጉሱን ለማስነገስ የሚወስዱት ሰዎች ናቸው፡፡«ኤንኪ» የቦታ ስያሜ ሲሆን ነገስታቱ ስርዓተ ንግስናቸውን የሚፈጽሙበት ቦታ ነው፡፡
የዛር መንፈስ የሚባለው በሰይጣን መንፈስ የሚመለክ አምልኮ ነው፡፡

*አምኖቴአምኖቴኬምናሴ..........ንጉሳችንንጉሳችንአይናችን*

*አምኖቴአምኖቴአፋይናሴ ..........ንጉሳችን ንጉሳችንውሎአዳራችን*

*አምኖቴአምኔበዝኒ........ንጉሳችንጀግናችንእያሉለንጉሳቸውያላቸ ውንክበሬታናፍቅርታዛዥነታቸውንይገልፃሉ፡፡*

በተረክ 34እንደምንመለከተውም ህዝቡ የመጀመሪያው የሞዋ ንጉስ የነበሩት ባላም የነገሱበት ቀን (ግንቦት1) በህዝቡ ዘንድ ይከበር ነበር፡፡ደግሞም ይህበዓል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስበህዝቡ ዘንድ እንደአምልኮት በዓል በመቁጠር ያንን ዕለትያከብራሉ፡፡በዓሉን ማክበርንም እንደ በረከት ማግኛ አድርገውም ይቆጥሩት እንደነበር ያስረዳል፡፡

*የመጀመሪያውየሞዋኀሳንጉስታቶባላም (ንጉስባለወልድ)*

*የነገሱትበግንቦትአንድቀንነውይባላል፡፡ሕዝቡምእስከአሁንድረስያንን ቀንበጣምያከብራሉ፡፡የሚያከብሩትምበአካባቢያቸውትልቅዛፍስርከብ ትታርዶ፣የቆጮድፎተጋግሮናየእንሰትስር (አምቾ) ተቀቅሎይከበራል፡፡የሚከበርበትምክንያትምየንጉስባላምፌጣሪዝናብያ መጣል፣በረከትሰላምያመጣልበሽታከሀገራችንይርቃልተብሎይታመና ል፡፡በተጨማሪምበዚያንቀንኅተራቸውን፣ቀሮቻቸውንወ.ዘ.ተክፍትያሳ ድራሉ፡፡ይህንንምየሚያደርጉት"የንጉስባላም"ፌጣሪበረከትይሞላልብለ ውስለሚያምኑነው፡፡በአንዳንድየወረዳዋአካባቢዎችይህባህላዊስርዓትእ ስከአሁንምይደረጋልሲሉመረጃሰጪዎቹነግረውኛል፡፡*

## 5.4 በቤተ-መንግስቱአመሰራረትና በነገስታቱ አመራር ዙሪያ የተነገሩ አፈ ታሪኮች

በተረክ 41 አቶ ሳህሌ ዘበን እንደ ገለጹትና የየም ሕግ ስርዓት(2005፣34-35) እንደሚያስረዳው ስለአንገሪ ቤተ-መንግስት አመሰራረትንና ስያሜ እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው የጻድቁ ንጉሥ ዮሐንስ ወደ የም ምድር መምጣት

እንደሆነ በአፈ-ታሪክ ይነገራል፤ይኸውም በጥንት ዘመን በጎንደር ይኖሩ የነበሩ ጻድቁ ንጉስ ዮሐንስ ፣ባለቤታቸው ንግስቲቱና የንስሃ አባታቸው በአንድነት ሆነው የተጠበሰ ዓሣ እየበሉ እያለ ንጉሱ እንዲህ ይላሉ «ከእኛ መሃል እውነት የሚናገር ሰው ካለ ይህ የተጠበሰ ዓሳ ነፍስ ይዘራል፤ከዚያም ነፍስ አባታቸው «እኔ ንግስቲቱን በጣም እወዳታለሁ፣የአበ ነፍስ አባትነት ክብሩ ቀርቶብኝ እሳቸውን አግብቼ በኖርኩ ይላሉ»፤ «ንግስቲቱም የንግስትነት ክብሩ ቀርቶብኝ የሚወደኝ እረኛም ባለጌም ቢሆን አግብቼው ደስ ብሎኝ በኖርኩ ትላለች፤» በመጨረሻም ንጉሱ «እኔም የዚህ ዓለም ዕውቀት፣ክብር፣ተድላና ደስታው ቀርቶብኝ አስፈሪ የዱር አውሬዎች ወዳሉበት የአራዊት ገዳም ገብቼ በኖርኩ» ሲሉ ያየተጠበሰ ዓሳ ነፍስ ዘርቶ መንቀሳቀስ ይጀምራል ንጉሡም አንስተው ውሃ በያዘ ገበቴ አድርገው ወደ ጣና ባህር ውስጥ ጣሉት ይባላል፡፡

በየም ብሄረሰብ ዓሳና ዓዞ አይበላም ምክንያቱም የተቀደሱ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው ይላሉ፡፡ይህ ማለት በብሄረሰቡ ዘንድ በወቅቱ በዓዞ ያመልኩ ስለነበርና ዓሳም የዚያው ዘር ስለሆነና ለጻድቁ ንጉስም ካላቸው ክብር የተነሳ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት ተብሎ ከተነገረው አንጻር እንዳልሆነ መረጃ አቀባዮች ይገለጻሉ፡፡

ከዚያም ንጉሱ ሁሉን ትተው ወደ አራዊት መኖሪያ ወደ አንገሪ(የአሁኑ የየም ምድር) መጡና በዚያ ሲኖሩ እሳቸውን ለመጠየቅ የቅርብ ዘመዶቻቸው ይመጡ እንደነበርና በወቅቱ የንጉሱ ምክትል የነበረ ጊዮርጊስ ሐንገሪ የተባለ ሰው እንደነበርና እርሱም ከጻድቁ ንጉስ ሞት በኋላ በነገሰው በንጉሥ ሐንገሪ ሥም ቦታውም እንደተሰየመ ይነገራል፡፡ይህ አፈ-ታሪክ ስለ ጻድቁ ንጉሥ ዮሐንስ ወደ የም ምድር አመጣጥና ስለ አንገሪ ቤተ መንግስት አመሰራረት መረጃ የሚሰጥና በማህበረሰቡም ዘንድ በዚህ ምክንያት ለቦታው(ለአንገሪ) ልዩ አክብሮትና ለነገስታቱም ልዩ ከበሬታ እንዲሰጡ ምክንያታቸው ይህ አፈታሪክ መነሻ እንደሆናቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨምሪም ይህ አፈ-ታሪክ በየም ብሄረሰብ የሞዋ ጎሳ አመጣጥን ጭምር የሚያስረዳ በመሆኑ

ይህን አፈ-ታሪክ መሰረት በማደረግ የሞዋ ጎሳ ከእሥራኤል ተነስቶ በጎንደር አድርጎ ወደ አሁኑ የየም ምድር እንደመጣ በማስረጃነት ይገለገሉበታል፡፡

በተረክ 41 አቶ በረከት ይገዙ እንደተገለጹትበነገስታቱ ዘመን ጥፋተኛ ሰው የሚቀጣበት «ዛንሶ»የሚባል የመገፍተሪያ ገደል ነበረ ወንጀል የፈጸመ ሰው ፣የንጉሱን ትዕዛዝ የተላለፈ ሰው ወደ ገደል ተገፍትሮ እንዲሞት ይደረግ ነበር፤በሞዋ ስርወ መንግስት ዘጠነኛው ይሁን አስረኛው ንጉስ ዘመን ንጉሱ አባጂጋዎችን(የየጎሳ መሪዎችን) ስብሰባ ይጠራሉ ይባላል በዚያን ጊዜ አንድ ‹‹ኮርቦ›› የሚባል ጎሳ መሪ ስብሰባውን በመቅረቱ ንጉሱ ያሰው በወታደሮች ተይዞ እንዲመጣ ያዙና ያስመጡታል፤ንጉሱም እንዲህ ሲሉ ይጠይቁታል «ለምንድነው ትዛዜን ያላከበርከው ለመሆኑ እኔ ነኝ ወይስ እግዚአብሄር ነው የሚበልጥው ይሉታል» ሰውዬውም« ከርሶማ እግዚአብሄር ነው የሚበልጠው» ሲል

ይመልስላቸዋል፡፡ከዚያምንጉሱበቁጣይሞሉናወስደውገፍትረውእንዲገሉትለወታደሮቹትዕዛዝያስተላልፋሉ፤ወታደሮቹምያንሰውወደ«ዛንሶ»ወስደውሊገፈትሩትሲሉ«ቆይአንድነገርልለምናችሁእባካችሁቶሎእንድሞትወደኋላሄዳችሁተንደርድራችሁገፍትሩኝ»ይላቸውናወታደሮቹምከኋላተንደርድረውሲመጡሰውዬውጎንበስብሎበደረቱለጥሲልወታደሮቹወደገደልተወርውረውገቡናወድቀውሞቱ፤ያንጊዜያሰውወደንጉሱሄዶ«የእርሶወታደሮችሞቱእኔግንተረፍኩብሎ»ይነግራቸዋል፡፡ንጉሱምእጅግበጣምያዝኑናከዚያጊዜጀምሮየዛንሶቅጣት(ወደገደልተገፍትሮመሞት)የመገደልቅጣትበዚህምክንያትቀረይባላል፡፡



ፎቶ ግራፍ 16 የዛንሶ የወንጀለኛ መገፍተሪያ ገደል ይህ ነው

ሌላው[10]በዚያን ዘመን ነገስታቱና ህዝቡ የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው (ነገስታቱ የህዝቡን ብሶት ያዳምጡ) ነበር ይባላል በንጉሱ ቤት አገልጋይ የሆነች ሴት ነበረች ይባላል ከዕለታት አንድ ቀን ንጉሱ ቤት ውስጥ የሌሉ መስሏት እንዲህ ብላ ትናገራለች «እኚህን ንጉስ በነቀላቸው» ትላለች በዚህ ጊዜ ንጉሱ ይሰሙና «ምን አልሽ አንቺ ብለው ቢጠይቋት ንጉስ የሚባለው ይህን ሁሉ ችሎ የሚያስተዳድር ነው አለች ይባላል»፡፡ከዚያም ንጉሱ ትዕግስተኛ መሆን እንዳለባቸው ተረዱ ይባላል፡፡ ሌላው ደግሞ ንጉሱ ለም የሆኑ መሬቶችን ለመጤዎች (በእንግድነት ወደዚያ አካባቢ ለሚመጡ ሰዎች) ሰጥተው ሲጨርሱ ህዝቡ ማጉለምረም ጀመረና ‹‹እኚህን ንጉስ አልሚ አንበላቸው ወይስ አጥፊ እንበላቸው›› ሲሉ ሰምተው ለካስ አያጠፋሁ ነው በማለት ከጥፋታቸው ተመለሱ፤ ለጥፋተኞችም ይቅርታ ማድረግ ጀመሩ ይባላል፡፡

[10] ኮርቦ  የጎሳ ስያሜ ነው፡፡
ዛንሶ ገደል ነው፡፡ በወቅቱነገስታቱ ጥፋተኞችን የሚቀሙበት ቦታ ነበር፡፡

ከላይ ከቀረቡት ከእነዚህ አፈ-ታሪኮች የምናየው ማህበረሰቡን ከማስተማርና ከመግታት አንጻር ምን ያህል ተግባር እንዳለቸው ሲሆን ንጉሱ በህዝቡ ላይ ብቻ ጥፋተኝነትን እየፈለጉ መቅጣት እንደሌለባቸውና ንጉስም እንደሌሎች ሰዎች እንደሚያጠፋናእንደሚሳሳት አውቆ ሆደ ሰፊ መሆን እንዳለበት የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ቀጣዩ ተረክ 42ም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

*በንጉሱቤትየምትኖርሴትአገልጋይነበረችከዕለታትአንድቀንንጉሱቤ ትውስጥየሌሉ*

*መስኳትይህንንንጉስአመድያድርገው፡፡ብላስትራገምንጉሱሰሙና ብቅብለውአሁንምንድነውያልሽው?                    (የተናገርሽው) ብለውቢጠይቋትአገልጋይቱምይህንንጭምርየታገሰነውንጉስየሚ ባለውብላመለሰችላቸውይባላል፡፡*

በተረክ 39 እንደቀረበው በየም ብሄረሰብ ዘንድ የሴት ልጅ ግርዛትበባህሉ የተከለከለ ነው፡፡ለዚህም መነሻ ተደርጎ የሚነገረው የንጉስ ፊት አውራሪ ገ/መድህን ባለቤት የተገረዙ ስለነበረ ወደ ቤተ-መንግስት እንዳይገቡ የዛር መንፈሱ ከለከላቸው ይባላል፤ በዚህ ምክንያት በአጠቃላይ የየም ሴት ልጆች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መገረዝ ቀረ ይባላል፡፡ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው እነዚህ ተረኮች ማህበረሰቡ ጎጂ  ባህሎችን ነገሮችን የሚገታበት፤በጎ ተግባራትን የሚተክልበት እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው ነገስታቱ የማህበረሰቡን አንዳንድ ችግሮች አይተው በመረዳት ያልፏቸው እንደነበር ይታያል የንጉስና የእግዜር ቃል ጠብ አይልም እንደሚባለው ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ የሰዎችንም ችግር ተረድተው የማለፍ ሁኔታ እንዳለ ለዚህም ተረክ 36 ማሳያ ነው፡፡

*በንጉሱዘመንህዝቡስብሰባተጠራይባላል፡፡ከህዝቡመሀልአንድሰውሚስትጠል ፎአግብቶስለነበርንጉሱየጠሩትንስብሰባቀረይባላል፡፡ከዚያም“አስተሰሮቹ “ (የንጉሱአማካሪዎች) በግድእንዲመጣያስደርጉታል፡፡በዚህምጊዜንጉሱ «እንዴትእኔየጠራሁትንስብሰባንቀህትቀራለህ?»*

*ብለውበቁጣጠየቁትይባላል፡፡በዚህጊዜሰውዬው«*

*አይስብሰባውንንቁሳይሆንአንድወርቅአግኝቼእንዳትጠፋብኝእየጠበኳትነ*

*ው»*

*ሲልመልስይሰጣልይባላል፡፡በዚያንጊዜንጉሱገብቷቸውቶሎፍቱትናልቀ*

*ቁትብለውለአንድወርፈቀዱለትይባላል፡፡*

## 5.5 የነገስታቱን የአመራር ጥበብ የሚያሳዩ ተረኮች


አቶ ኪዳኔ ከበደ በተረክ 46 እንደ ገለጹትና በተጨማሪምበ48ና50 እንደምናገኘው የነገስታቱን የአመራር ስልት በተመለከተ ነገስታቱ የሚመሩት በንጉሳዊ አገዛዝ ስልት ሲሆን በተዋረድ ደግሞ የየጎሳ መሪዎች «አስተሰሮች» የሚባሉ የንጉሱ አማካሪዎች አሉ፡፡አስተዳደራዊ ሚናቸውን ስንመለከት በማናቸውም ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ጉዳዩ ወደ ንጉሱ ከመድረሱ በፊት ተወያይተው የመፍሂ አቅጣጫ በማስቀመጥ በእነርሱ አቅም የሚፈቱ ጉዳዮችን የመፍታት/የመምራት/ ስራ ይሰራሉ፡፡ ነገር ግን ከበድ ያሉ ውሳኔዎችን የሚሹ ጉዳዮችን ለንጉሡ በማቅረብ ያስወስናሉ፡፡

እንግዲህ እነዚህ «አስተሰር» የሚባሉት እንደ ተወካዮች ምክር ቤት ዓይነት ስራ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተዋረድም የየጎሳ መሪዎች /ጋኛ/ የሚባሉ በተጨማሪም የመንደር መሪዎች /ኤራሾ/ የሚባሉ አሉ፡፡ በመሆኑም ህዝቡ ቀጥታ ከንጉሱ ጋር አይገናኝም ከአስተሰሮችለጋኛ፣ ከጋኛ ለኤራሾ፣ ከኤራሾ ለህዝቡ ትዕዛዝ ይተላለፋል፡፡በተቃራኒው ደግሞ ከህዝቡ ግብርና እጅመንሻ ወዘተ… ለንጉሱ የሚደርሰውበእነዚህ አማካይነት ነው፡፡በዚህ ዓይነት ንጉሡ ህዝቡን ይመራሉ፡፡ከዚህ ደንብ የሚወጣ ቅጣት ይጠብቀዋል ማለት ነው፡፡እንግዲህ በየም ብሄረሰበ ከ300 በላይ ጎሳዎች ያሉ በመሆኑ እነዚህ የየጎሳዎች ተወካዮች ህዝቡን ወክለው ከንጉሱጋር ተቀራርበው ይሰራሉ፡፡ መብትና ግዴታቸውን ይወጣሉ፡፡በተጨማሪም በህዝቡ መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችሲፈጠሩ ከታች ከመንደር መሪዎች/ኤራሾዎች/ ጀምሮ ባህላዊ ዳኞች አማካኝነት እዛው ይፈታሉ፡፡በዚህ ዓይነት ከታች እስከላይ በተዘረጋ አስተዳደራዊ ሰንሰለት አማካኝነተ ነገሥታቱ ህዝቡን ያስተዳድሩ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከነገሥታቱ ጋር አብረው የሚሰሩ መዋቅሮችም እንደነበሩ መረጃ ሰጪዎች የገለጹ ሲሆን እነዚህም ከንጉሡ ቀጥሎ አስተሰሮች /ከአሰራሁለት ጎሳዎች የተወከሉ፣ሜን ታሰር/የጦር አዛገሮች/፣ፎን ታሰር/የኑሮ ዘዴ ቀያሾች/፣ ቱምታሰር /ህግአውጪዎች/ ፣ፍላ ታሰር/ነጻ አውጪዎች/ ፣ፋራ ታሰር/አዳዲስ ነገር ፈጣሪና/፣ ያንግ ታሰር/የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት/ የሚኙ ሲሆን ከነዚህ በተዋረድ ከላይ የዘረዘርናቸው የበታች አመራሮችን ይዞ ይመራ እንደነበር ሊታወቅ ችሏል፡፡ቀጣዮቹን ተረክ 46ና48 ይህንኑ ያብራራሉ፡፡

*በባህላዊናበንጉሳዊአገዛዝሥርዓትያስተዳድሩነበርህዝቡከአምላክየተሾሙአ ድርጎይቀበላቸዋል፡፡ንጉሱምህዝቡንያከብራል፣ህዝቡምለንጉሱይታዘዙ ነበር፣በተጨማሪምከየጎሳውተመርጠውየተቀመጡሽንጎዎችአሉ፡፡እነዚ ህበቤተ-መንግስቱዙሪያሆነውስራዎችንያከናውናሉ፡፡ከዚህምባሻገርበየቦታውየ ተሾሙ (ኤራሾ፣ጋኛ፣ጆጋ) የተባሉየንጉሱእንደራሴዎችነበሩ፡፡በህዝቡናበንጉሱመካከልእንደድል ድይሆነውየሚወጡአዋጆችንመመሪያዎችያስተላልፋሉ፣ህዝቡንከንጉሱ ጋርያገኛሉ፡፡*

*ነገስታቱየራሳቸውየሆነባህላዊየአስተዳደርሥርዓትእንደነበራቸውየታሪክአዋ ቂአባቶችይናገራሉ ሥርዓቱምበአስተሰሮች (ከየጎሳየተወከሉተወካዮች) የሚመራሲሆንአስተሰሮቹንበበላይነትየሚመሩት (ታቶ) ንጉሱናቸው፡፡አስተሰሮቹለ"ጋኛዎች " ለየጎሳመሪዎችመመሪያይሰጣሉ፡፡ "ጋኛዎች " በየጎጥ (መንደር)አመራሩአማካይነትለንጉሱግብርያስገብራሉ፡፡ህዝቡለንጉሱ እንዲገዛምያስገድዳሉበእነዚህአማካይነትንጉሱህዝቡንይመራሉ፡፡*




[11]ቻርት አንድ  የንግስናውን ተዋረዳዊ መዋቅር የሚያሳይ


[11]ከፍተኛው የስልጣን መዋቅር ንጉሱ ሲሆኑ ከንጉሱ ቀጥሎ አስተሰር አሉ፣ከአስተሰር ቀጥሎ ጋኛ አሉ ከጋኛ ቀጥሎ ኤራሽ የሚባሉ የስልጣን ደረጃዎች ይገናሉ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ በየተለያ የስራ ዘርፎችም የተለያዩ ባለስልጣናት ያሉ ሲሆን አነሱም ከፖለቲካው ወጣ ብለው ልማትላይ የሚሰሩ ናቸው፡፡እነሱም ሜንታሰር፣ፎንተሰር፣ቱምተሰር፣ፍላተሰር፣ፋራተሰርና ያንግተሰር ናቸው፡፡




ፎቶግራፍ አስራ ሰባት አስራ ሁለተኛው የሞዋ ንጉስ ፊትአውራሪ ገ/መድህን(ጌራኖ) ምንጭ(የየም ልዩ ወ/ባ/ቱ/ስ /ጽ/ቤት

*በተረክ 50 እንደተገለጸው ህዝቡ ነገስታቱንከፈጣሪ እንደተሰጡአድርጎ ይታዘዝላቸው እንደነበር ያሳያል፡ህዝቡለነገስታቱበሚገባይገዛል፡፡ምክንያቱምአምኖየሰጣቸው ስልጣንበመሆኑየላቀከበሬታይጣቸዋል፡፡ከፈጣሪእንደተሰጡተደርጎስ ለሚወሰድየንጉሱትዕዛዝመሬትጠብአይልም፡፡ንጉሱምለህዝቡያስባል ህዝቡንምይወዳል፡፡እያንዳንዱጎሳየራሱመሪ «ጋኛ»የሚባሉአሉት፡፡ሌሎች ደግሞ «ኤራሾ»እነዚህምመሪዎችየመንደርመሪዎችናቸው፡፡ ህዝቡበቀጥታከንጉሱጋርአይገናኝም፡፡ከአስተሰሮች--->ለጋኛ--->ከጋኛ--->ለኤራሽ--->ከኤራሾለህዝቡመልዕክት (ትዕዛዝ) ይተላለፋል፡፡በተቃራኒውደግሞከህዝቡግብርናእጅመንሻለንጉሱየሚ ደርሰውበእነሱአማካኝነትነው፡፡በዚህዓይነትሁኔታንጉሱህዝቡንይመራ ሉ፡፡ከዚህደንብየሚያፈነግጥካለቅጣትይጠብቀዋል፡፡ቅጣቱም "ዛንሶ " የሚባልገደልውስጥተገፍትሮመሞትነበርይባላል፡*

ቀጣዩ ተረክ 52 ደግሞ የስልጣን ተዋረዳቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የሞዋ ጎሳ አስተዳደራዊ መዋቅር እንደ አሁኑ ስርዓት ከየ ጎሳው በተወከሉ ጂጋዎች (እንደ ተወካዮች ምክር ቤት )ዓይነት ነበር ይላሉ፡፡ ከስራቸውም እንደ ሚኒስትሮች ዓይነት መዋቅሮች ነበሩት፤ የጋራ መከላከያ ስርዓትና የጋራ የንግድ ኢኮኖሚ ትስስር ኖሮት የራሱ ንጉስ ያለው በራሱ ባህል የሚተዳደር ስርወ መንግስት ነበር፡፡ በጻድቁ ንጉስ ዮሐንስ በትውልዳቸው ንግስና ዘመንንጉሱ በመንፈሳዊ እምነት መነኩሴና የነገስታት ንጉስ ስለሆኑ መንፈሳቸው ያያል፣ ይቀጣል፣ በሚል ሕዝቡ በፍርሃት በማክበር ይታዘዝላቸው ነበር፡፡ በዚህ የንግስና ስርዓት ከንጉሱ ቀጥሎ አስተሰር ከአስተሰሮች በታች የየዘርፉ መሪዎች ነበሩ፡፡እነሱም ናግተሰር፣ ቱምታሰር፣ ፋሪታሰር፣ ፎንታሰር፣ ሜንታሰር፣ ፍላታሰር፣ ተብለው እያንዳንዳቸው ከተለያዩ ጎሳዎች ሰባት ሰባት አባላት ያሉት መዋቅር ከንጉሱ ጋር የሚሰሩ የበታች አመራሮችም ያሉትየአስተዳደር ስርዓት ነበሯቸው፡፡




*ቻርት ሁለት ከንጉሱ ቀጥሎ አመራሮች  ያሉ የስልጣን መዋቅሮችን የሚያሳይ*

እነዚህ በቻርቱ ላይ የምናያቸው የነገስታቱ የአስተዳደር መዋቅሮች ሲሆኑ ከላይ ወደ ታች እንደምንመለከተው በመጀመሪያ ንጉሱ የበላይ መሪ ሆነው ከስራቸው «ዋሶ» የሚባል የጌመሎ ጎሳ መሪ አለ እሱም አፈ ጉባኤ በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ «አስተሰር» የሚባሉት ከአስራ ሁለት ጎሳዎች የተመረጡ የንጉሱ አማካሪዎች ናቸው ፡፡ እነዚህ አካላት እንደ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያገለግሉ ሆነው ማንኛውንም ጉዳይ የመፍታት ስልጣን ያላቸውና ንጉስም ጭምር ከስልጣን የማውረድም ሆነ የመሾም ኃላፊነት ያላቸው ናቸው፡፡ሌሎቹ ከስር ያሉት አካላት ደግሞ እንደ ሚኒስትሮች  አይነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ ሜንታሰር (የጦር አዛዥ)፣ ፎን ታሰር( የኑሮ ዘዴ ቀያሽ)በዘመናዊው የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር እደሚባለው ነው፤ቱምታሰር ( ህግ አውጪዎች) ፣ ፍላታሰር (ነጻ አውጪዎች)፣ ፋራ ታሰር (አዳዲስ ነገር ፈጣሪና) ያንግ ታሰር፣እንደ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰብሳቢ አይነት በመሆን ለንጉሱ የሚሰሩ ናቸው፡፡

እንግዲህ ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው የዘመናዊ የአመራር ስልትን የጥንት የየም ባሕላዊ ነገስታት ቀድመው እንደ ጀመሩትየሚያሳይና ለዘመናዊውም የአመራር ስልት መሰረት እንደሆነ ነው፡፡ከላይ ከተዘረዘሩት የስልጣን መዋቅሮች በተጨማሪ  በርካታ የየጎጡ (የየመንደሩ) የጎጥ መሪዎች «ጂጋ»፣

«ሸኒ»፣ ባህላዊ ዳኞች ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ የስራ ድርሻዎችም አሏቸው፡፡እነዚህ አካላት አሁንም በዘመናዊው የአመራር ዘመንም በየመንደራቸው የ1ለ5 ቡድን መሪ በመሆን በየመንደሩ በሰዎች መካከል ግጭቶች ሲፈጠሩ በመፍታት ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ማህበረሰቡን ለክስ ገንዘብ ከማውጣትም ሆነ ፍትህ ፍለጋ ከመንከራተትይድናሉ፡፡ ዘመናዊ የህግ አስከባሪዎችም ከስራ ጫና ይተርፋሉ፡፡ ይህ ትልቅ ማሕበራዊ ፋይዳ አለው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች

### 6.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

ከጥናቱ ለማወቅ እንደተቻለው በአንገሪ ቤተ መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገስታት ባህላዊ የአመራረጥ ስርዓትን በተመለከተ በየም ብሄረሰብ የንግስንና ታሪክ በየም ከሚገኙ ከ300 በላይ ጎሳዎች መካከል ወደ ንግስና የመጡት ሶስት ጎሳዎች ሲሆኑ እነሱም‹‹ የጋማ፣የጌመሎና የሞዋ››ጎሳዎች ሲሆኑ የንግስና መቀመጫውን በአንገሪ ያደረገው ግን ‹‹የሞዋ››ጎሳነው፡፡ባህላዊ የአመራረጥ መስፈርቱን በተመለከተ የመጀመሪያው መስፈርት የዚያ ጎሳ አባል መሆንና የቀድሞው ንጉስ ልጅ መሆን ሲሆን ቀጣዩ መስፈርት ለንግስና የታጨው ወጣት ያላገባና ድንግል የሆነና መሆን አለበት፡፡ወጣቱ እነዚህን መስፈርቶች በመጀመሪያ ካሟላ ከዚህ የሚቀጥለው መስፈርት ደግሞ አምልኮአዊ መስፈርት ሲሆን ያንን ወጣት ወደ ጫካ ይወስዱትና ያስቀምጡታል፣ከዚያም ከጫካ ውስጥ ዘንዶ ወይም ነብር መጥተው ሳይተናኮሉት ታክከውት ከሄዱ ያን ወጣት የዛር መንፈሱ እንዲነግስ መርጦታል ይባልና ሌሎች ባሕላዊ ስነ ስርዓቶች ይደረጋሉ፡፡ ከዚያም ያንን ወጣት ሰዎች በየተራ እያዘሉ ወይም የቀኝና የግራ ክንዱን ይዘው «ከርዋ» ቀበሌ ውስጥ ወደሚገኝ ‹‹ኤንኪ›› ወደ ተባለ ቦታ ይወስዱታል፡፡ በዚያም ለዓዞ(ለዛር መንፈስ መስዕዋት አቅራቢ) «ማግ» የሆነ ሰው ዘንድ ይወስዱትና እርሱም ከብት ያርድና ለመንፈሱ መስዕዋት አቅርቦ ይቀባውና ያነግሰዋል፤ከዚያም ጥሩንባ ይነፋና ለሕዝቡ ንጉሥ መንገሱ ይነገራቸዋል፡፡ ከዚያም ማስተዳደር ይጀምራል፡፡

በቤተ መንግስቱ ይፈጸሙ የነበሩ አስተዳደራዊ ስርዓቶችን በተመለከተ ንጉሡ ማንኛውንም አስተዳደራዊ ስራ የሚሰሩት ለብቻቸው ሳይሆን ከበታቾቻቸው ካሉ አማካሪዎቻቸው‹‹አስተሰሮች››ወይም ከአስራ ሁለት ጎሳዎች ከተወከሉ የየጎሳ መሪዎች ጋር ሲሆን ንጉሡ ማንኛውንም ውሳኔ ብቻቸውን አያስተላልፉም፡፡ ከነዚህ በተጨማሪም ‹‹ከአስተሰሮቹ በታች «ጋኛ» የሚባሉ የሶስት መቶውም ጎሳዎች ተወካዮች አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች

ዙሪያ ተጠርተው ከንጉሡ ጋር በመወያየት መፍትሄና ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ከእነዚህ በታች ደግሞ «ኤራሾ»የሚባሉ አሉ፤ በእነሱ አማካኝነት ደንቦችና መመሪዎች ወደ ሕዝቡ ይደርሳሉ፤ ተፈጻሚነታቸውም ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

ነገስታቱ ከሚመረጡባቸው ጎሳዎች ጋር የተያያዙ ተረኮች የሚያመለክቷቸው ማህበረ ባህላዊ አንድምታዎች ‹‹የጌመሎና የጋማ ጎሳዎች››በነገሱበት ዘመናት በህዝቡ ላይ ድርቅ፣ረሃብ፣በሽታ ወዘተ… በመፈራረቁና ‹‹የሞዋ›› ጎሳ በነገሰ ዘመን ግን ድርቁ፣ረሃቡና በሽታው በመጥፋቱ ምክንያት ‹‹የዛር መንፈሱ ለንግስና የመረጠው የሞዋ ጎሳን ነው›› በሚል ታምኖበት ስለ ነበር የሌሎች ጎሳዎች አባላት በታችኛው የስልጣን ዕርከን ላይ እንዲወሰኑ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው እነዚህ ተረኮች  የነገስታቱን የንግስና ሹመት ማንም ተነስቶ መንጠቅ እንዳይችል  የመጠበቅ ተግባርን ሲወጡ በተቃራኒው ደግሞ ሌሎችን የንግስናን ስልጣኑን እንዳያስቡት የሚሾመው(የሚቀባው) ነብር ወይም ዘንዶ [12]ስለሆነ ማንም ተነስቶ ልንገስ (በሃይል ልቆጣጠር) እንዳይል የመግታት ተግባርን በመወጣታቸው ምክንያትእስከ መጨረሻውዳግማዊምኒልክየየብሄር ንግስናን አስቀርተው  አንድ አድርገው አስካስተዳደሩበት ጊዜ ድረስ የሞዋ ጎሳ ንግስና ሊዘልቅ ችሏል፡፡

በዚያን ወቅት ነገስታቱ ህዝቡን ያስተዳድሩበት የነበረው የአመራር ጥበባቸው ከላይ እስከ ታች ተዋረዳዊ የስልጣን ክፍፍል በማድረግ ማለትም ንጉሡ--->አስተሰሮች--->ጋኛ(የየጎሳ ተወካዮች)--->ኤራሾ (የየመንደር መሪዎች) እያለ በሥልጣን ተዋረድ ነበር የሚመራው፡፡ይህም ለዘመናዊ አስተዳደር አርአያ የሚሆን ነው፡፡ በዘመናዊ አመራር ከጠቅላይ ሚኒስተር ጀምሮ እስከ መንደር(ጎጥ አመራር እንዳሉት ማለት ነው፡፡በዚህምእያንድንዱ የየራሱን ሚና አውቆ እንዲኖሩ የሚያደርጉት ተረኮች ጠቀሜታ ማህረረሰቡ በመቻቻልና በመተሳሰብ ባህሉንና እሴቶቹን ጠብቆ እንዲኖርና ላለው

---

[12] አስራ ሁለቱ የሞዋ ጎሳ ነገስታት ባላም (ባለወልድ) ፣አዛግኖ፣ ቶኪኖ፣ ስልባብኖ፣ ማውዳንኖ፣ ኮኬኖ፣ ኖዲኖ፣ ዘርማዲኖ፣ ዲጋምኖ፣ አደሎ፣ቦጊቦና ጌራኖ(ፊት አውራሪ ገ/መድህን) ከ12ው መ/ከ/ዘ እስከ 19ኛው መ/ከ/ዘ ብሄረሰቡን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡

ትውልድም እንዲያስተላልፍ፤ ብሎም የብሄረሰቡ ማሕበራዊ መዋቅሩ እንዳይፈርስ ረድቶታል፡፡

ወደ ንግስና ይመጡ የነበሩት ጎሳዎች ከሶስት ነበሩ፡፡እነዚህም የጋማ፣የጌመሎናየሞዋ ሲሆኑ መስፈርቱ ደግሞ የመጀመሪያው ብዙ የህዝብ ቁጥር መኖር ሲሆን ሌላው ደግሞ ተሰሚነትና፣ ተጽዕኖ ፈጣሪነትና አርበኝነት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገርም በንግስና ዘመናቸው ጥጋብ፣ ሰላም፣ ጤና፣ በረከት ከሰፈነ(ለማህበረሰቡ ምቹ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ) ያ ጎሳ ለንግስና ተመራጭ ይሆናል፡፡ ያ ሳይሆን ቀርቶ በተቃራኒው ረሃብ፣ ጦርት፣በሽታ፣ ችግር ወዘተ…ከተከሰተ ምንም እንኳን ንጉሱ ሌሎች ባህላዊ መስፈርቶችን አሟልቶ ቢመረጥም ለጥቂት አመታት ይታይና ስልጣኑን እንዲለቅ ተጠይቆ ከለቀቀ ለቀቀ ካልሆነ ግን በኃይል ስልጣኑን እንዲለቅ ይደረጋል፡፡ይህም መደረጉ አንድ ንጉስ ስዩመ እግዚአብሄር ነኝብሎ ሕዝቡን በችግርና በመከራ እንዳይሰቃይና በንግስናው ህዝቡ እንዳይማረርና ከባህሉ እንዳያፈነግጥ የመቆጣጠር አስተዋጽ ያበረክታል፡፡

ነገስታቱን ለመምረጥ የሚጠቀሚቸው ባህላዊ መስፈርቶች ማለትም የህዝብ ቁጥር ብልጫነት፣የማስተዳደር ብቃት፣ ብልህነት፣ ጀግንነት ወዘተ የሚያሟላ ጎሳ የሚመረጥበት ምክንያት በብሄረሰቡ ከ300 በላይ ጎሳዎች በመኖራቸው እነዚህን በሙሉ በብልሃትና በጥበብ አዋህዶ ለመምራት የአመራር ጥበብ ያስፈልጋል፣ በተጨማሪም የህዝቡን ደህንነት ለማስጠበቅም ጀግንነት ወሳኝ በመሆኑነው፡፡ ከዚህ ባሻገርም ብዙ የህዘብ ቁጥር ካለው ጎሳ መመረጡ፤ የብዙሃንን ፍላጎት ለማሟላት እንደሆነና በተቃራኒው ደግሞ የስልጣን ዘላቂነትንም ለማስቀጠል ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የነገስታቱ የአመራረጥ ስርዓት የሚፈጸመው በዛር አምልኮ በነብርና በዘንዶ (በልዕለ ተፈጥሮአዊ አካላት) መሆኑ የስልጣን ጥያቄ ለማንሳት የማያስደፍርና ጥያቄውንማንሳት ቢፈለግ እንኳን መራጩ መንፈስ በነብርና በዘንዶ አማካይነት የሚመርጥ በመሆኑ የሌሎች ጎሳዎችን የስልጣን ፍላጎት የመግታትና በአንጻሩ ደግሞ የነገስታቱን ንግስና ቀጣይነት

የማስጠበቅን ተግባር ይወጣል፡፡በተቃራኒው ደግሞ ሌሎች ጎሳዎች ወደ ስልጣን እንዳይመጡ የመግታትን ሚናን ይወጣሉ፡፡

## 6.2 የይሁንታ ሐሳቦች

በአንገሪ ቤተ- መንግስትና በቤተ መንግስቱ ይነግሱ በነበሩ ነገስታቱ ዙሪያ የሚተረኩ ተረኮች ስለየም ብሂረሰብ ታሪክ ጭምር የሚገልጹና ለዘመናዊውም የአመራር ስርዓት እንደ ግብዓት ሊያገለግሉ የሚችሉ በመሆናቸውናከፎክሎር ተለዋዋጭነት አኳያምጨርሰው ሳይጠፉ እነዚህ ገላጭ ተረኮች በአግባቡ ተመሰንደውና ተቀርሰው ቢቀመጡ ለተተኪው ትውልድና ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም በታሪክ ማስረጃነት ያገለግላሉ፡፡

በአንገሪ ቤተ መንግስት፣ ውስጥና በዙሪያው የሚገኙ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ደህንነታቸው በተገቢው ሁኔታ ተጠብቆ ለቱሪስት መስህብነት እንዲውሉ ቢደረግ ብሂረሰቡን ከማስተዋወቅና አልፎም ለወረዳው በገቢ ምንጭነት የሚያገለግል በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ ቢሰራ መልካም ነው፡፡

በየም ልዩ ወረዳው ከአንገሪ ቤተ መንግስት በተጨማሪ ሌሎች ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ፣ሀገረ ሰባዊ ልማዶችና ሐገረ ሰባዊ ትውን ጥበባት ሃብቶች የ ለምሳሌ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቶች፣ ባህላዊ የመስቀል በዓል አከባበር፣ ባህላዊ የዘመን መለወጫ በዓል አከባበርና ወ.ዘ.ተ.ይገኛሉ፤በመሆኑም የልዩ ወረዳው ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽህፈት ቤት በእነዚህ ዙሪያየተለያዩ አጥኚዎችን በመጋበዝ፣በቂመረጃዎችን በመስጠትና በማስጠናት ለሌሎች ማስተዋወቅ ቢችል፣ ብሎም በዩኔስኮ ጭምር ለማስመዝገብ ጥረት ቢያደረግ ለሃገርትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ዋቢዎች

ለማ ንጋቱ/1999 ዓ.ም/‹‹በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና››ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

መሪማ ሙሀሐመድ/2009 ዓ.ም/ «የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነምህረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና» ለኤም ኤ ድግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናታዊ ፅሁፍ ፡፡ አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ማንያለው አባተ/1999 ዓ.ም/‹‹የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው››ለአርትስ ማስተርስ የተረደረገ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ሠመረ ተስፋጋብር/2010 ዓ.ም/«የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ምደባና ይዘት ትንተና»ለኤም ኤ ድግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ሳምራዊት ዘውዱ/2002ዓ.ም/‹‹በጎንደር ከተማ ውስጥ ስለሚገኙ የነገስታት ግንቦች የሚነገሩ አፈ ታሪኮችና ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና››ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ትዕግስት አለማየሁ/2004 ዓ.ም/‹‹የአገው (አዊ) ብሄረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፋይዳ››ለአርትስ ማስተርስ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

አበበ ኃይሉ/1999 ዓ.ም/‹‹ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሄረሰብ››ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ግርማ ቡኤ /2003 ዓ.ም/‹‹የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት››ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ከሁሉም በላይ/2004 ዓ.ም/‹‹የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት››ለአርትስ ማስተርስ ማሟያ የተደረገ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

ወንድወሰን አውላቸው/1998 ዓ.ም/‹‹የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት››ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡ ወርቁ ካብቱ፤ (2007 ዓ.ም) የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/የመ/ኮ/ጽ/ቤት፤ያልታተመ፡፡

ሰሎሞን ተሾመ(2007፣83) ቃለ ተረክ «ፎክሎር ምንነቱና የትኩረት አቅጣጫአዲስ አበባ፣ፋርኢስት ትረዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር

ብርሃኔ ቀያስ(2002 ዓ.ም) ፡፡ የየም ብሄረሰብ ባህላዊ የመስቀል በዓል አከባበርና በበዓሉ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1966 ዓ.ም)የኢትዮጵያ ታሪክ፣ከዓጼ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓጼ ልብነ ድንግል፣አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ታየ ገብረ ማርያም፣(1995 ዓ.ም)የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

ሽኡ መጽሔት (2001ዓ.ም)የየም ልዩ ወረዳ ባህልና ቱሪዚም ጽ/ቤት፡፡

አለም አሸቱ፣ (1992 ዓ.ም) መሰረታዊ የዘገባ አጻጻፍ፣አልፋ አሳታሚዎች፡፡

አንባሳደር ምትኩ ነጋሽ፣ (2005 ዓ.ም)የየም ህግ ሥርዓት፡፡

የየም ልዩ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት (2003 ዓ.ም) ‹‹ የመሬት አጠቃቀም መረጃ››

የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች የኢንቬንተሪ ማኑዋል 2002 ዓ.ም

ያለው እንዳወቅ(1998፣122)የምርምር መሰረታዊ መርሆች አተገባበር፡፡አዲስ አበባ ንግድማተሚያ ቤት፡፡

ዮናስ አድማሱ (1992፣77-119) «አስረኛንኩዋ» የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ-ጽሑፍ መጽሔት፡፡ቁጥር 10፤የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘርሁን አስፋው (2004 ዓ.ም)የስነ ቃል መሰረታዊያን፡፡የተረቶች ዋና ዋና ውጫዊ ቅርጾች፣አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያድርጅት፡፡

ወንድማገኝ ብዙአየሁ፣አየለ ገላንና ሌሎች (2004 ዓ.ም)የየም ብሄረሰብ ታሪክ ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

ወርቁካብቱ (2009 ዓ.ም)ያልታተመ፤የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991፣63-65) የስነ-ቃል መምሪያ፡፡የተረቶች ዋና ዋና ውጫዊ ቅርጾች ፣አዲስአበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

William Bascom (1965, pp. 3-20)The Forms of Folklore: Prose Narratives Author(s): Source: The Journal of American Folklore, Vol. 78, No. 307 Published by: American Folklore Society

Dan Ben-amos (1971)Taward Adefinition at Folklore in context.The journal of American folklore.

Donald A.Macdonald(1972).field work,collecting oral literature Dorson, Rechard (1963፡93-112) «current folklore theories» journal at current Antropology4/1

Deign;cind(1972፡54June 1963)p 235,295.«Oral Folklore, oral narratives»in Folklore and Folklife;Richard M.Dorson Chicago and London; the Universty of Chicagopress,,The university of Chikago press.http://www.Justerorg/stable/URl

Finnegan,Ruth(1970),Limba stories and story telling oxford:clarendon press1967. Finnegan oral literature in Africa.Oxford;Clarendonpress

Fischer I.L «The sociopsychological analysis of folktales»The jornal of current Antropology vol4.No3(

Getachew Fule. (1985). The kingdom of Janjero a historical survey fulfillment of the requierment for B.S Addis Abeba University

Glassie.Henery,(1999).«Material culture»Chikago and London.The university of Chikago press

Goldstein,Kenneth(1964).aguide for field works in folklore,The American folkloresociety;folklore association In1964.

Getachew Fule. (1985). The kingdom of Janjero a historical survey fulfillment of the requierment for B.S Addis Abeba university

Kumar Ranjit; Research methodology;Astep by step guide for beginners(Third edition)London SAGE publicationLtd 2011.

Leach Mareya (Ed) Funk and wagnallsstandard dictionary of folklore ,mythology and legend .Newyork,Kunk and Waganalls 1949.

Lisa M.Given EditoR;The SAGE Encyclopediaof Qualitative Research Methods.volumes 1and2

Martha C.sims;Living Folklore.UtahstateUniversitpress/Logan,Utah2005:1-

Okpewho,Isidore,African oral literature,Bloomington and Indiana polish,Indian university press 1972.

Oring, Elliot.Folkgroups and folklore Geners: An introduction.Logan; Utahstate university press 1986:135-142Thompsonstith,The folklore.

The Dryden press,New York,1946.V.Propp.morphololgy of the folkl the folktale. (2nd edition)

S.N.N.P.R Bureau of Culture and Tourism,The History of yem.by Milkyas Lamiso(2017)

Thompson, Stith. The Folktale. The Dryden Press, New York, 1946. V.propp. Morphology of the Folk the Folktale. (2nd revised edition), Austin, University of Texas Press, 1968

አባሪ1፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ጾታ | ዕድሜ | የስራ ዘርፍ (የሙያ ዘርፍ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ሃይሌ ቀልቤ | ወ | 50 | አርሶ አደር |
| 2. | ወ/ሮወለተ ጊዮርጊስ ሳርባ | ሴ | 80 | አርሶ አደር |
| 3. | ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሰንበት | ሴ | 60 | አርሶ አደር |
| 4. | አቶ ገ/ሚካኤል ባልቻ | ወ | 45 | አርሶ አደር |
| 5. | አቶ ጌታቸው ኃ/ማርያም ሩክሲ | ወ | 50 | የመንግስት ሰራተኛ/አ/ፍ/ቤት |
| 6. | ሊቀ ስዩማን በቀለ ወ/ዮሐንስ | ወ | 67 | ቤተ ክህነት |
| 7. | አቶ ተክለ ማርያም ገሮ | ወ | 88 | አርሶ አደር |
| 8. | አቶ ዲጋ ሙገር | ወ | 89 | አርሶ አደር |
| 9. | አቶ ደግፌ ትዕዛዙ | ወ | 95 | አርሶ አደር |
| 10. | አቶ ንጉሴ ዘበን | ወ | 48 | የመንግስት ሰራተኛናደራሲ |
| 11. | አቶ ገዛኸኝ ረጋ | ወ | 38 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 12. | አቶ ቦጋለ ገ/ማርያም | ወ | 46 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 13. | መ/ር ገበየሁ ጋሼ | ወ | 46 | መምህር |
| 14. | መ/ር ገ/ሚካኤል ጉንቡል | ወ | 52 | መምህር |
| 15. | አቶ ተመስገን አክሊሉ | ወ | 27 | የመንግስት ሰራተኛ/የ/ል/ወ/ባ/ቱ/ስ/ጽ |
| 16. | መ/ር አዳሙ ማሞ | ወ | 43 | መምህር |
| 17. | አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ | ወ | 40 | የመንግስት ሰራተኛ/የ/ል/ወ/ባ/ቱ/ስ/ጽ |
| 18. | መ/ር አሳየ መንጌ | ወ | 42 | መምህር |
| 19. | አቶ ሐብታሙ ዘውዴ | ወ | 42 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 20. | አቶ ሳህሌ ዘበን | ወ | 55 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 21. | አቶ ተካልኝ ሃይሉ | ወ | 40 | የመንግስት ሰራተኛ/የ/ል/ወ/ባ/ቱ/ስ/ጽ/ኃላፊ |
| 22. | አቶ አየለ ዱራ | ወ | 52 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 23. | አቶ በረከት ይገዙ | ወ | 42 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 24. | መ/ር ተሾመ ገ/ሰንበት | ወ | 45 | መምህር |
| 26. | መ/ር አዲሱ ሙሳ | ወ | 52 | መምህር |
| 27. | አቶ ኪዳኔ ከበደ | ወ | 42 | የመንግስት ሰራተኛ |

አባሪ 2 የተሰበሰቡ ተረኮች

ተረክ 1.

ወደ ንግስና የሚመጣው ሰው በቤተሰቡ አንድ ወንድ ልጅ የሆነ ሲሆን እህቶች ቢኖሩትም ችግር የለውም በወቅቱ ለንግስና ተመራጭ ከሆነው ጎሳ ማለትም ከጌመሎም ይሁን፣ ከጋማም ይሁን፣ ከሞዋም ብቻ መስፈርቱ አንድ ወንድ ልጅ መሆንነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ብዙ ወንዶች ካሉበት ቤተሰብ ከሆነ ለስልጣን ሽሚያና ግጭት እንዳይኖር ነው፡፡

ተረክ 2.

የዱሮ ንግስና ሽግግር የሚደረገው ቀድሞ የነበረው ንጉስ በተለያየ ምክንያት ሲለቅ ማለትም በሞት ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላ ወደ ንግስና የሚመጣው ሚስት ያላገባ ብቻም አይደለም ወጣትና ድንግልናውን ያላፈረሰ መሆን አለበት፡፡ ይባላል ንጉሱ በህይወት እያለም በሱ የንግስና ዘመን ለህዝቡ ምቹ ነገር ከሌለ ማለትም ረሃብ ከሆነ፣ ድርቅ ከሆነ፣ በሽታ ከበዛ ፣ግጭትና ብጥብጥ ከሆነ የንጉሱ አማካሪዎች «አስተሰር» ከአስራ ሁለት ጎሳዎች የተመረጡ የንጉሱ አማካሪዎች ናቸው፡፡ እነሱ ህዝቡን ጠርተው ከህዝቡ ጋር ምክክር ካደረጉ በኋላ ያሉት ንጉስ መውረድ እንዳለባቸው ይስማሙና ለንጉስነት ለመመረጥ መስፈርቱን የሚያሟላ ወጣት ያፈላልጉና በቀድሞ ንጉስ ፊት ለፊት ወታደሮች ግራና ቀኝ ክንዱን ይዘው ያልፋሉ፡፡ ንጉሱም እሳቸውን የሚተካ እንደሆነ አውቀው ስልጣን ይለቁና ያ ወጣት ይነግሳል፡፡



ወ/ሮ ወለተ ጊዮርጊ ሳርባ ለንግስና የሚያበቁ መስፈርቶች ዙሪያ ማብራሪ ሲሰጡ

ተረክ 3.

በአንገሪ ቤተ-መንግስት ወደ ንግስና የሚመጣው ሰው በህብረተሰቡ ከተመረጠበኋላ ንግስናውን እንዲይዝ ከተመረጠው ጎሳ ማለት ነው፡፡ያ ሰው ሴት የማያውቅ (ድንግል) የሆነ መጥቶ በቤተ- መንግስቱ እንዲቀመጥ ይደረጋል ከዚያም ነብር መጥቶ ከታከከው ወይም ካልተተናኮለው ያን ሰው በቤተ መንግስት ውስጥ ለ3 ወራት ያህል ስልብ የሆኑ ሰዎች እየቀለቡ ያቆዩታል ከዚያም አስተስሮች« ኡሙ» (ጡሩንባ) እንዲነፋ ያደርጉና ህዝቡን ሰብስበው አዲስ ንጉስ ሊነግስ እንደሆነ በማሳወቅ ያነግሱታል ይባላል፡፡

ተረክ 4.

ሲነገር እንደሰማሁት በመጀመሪያ ከጋማ ጎሳ ቀጥሎ ከጌመሎ በመጨረሻም ከሞዋ ጎሳ ሆኖ ወደ ስልጣን ይመጡ የነበረበት ሁኔታ ልክ እንደ ፊውዳል ስርዓት ከአባት ወደ ልጅ ሆኖ ነገር ግን አስራ ሁለት ሰዎች (አስተሰሮች) ልክ እንደ ሚኒስተሮች ያሉ የንጉስ አማካሪ የሆኑ ሰዎች ነበሩ ይባላል፡፡ እነዚህ በየም ብሔረሰብ ካሉት ከ300 መቶ በላይ ጎሳዎች መካከል

በመምራት ሰዎችን በማስተባበር የተሻሉ ናቸው፡፡ከተባሉ አስራ ሁለት ጎሳዎች ተመርጠው ከዚያም ከአስራ ሁለቱ ጎሳዎች ደግሞ ከየጎሳው የጎሳው አባላት የሚመርጧቸው ናቸው፡፡ አስተሰር (የንጉሱ አማካሪ) ሆነው የሚያገለግሉና እነዚህ ከማማከር ያለፈም ስልጣን አላቸው ይባላል እናም ንጉስ የሚተካ ከሆነም እነዚሁ አስተሰሮች በሚገባ መክረው ማን ቢመርጥ ይሰራል የሚለውን ተወያይተው ለዛር አምልኮ ተፀልዮ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ስርዓት መስዕዋት ለአዞ ከቀረበ በኋላ መስዋቱን ከተቀበለ ከሚመረጠው ጎሳ ለቤተሰቡ አንድ ወንድ የሆነና ሴት የሚያውቅ ልጅ ተመርጦ ይነግሳል፡፡



ሊቀ ስዩማን በቀለ ወ/ዮሐንስ በባህላዊ ንግስና አመጣጡ ዙሪያ ማብራሪያ ሲሰጡ

ተረክ 5

በአጼ ምኒልክ ዘመን የጅማው አባ ጅፋር የየምን ብሔር ጨምረው ለማስተዳደር ጦርነት ከየሙ ንጉስ ፊትአውራሪ ገ/መድህን ጋር ጦርነት ገጥመው በጦርነቱ ሳይሳካላቸው ሲቀር አጼ ምኒሊክን አስፈቀዱ ይባላል፡፡በዚያን ጊዜ የሞች እኛ ራሳችንን በራሳችን ማስተዳደር እንፈልጋለን

ለሚል ጥያቄ በእግር ለ3 ወራት ተጉዘው የተመረጡ ሰዎች ዳግማዊ ሚኒልክ ጋ ሄደው አቤቱታ አቀረቡ ይባላል፡፡ ከዚያም ከሄዱት ሰዎች መካከል ፊት አውራሪ ገ/መድህ ነበሩበት ይባላል፡፡ ምኒልክም ሃይማኖታችሁ ምንድነው? ብለው ቢጠይቋቸው እኛ ሃይማኖት የለንም ሲሉ «ሃይማኖት የሌለው ህዝብ መምራት አይችልም ወይ ክርስቲያን ወይ እስላም የሆነ ነው ህዝብ መምራት የሚችለው ስለዚህ ከአማራ ሀገር ክርሲቲያን መጥቶ እንዲመራችሁ ላደርግ ወይስ ክርስትና ተነስተህ አንተ ትመራለህ?» ብለው ቢጠይቋቸው ፊታውራሪ ገ/መድህ ተጠምቀው መጡ ይባላል፡፡ የመድሃኔ ዓለምን ታቦትና ካሕናት ይዘው በ1888ዓ.ም አምጥተው ቤ/ክ አሰርተው ህዝቡም ክርስትናን እንዲቀበል አደረጉ፡፡ ንግስናቸውንም አጸኑ ይባላል፡፡

በመጀመሪያ የጋማ ጎሳ ነበር ይባላል በጋማ ንጉስ ዘመን ረሀብ ሆነ ዝናብም ጠፋ ለከብቶች የሚሆን ሳር ሳይቀርም ጠፋ እንደገናም አገዛዙ በህዝቡ ላይ ጫና በዛበት እንዲህ እየሆነ ለሰባት አመታት ከመራ በኋላ አስተሰሮች ህዝቡን ሰብስበውት እንዴት ይሻላል በማለት ከመከሩ በኋላ ያ የነበረው የጋማ ንጉስ ስልጣኑን አለቅም በማለቱ አባረው " ኬሌ " የሚባል ቦታ ላይ ገደሉት፡፡ ያ ቦታ አስካሁን ጫካው (ደኑ) ተጠብቆ ነው ያለው፡፡ ማንም ያንን ደን አይነካም፣በጣቱ የጠቆመ ጋሱ ይሞታል ተብሎ ይፈራ ነበር፡፡ ከዚያም ለዛር አምልኮ ተፀልዮ በህልምም ከሞዋ ጎሳ ቢነግስ ገዱ ጥሩ እንደሚሆን አሳይቷል፡፡ በሚል ከሞዋ ጎሳ ፈልገው አነገሱ ይባላል፡፡ የሞዋን ጎሳ ለንግስና ለማጨት ፈልገው ሲያጡ የሞዋ ልጅ ፈልጎ ያገኘ ይሸለማል በማለት አዋጅ አስነገሩ ይባላል፡፡ ከዚያም ይህንን የሰማች ሸክላ ሰሪ ሸክላዋን ልትሸጥ " አያቄጾ" የሚባል ቦታ የሚሸጥ ሸክላ ይዛ ስትሄድ ሁለት ወጣቶች ጉድጓድ ቆፍረው ኢላማ ይጫወታሉ፡፡ በዚህ መሀል አንዱ አልሞ ይመታና እኔ የሞዋው ልጅ ጎበዙ... እያለ ሲፎክር ሸክላ ሰሪዋ ትሰማና ልጆቹ ጨዋታቸውን ጨርሰው ሲሄዱ እኔ የሞዋው ልጅ ያለውን ተከትላ ትሄድና እነሱ ዳጃፍ ቆማ «ሸክላ የሚገዛ» እያለች ስትጮህ የልጁ እናት ትወጣና «እኔ ገዛለሁ» ብላ እህል ትሰጣታለች፡፡ በዚያ ዘመን የሸክላ ዕቃ በእህል ነበረ የሚቀየረው፣ ሸክላ ሰሪዋም «እኔ በእህል ሳይሆን በተልባ ነው

የምቀይረው»ትላለች፡፡ የልጁም እናት እህሉን መልሳ ተልባ ትሰጣታለች ሽክላ ሰሪዋም ተልባውን ትደፋና የምትለቅም መስላ ሁኔታውን እያጠናች ትቆያለች፡፡ ከዚያም የልጁ አባት ሲመጡ ጎሳቸውን አጣርታ ትጠይቃለች፣ ከዚያም ወደ አንገሪ ተመልሳ ለንግስና የሚሆን የሞዋ ወጣት ማግኘቷን ለአስተሰሮች ታሳውቃለች፣ ከዚያም እነሱ  መልዕክተኛ ልከው ሁኔታውን ካጣሩና ትክክለኛ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው በመሄድ የልጁ አባት ቤት ይገቡና የልጁን አባት ይጠይቃሉ፣ ልጁን ንጉስ ለማድረግማሰባቸውን ያስረዱታል፣ አባትየውም ፈቃዱን ይሰጣል፡፡ ከዚያም ወደ ቤተ-መንግስት ባመጡት ዕለት ጠፍቶ የነበረው ዝናብ ይዘንባል፡፡ በዚህም ፈጣሪ የመረጠው ንጉስ ነው ብለው አነገሱት ይባላል፡፡ ከዚያም ረሃብ፣ የዝናብ እጥረት ወ.ዘ.ተ ጠፍቶ የጥጋብ ዘመን ሆነ፡፡ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ንግስናው በዚያው በሞዋ ጎሳ ፀንቶ እስከ ምንኒልክ ዘመን ድረስ ዘለቀ ይባላል፡፡

የመጀመሪያው የሞዋ ንጉስ ባላም (ባለወልድ) ከዚያ አዛግኖ፣ ከዚያ ቶኪኖ፣ ከዚያ ሰልባብኖ፣ ከዚያ ማወዲኒኖ፣ከዚያ ኮከኖ፣ ከዚያ ኖዲኖ፣ከዚያ ዛርማዲኖ፣ከዚያ ዲጋምኖ፣አዱሉኖ እና በመጨረሻም አባ ቦጊቦ (የባህል ስማቸው) ጌራኖ ፌት አውራሪ ገ/መድህን የመጨረሻው፣ ናቸው ፡፡ምኒልክ ሲነግሱ ግን የየብሔረሰቡን ነገስታት ስልጣን አስቀሩና ሁሉንም አንድ አድርገው ገዙ፤ በአንገሪ ቤተ-መንግስት ይነግሱ የነበሩት የሞዋ ጎሳዎች ብቻ ነበሩ፡፡ የጋማ ጎሳ ንጉስ በነበረ ጊዜ መቀመጫው የነበረው “ ዝማር አማ “ የሚባል ቦታ (ኦያ ቀበሌ) በሚባል ቀበሌውስጥ እንደነበርይነገራል፡፡ ቀጣዩም የጌሚሎ ንጉስ ደግሞ መቀመጫውን ያደረገ«ካኘፎቻ “ የፎፋ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ከተተከለበት በስተጀርባ ያለ ቦታ ላይ እንደነበረና የሞዋ ነገስታት ግን በአንጋሪ ቤተ-መንግስት ሆነው ያስተዳድሩ እንደነበር ይነገራል ፡፡



አቶ ተክለማሪያም ገሮ ፣ስለ ሞዋ ጎሳ ወደ ንግስና አመጣጥ ሲተርኩ

ተረክ 6.

በጥንት ዘመን በመጀመሪያ ንጉስ የነበረው የጋማ ጎሳ ነበር፡፡ ከዚያም በጋማ ንግስና ዘመን ድርቅ ተከስቶ ስለነበርና ሕዝቡ በረሃብና በመሳሰሉት፣ ችግሮች በጊዜው በመቸገራቸው የጋማ ጎሳ ንጉስን ወግተው ገድለው በማሶገድ በምትኩ፣ የሞዋ ጎሳ ዘር ተፈልጎ « በከኖሲ ፉጋ» ወይም “ላምነው“ በሚባል ፉጋ አማካኝነት፣ አስፈልገው የሞዋ ዘር በማግኘት መክረው በማሳመን አነገሱ፡፡ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሞዋ ንጉስ መንገስ ጀመረ፡፡ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የመጀመሪያው ንጉስ በሞት ሲለይ ከዚያው ጎሳ ሌላ እያሳመኑ በማንገስ ቀጠሉ በሞዋ ንጉስ ዘመን በጋማ ንጉስ ዘመን የነበረውን አይነት ረሀብ፣ ችግር፣ በሽታ ወ.ዘ.ተ አልተከሰተም በተቃራኒው ጥጋብ፣ ጤና ሰላማዊ ኑሮ በመፈጠሩ ከኋላ ንግስናው በሞዋ ጎሳ ፀንቶ ኖረ፡፡

ተረክ 7.

የአንገሪ ቤተ-መንግስት አመጣጥን በተመለከተ በዚያ ቤተ-መንግስት ይነግስ የነበረው ከሞዋ ጎሳ ሆኖ ለንጉስነት የሚመረጠው መልኩ ያማረ፣ ቁመናው የተስተካከለ፣ ሕዝብን ማስተዳደር ይችላል ተብሎ እምነት የተጣለበት ሰው ከጎሳው አባላት መካከል ተመርጦይሾም ነበር፡፡ ይህም የንግስናውን ሹመት የመስጠቱ ሂደት የሚካሄደው ወይም ይካሄድ የነበረው ቀድሞ የነበረው ንጉስ በሞት ሲለይ የንግስናው ዘመንም ሰባት ዓመት ነበር ይባላል፡፡ የንግስናው ስልጣን አሰጣጥም ለንግስና የተመረጠው ሰው ምርጫ ከተደረገ በኋላ "ዲዛይዛዋ" ወይም "ሺዛይ ሆራ" የሚባል ፍልውሃ ያለበት በርሃ ወርዶ ታጥቦ ከመጣ በኋላ "መላቆ" የሚባል ጎሳ ሴቶች እንስት እየፋቁ እያለ ያ ሰው በዚያ በኩልያልፋል፡፡ ሴቶቹም "ይህ የሚመጣው በእኛ እንሰት መፋቂያ ስፍራ የሚያልፈው ንጉስ ነው ወይ? ብለው ከጠየቁ ከዚያ በኋላ ንጉስ ተብሎ ይሰየማል፡፡

ተረክ 8.

በየም ብሄረሰብ የንግስና አመጣጥ ታሪክ በመጀመሪያ  የጋማ፣ከዚያየሜሎ በመጨረሻም የሞዋ ስርው መንግስት ተያይዞ የመጣ ሲሆን ቀድሞ ከነበሩት በመተላለፍ የሞዋ ስርወ መንግስት ትልቅ ቦታ የነበረውና የመጨረሻዎቹ ናቸው፣ ተብሎ ይነገራል፡፡ በአንገሪ ቤተ-መንግስት ከመመሰረቱ በፊት የጋማ የንግስና መቀመጫ የነበረው "በዝማር አማ" በአያ ቀበሌ ውስጥ እንደነበረና የአንገሪን ቤተ-መንግስትን የመሰረቱት የሞዋ ነገስታት እንደነበሩ የባህላዊ ንግስና ስርዓቱን ግን የወረሱት ከቀድሞው ከጋማ "ከዝማር አማ" ቤተ-መንግስት ነገስታት ነው ተብሎ ይነገራል፡፡

ተረክ 9.

በዚያ ዘመን የነበረው የህዝብ ስልጣን የሚገኘው በስርወ መንግስት ስርዓት በመሆኑ  በባህላዊ ዕውቀትና በባህላዊ እምነት ሒደት ውስጥ የሚፈፀም ነው፡፡ አንድ ንጉስ ሰፊ የህዝብ ቁጥር ካለው ጎሳ የሚመረጥ ሆኖ በህዝብ ብዛት "የጋማ ጎሳ " በጥንቱ በመጀመሪያ የነገሰና መቀመጫውም ሌላ ቦታ

ነበር፣ በመቀጠልም የ"ጌመሎ" ጎሳ ንጉስም የነገሰ ሲሆን ሌላ ቦታ ነበር፣ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ግን የ"ሞዋ" ጎሳ ንጉስ መቀመጫ ቦታ ሲሆን ሁሉም የሞዋ ጎሳ ነገስታት በዚያው ቤተ-መንግስት ነበር፤ ይነግሱና ህዝቡን ይመሩ የነበረው የንግስናው አመጣጡ ንጉስ ሲሞት ሌላ የሚሾም ሲሆን ሌላ ንጉስ እስኪሾም ድረስ ሞቱ በድብቅ ይያዛል፤ ሂደቱ የሚሆነው ሟቹ ንጉስ ልጅ ካለው የእሱ ልጅ ይተካል፡፡ እሱ ወንድ ልጅ ከሌለው ግን የቅርብ የዘመድ፣ የሚሆነው (የወንድም ልጅ) ሊሆን ይችላል ያንን ልጅ ወደ ጫካ ወስደው ያስቀምጡትና በባህሉ ባለው እምነት ነብር መጥቶ ተሻሽቶት ሳይተናኮለው ትቶት ከሄደ ንግስናው ፀድቆለታል ተብሎ ይነግሳል፡፡ ካልሆነ ግን ሌላ ሰው ይፈለግና ያንኑ አይነት ስርዓት ካለፈ ይሾማልእንዲህ እንዲህ እያለ የመጣ ነው፡፡

ተረክ 10.

ቀድሞ ሐንገሪ መናን የነበሩት ፃድቁ ዮሐንስ ነበሩ ይባላል፡፡ እኚህ ሰው ክብር፣ ስልጣን ጥበብ የመሳሰሉትን በቃኝ ብለው ወደ አራዊትና ሐብት ዝሆኖች ገዳም ገብተው ከሰው ተለይተው ሲኖሩ እሳቸውን ፍለጋ ሰባት ነገድ ቤተሰብ ብቻና አልፎ አልፎ የሚመጡ ከብት እረኞች ብቻ እንደነበሩ ይነገራል፡፡ ይህም የሆነው በ435 ዓ.ም እንደሆነና ፎፉ ከተማም የተቀረቀረው በአጼ አምደጽዮን ዘመን በ1212 ዓ.ም ጀምሮ እንደነበር ይገለፃል፡፡ወደ ንግስና ይመጡ የነበረበት መስፈርት በብሔረሰቡ ከሚገኙት ጎሳዎች መካከል አንደኛ በጎሳው አባላት ብዛት ካላቸው ጎሳዎች ማስዳደር አለበት በሚል፣ ባህላዊ መስፈርት፣ ሌላው ባላቸው ማህበራዊ የክብር ደረጃ ነበር፡፡

ተረክ 11.

የታሪክ አዋቂዎች እንደሚናገሩት የየም ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጡ ከየመን በጎንደር አድርገው እንደመጡ የሚነገር ሲሆን ከየመን የመጣው የጌሜሎ ጎሳ እንደነበርና ስርወ መንግስቱንም የመሰረቱት ሼህ ድንቡል የሚባሉእንደሆኑ የንግስና መቀመጫቸውም ሌላ ቦታ እንደነበር ይናገራል፡፡ ከጎንደር የመጣው የሞዋ ጎሳ ሲሆን የሞዋ ስርወ መንግስት መቀመጫውን በአንገሪ ቤተ-

መንግስትቱንቆርቁሮ ሲመራ እንደነበር የሚነገር ሲሆን የመጀመሪያው የሞዋ ንጉስ በላም (ባለወልድ) ተብለው ይጠሩ ነበረ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ዋዛም ቀጣዪ ገልማሽ ቀጣዪ ፉጋቴስቶ የመጨረሻው ተፈራ ገ/መድህን እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡ መስፈርታቸው ካሉት ጎሳዎች መካከል ብዙ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውና ተሰሚነትና ተፅዕኖ ፈጣሪነት ያላቸው ጎሳዎች ነበር ይመረጡና ይመሩ የነበረው አሁንም ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ብናይ በመሪነት ሚና የተሻለ ተብሎ የሚታሰብና አብዛኛው የተሳካለት መሪ የሚሆነው የሞዋ ጎሳ ነው ተብሎ ይናገራል በተግባርም ይታያል፡፡

ተረክ 12.

የአንገሪን ቤተ-መንግስት የመሰረተው የሞዋ ስርወ መንግስትነው፡፡ ስርወ መንግስቱን የመሰረቱት ንጉስ ባላም (ባለወልድ) የተባሉ ክርስትናንም ጭምር ይዘው መጥተው በ12ኛ መ/ክ/ዘመን አጋማሽ ህዝቡን ይመሩ እንደነበር የታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ የንግስና አመጣጡን በተመለከተ እንደሚነገረው የነበረው ንጉስ በሞት ከተለየ የእርሱ ወንድ ልጅ ይመረጣል፡፡ ንጉስ ብዙ ወንዶች ልጆት ካሉት ያሉት ልጆች ተመካክረው ለንግስና እከሌ ይሁን ብለው ይመርጣሉ፡፡ የሚመረጠውም እሱ በዛር አምላክ የሚያምን መሆን አለበት፡፡ ይህንንም ለማጣራት ልጆቹ ወደ በርሃ ዘንዶ ወደሚመለክበት ይወርዳሉ፡፡ ከዚያም ዘንዶው መጥቶ የተጠመጠመበት ከልጆቹ መካከል ንጉስ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ተረክ 13.

የየም ብሔረሰብ የተለያዩ ጎሳዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ጎሳዎች ውስጥ ከሶስት ጎሳዎች ነገስታት የነገሱ ሲሆን በቀደምነት ከጋማ ጎሳ የነገሰ ሲሆን መቀመጫው ሌላ ስፍራ ነበር፣ ቀጥሎከጌሜሎ ጎሳ የነገሰ ሲሆን የእሱም መቀመጫው ሌላ ቦታ ነበር፤ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ላይ ግን የነገሰው የሞዋ ጎሳ ነበር መስፈርቱ የጎሳ አለቆች የምርጫ ስምምነት ነው፡፡ ስለ ንግስናው ታሪክ አመጣጥ የሚነገረው በመጀመሪያ የጋማ ጎሳ ነግሶ ሲያስተዳድር የጌሜሎ ጎሳ አሸንፎ ስልጣኑን ተረክቦ ያስተዳድር እንደነበርና ከኋላም የሞዋ

ጎሳ የጌሚሎን ንጉስ አስወግዶ እንደነገሰና የአንገሪ ቤተ-መንግስትንም የመሰረተው የሞዋ ስርወ መንግስት እንደሆነ ይናገራል፡፡ መስፈርት ተብሎ የሚነገረው ኃይልና ጫና በመፍጠር ብዙ የጎሳ አባላት ያሉት ማስተዳደር አለበት በሚል እምነት ነው፡፡ ከላይ ነግሰው የነበሩ ነገስታት ጎሳዎች ከሌሎች ጎሳዎች ይልቅ ብዙ ሕዝብ ያላቸው ናቸው ይባላል፡፡

ተረክ 14.

በየም ብሔረሰብ ነገስታት ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የነበረው ንጉስ በሞት ሲለይ የንጉሱን ወንድ ልጆች ወይም ከሌላቸው የቅርብ ዘመድ ወንድ ልጆች ተሰብስበው ወደ በርሃ ይወሰዱና ባንድ ቦታ ያስቀምጧቸዋል ብዙ ከብትም በዓይነት ይታረዳል ህዝብ ይሰበሰብና ከልጆቹ፣ 2 ሺህ ክንድ የሚሆን  ርቀ ቆሞ ከልቡ እየጮኸ በልዩ ልዩ ዜማ እየዘፈነ ይጨፍራል፡፡ ጩኸቱ ዘፈኑንና ማቅራራቱ ደምቆ በተሰማ ጊዜ ዘንዶው ከጎሬው መዘዝ ብሎ ይወጣና ከታረደው ከብት ከደሙ ከላሰ (ከቀመሰ) በኋላ በልጆቹ ዙሪያ ይዞርና አንዱ ላይ ይጠመጠማል የቀሩት ወንድሞቹ ተነስተው በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ ከሩቅ ያለው ሕዝብም ማለትም ዘፋኙና ጨፋሪውም ሕዝብ እየሮጡ ይቀርቡና፣እየተደፉ ይሰግዳሉ፣ ከዚያም በኋላ ስልጣን ቀቢ ተብሎ የሚታመነው ዘንዶ ወደ ጎሬው ተመልሶ ይገባል፡፡ ይህ የተቀባ ንጉስ ይነሳና ህዝቡም ይሰግድለታል፡፡ የቀሩት ወንድሞቹም ይሰግዱለታል፡፡ ግን ከዚያ ቀን ጀምሮ እንደ ሌሎቹ ህዝቦች ናቸው እንጂ ከንጉስ ዘር ቁጥር የላቸውም፡፡ ይህ የማንገሱ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ እንደ ግብር ይቆጠርና ያ የታረደው ከብት ሥጋ ይበላል፡፡ ተበልቶ የተረፈ ሥጋ ካለ ወደ ቤት መጥቶ አይገባም እዚያው ጥለውት ነው የሚመጡት ይህ ባህላዊ ስርዓት ነው፤ ከዚያው ንጉሱን አጅበው ወደ ቤተ-መንግስቱ ያገቡታል፡፡

ከዚያም በኋላ በዙሪያ ያሉ ነገስታት መልዕክቶቻቸውን ወደ እርሱ ይልካሉ፡፡ ንጉሱንም ዘላለማዊ ንጉስ ለማለትና ከዘር መንፈሱ እንዲልክላቸው (በረከት እንዲደርሳቸው) በማለት ይደረጋል፡፡ የጥንት አባቶች እንደሚናገሩት የንጉሱ ገላ በዛርመንፈስ ማደሪያ ዘንዶ የተዳሰሰ ገላውን በመዳሰስ የአጎራባች ነገስታትን ገላ በመዳሰስና በመጨረሻም እጁን ታጥቦ በነገስታቱ ራስ ላይ

በመርጨት ይቀቧቸው ነበረ ይባላል ይህም ሥርዓት እስከ ቀደማዊ ሚኒልክ ድረስ ይደረግ እንደነበር ይናገራል ከዛር መንፈሱ ይቀቡ የነበሩ አጎራባች ነገስታት የተባሉትም የካፋ፣ የዳውሮ፣ የካምባታና የወላይታ እንደነበሩ ይነገራል፡፡በዚያን ዘመን በየም ብሄረሰብ ሀይማኖት ተከታይ (እስልምና ወይም ክርስትና) የለም ነበር ሰዎች በዘንዶ፣ በአዞ፣ በዛር፣ መንፈስ ነበር የሚያምኑት በዛን ጊዜ ዘርን እንደ ፈጣሪያቸው አድርገው ያመልኩና መስዋትም ያቀርቡ ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ዘርን የሰደበ የሚፈረድበት ከጃንጀሮ ንጉስ ዘንድ ሲሆን ውሳኔውም ለዘንደው ይሰጥና ያ የተሰደበውን ሰው ዘንዶው እንዲውጠው ይደረግ ነበር ክርስቲያኖችንም ጭምር ይሰጡ ነበር ይህ የዛር እምነት የቀረው በፊታውራሪ ገ/መድህን የአስተዳደር ዘመን አባጀፋር የየምንም ግዛት ጭምር ለመግዛት ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ ነበር በኋላም አባጅፋር በጦርነቱ ተሸነፉና ለዳግማዊ ምኒሊክ ከሰሱ ዳግማዊ ሚኒልክ ለየሙ ንጉስ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ በጠየቁበት ወቅት ፊታውራሪ ገብረ መድህንም ለአቤቱታ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ ሲሄዱ ዳግማዊ ምኒልክም አንተ ሀይማኖህ ምንድነው ብለው ቢጠይቋቸው እኔ በዛር ነው የማምነው ይላሉ፡፡ ንጉሱም ሀይማኖት የሌለው ሕዝብ መምራት አይችልም፡፡ ሀይማኖት የሚባለው ክርስትና ወይም እስልምና ነው፡፡ ከእነዚህ ሀይማኖቶች አንዱን ከተቀበልክ ንግስናህን ይዘህ ትቀጥላለህ አሏቸው፡፡ ከዚያም ፊት አውራሪ ገ/መድህን በማግስቱ እዛው አ.አ ተጠምቀው ንግስናቸው አጽንተው የጊዮርጊስ ጽላት ከካህናት ጋር ተሰጥቷቸው ይዘው መጡ ስማቸውም ቦጊቦ ይባሉ የነበሩት በስመ ክርስትናቸው ፊትአውራሪ ገ/መድህን ተባሉ ከዚያም በአንገሪ ቤተ-መንግስት አጠገብ ቤ/ክ ያን አስርተው የጊዮርጊስን ጽላት አስገብተው ህዝቡም ክርስትና እንዲጠመቅ አድርገው ሲያስተዳድሩ ያን የጊዮርጊስን ጽላት ማሮ ወደ ሚባል ቦታ አዛወሩትና በድጋሚ የፎፋ መድኃኒ ዓለምን ፅላት ያስመጡና ለዛር መስዋዕት ይሰዋበት የነበረ ቦታ ላይ (አሁን ቤ/ኑ) ያለበት ቦታ ላይ ታቦቱን ተከሉ ምክንያታቸውም የዛር መንፈሱን ለማራቅ ነው ይባላል፡፡

ተረክ15.

ንጉሱ ከሚመረጥበት ጎሳ ለንግስና የታጨውን ሰው አዝለው ለንግስና እንዲቀባ የሚወስዱት ሁለት ጎሳዎች ነበሩ ይባላል፡፡አንዱ«የመለቆ»ጎሳ ሲሆን ሌላው ደግሞ «የሰከኩ»ጎሳ ናቸው፡፡እነዚህ ሰዎች ለንግስና የተመረጠውን ወጣት የግራና የቀኝ ክንዱን በመያዝ ሲሄዱ እንሰት ከሚፍቁ ሴቶች መካከል አንዷ «ይህ ንጉስ ይመስላል» ብላ ከተናገረች ከዚያን ቀን ጀምሮ «ንጉስ ነህ» ተብሎ ስያሜ ይሰጠውና ከዚያም ታዝሎ ይሄድና ውጭ ጫካ ውስጥ ለ8 ቀናት ያድራል፡፡ ጠባቂዎቹም ነብር፣አባብና የመሳሰሉት አራዊት እየጠበቁት ከቆየ በኋላ መልሰው ወደ ቤተ መንግስት ያመጡትና ለ8 ቀናትከሰው ተለይቶ እንዲቀመጥ ይደረግና ከዚያ በኋላ በይፋ ንጉስ መሆኑ ይታወጅና ማስተዳደር ይጀምራል፡

በአንገሪ ቤተ መንግስት ለንግስና የሚመረጠው «ከሞዋ»ጎሳ ነው፡፡ምክንያቱም «ከባላም»የመጣ ዘር ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡«ባላም» ማለት የፈጣሪ ዘር ለማለት ነው፡፡ለንግስና የሚመረጠው የሞዋ ጎሳ ሆኖ ሌሎች ጎሳዎች እንደ ድጋፍ ሰጪ በመሆን ያገለግላሉ፡፡በየም ብሄረሰብ የሞዋ ጎሳ የባላም ዘር ነው ብለው ስለሚያምኑ አሁንም ድረስ ለጎሳው ልዩ አክብሮት ይሰጣሉ፣አሁንም ቢሆን በተለያዩ ባህላዊ ተቋማት ማለትም በመንደር መሪነት፣በሃገር ሽምግልና ወዘተ. የሚመርጡት የሞዋ ጎሳ አባላትን ነው፡፡

ተረክ16.

በየም ብሔረሰብ ከ300 በላይ ጎሳዎች እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም ወደ ንግስና የመጡት የጋማ ጎሳ፣ የጌመሎ ጎሳና የሞዋ ጎሳ ናቸው ይባላል፡፡ በመጀመሪያ የነገሱት የጋማ ጎሳ አባላት በቅድሚያ የነገሱና ህዝቡን ያስተዳደሩት እንደነበርና የተወሰነ ጊዜ ካስተዳደሩ በኋላ ቀጥሎ የጌመሎ ጎሳ በመጨረሻም የሞዋ ጎሳ እንደነበርና የአንገሪ ቤተ-መንግስትንም የቀረቆሩት የሞዋ ነገስታት እንደሆኑ ሲሆን መስፈርቱ ከየም ጎሳዎች መካከል የጎሳው አባላት ብዛት ካለው ጎሳ ቢያስተዳድር መልካም ነው በሚል ታምኖበት በምርጫ የተደረገ እንደሆነ ነው የሚነገረው፡፡የጌመሎ ጎሳ ንጉስ ወርዶ የሞዋ ጎሳ ንጉስ እስከዳግማዊ ምኒልክ ንጉስ ድረስ ዘልቋል፡፡

ተረክ 17

ታቶ ጌራኖ ( ንሩስ ጌራኖ) በወሎው ንጉስ በራስሚካኤል አበልጅነት ክርስትና ተነስተው "ጌራኖ "ይባል የነበረው ስማቸው «ፊትአውራሪ ገብረ መድህን ቦግቦ »ተብለው ተጠርተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት ለንጉሥ ፊትአውራሪ ገ/መድህን ተሰጥቶ ከነካህናቱጋር ወደ የም በማምጣት አንገሪ በተባለው የመናገሻ(ቤተ-መንግስት) ቦታ ላይ ታቦቱን አስተክለው በካህናት ሲያስገለግሉ የቆዩ ሲሆን የታቦቱ ቤተ መቀደስም የሣር ቤት እንደሆነ የሚያረጋግጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምሰሶውነበረ፡፡እንደ ክረስትያን ስርዓትም በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ መቃብሮቹ አሁንም አሉ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ በግምት ከ1888-1890 ዓ/ም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ባለው ጊዜ ውስጥ የመድሃኒዓለም ታቦት በድጋሚ በካህናትና በሊቃውንት ታጅቦ ወደ አንገሪ በመምጣቱ አንገሪ የነበረው የቅ/ጊዮርጊስ ታቦት ማፎ ወደ ተባለው ቦታ እንደተዛወረና አሁንም ድረስ ያለ መሆኑ የታሪክ ማረጋገጫ ነው፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረው የአንገሪቤተመንግስት በዝነኛው ንጉስ በአባ ቦግቦና በልጃቸው በጌራኖ ዘመን እንዳበቃና የፊትአውራሪ ገ/መድህን ልጅ አቶ ተፈራና ወንድመሞቻቸው ሥልጣን ተከፋፍለው በየቀበሌው ግዛት ይዘው እያስተዳድሩ ቢኖሩም የቀድሞውን ግርማ ሞገስ ግን አጥቷል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ማዕከላዊው መንግስት ሥር እየሰደደና እየጠነከረ መምጣት እና የአጼ ሃይለስላሴ ስርዓት ተወካዮች ከአዲስ አበባ እየተሸሙ ወደ ፎፋ የቀድሞው የየም ብሔረሰብ ዋና ከተማ በመምጣታቸው ንግስናው የይስሙላ/Nominal/ ሆነ፡፡ ሁኔታው በዚህ መልክ በመቀጠሉ የክርስትና እምነት ከቤተ-መንግስት ከመሳፍንትና ከመኳንንት/አስተሰር/ ማለትም ከፓርላማው አልፎ ወደ ተራው ህዝብ ዘንድ መድረስ ስላልቻለና ህዝቡ በባህላዊው አምልኮው በመቀጠሉ ዳይሬክተር መንገሻ በተባሉ የማዕከላዊ መንግስት ተሿሚ አማካይነት አዋጅ ወጥቶ ህዝቡ ይጠመቅ ዘንድ ነጋሪት ተጎሰመ፡፡ የዳይሬክተር መንገሻን አዋጅ እሺ በጄ ብለው የተቀበሉ ሰዎች ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በበጋው ወራት በወርሃ የካቲት በፎፋ ደብረ መድሃኒት

መድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ስርዓተ ጥምቀት በሺዎች ለሚቆጠር ህዝብ ተፈፀመ፡፡ይህ ማለት ግን ሁሉም የየም ህዝብ በሙሉ ተጠመቀ ማለት አይደለም፡፡ በተለይ የባህላዊ አምልኮ ካህናት፣ የየጎሣው አንኳር ተጠሪዎች፣ ትንቢት ተናጋሪ ቃሊቻዎች፣ መፍቀሬ ባህላዊ አምልኮ የሆኑ ሰዎች በእምነታቸው ስለፀኑ፤ አንዳንዴ በማግባባት፣ አልፎ አልፎም በኃይል መልክ እነዚህን እምቢተኞች ወደ ክርስትናው እምነት የማስገባት ሁኔታ ነበረ፡፡ ቀስበቀስም መላው ህዝብ ክርስቲያን ሆነ፡፡ ሆኖም ግን ባህላዊው አምልኮ እስከ ደርግ ጊዜ /ዘመን/ መባቻ ድረስ ከክርስትናው ጎን ለጎን በተጠናከረ መልኩ ቀጠለ፡፡ ሁሉም ጎሣዎች በአማልዕክቶቻቸው ማምለክና መስዋዕት ማቅረባቸውን ተያያዙ ፡፡ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ስብከተ ወንጌል በየእሁዱ ቢሰጥም በእጅጉ ስር በሰደደው ባህላዊ አምልኮ ምክንያት የክርስትናው እምነት ከአንገት በላይ ሆኖ ኖረ፡፡በዚህ ምክንያት የየም ብሔረሰብ ጎሳ መሪዎች ባለ ቃልቻዎች/የየጎሳው አንኳሮች/ ታቶዎች እርግጠኛ ቀኑን መናገር ባይቻልም በ1969 ዓ/ም ኦያ በተባለው ጫካ ውስጥ በመሰብሰብ ባህላዊውን አምልኮ/ሚዮ/ ለማስቀረት ውሳኔ በህዝብ ደረጃ ተደነገገ፡፡ አሁንም ውስጥ ውስጡን አምልኮው ቀረ የሚያስብል ሳይሆን ቀረ፡፡የደርግ ስርዓት ይህን ያደረገበት ምክንያት ክርስትናን ከማስቀደምና ባህላዊውን አምልኮ ከመፀየፍ አንጻር ሣይሆን ደርግ የማንኛውም እምነት /ሀይማኖት/ ተፃራሪና የማርክሲስት ቤኒኒንስት ፍልስፍና ተከታይ ስለነበር ነው፡፡ይህ ባህላዊው አምልኮ ውስጥ ውስጡን የመቀጠሉ ነገር በውስጥ ውስጡ ሲታይ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን እንደገና በ1996 ዓ/ም በወረዳ ደረጃ ህብረተሰቡን ያሳተፈና ወጥነት ያለው ውሳኔ ወጥቶ ህዝቡ ከባህላዊው እምነት ተፅዕኖ እንዲላቀቅ የተደረገው የቅርብ ጊዜ ተውስታ ነው፡፡(ምንጭ የየም ልዩ ወረዳ ባ/ቱ/መ/ኮ/ጽ/ቤት)

ተረክ 18

በየም ከሚገኙ ጎሳዎች መካከል ወደንግስና የመጡት የጋማ በመጀመሪያ ቀጥሎ የጌመሎ በመጨረሻም የሞዋ ጎሳ አሸንፎ ስልጣኑን ይዞታል፡፡ በአንገሪ የነገሰው የሞዋ ጎሳ ብቻ ነው፡፡ወደ ንግስና የሚመጣው የጎሳ አባል በህዝቡ

ብዛት ብዙ ሕዝብ ያለው ጎሳ ሆኖ ሕዝብን ማስተዳደር ይችላል ተብሎ እምነት የተጣለበት ሰው ብቃታቸውና በህዝብ ብዛቱ ጫና ማሳደር ከሚችል ጎሳ ተመርጦ ከነገሰ በኋላ በቤተ ዘመድ እየተላለፈ ስልጣኑ ይሄድ እንደነበር ይነገራል፡፡

ተረክ 19.

የየም ብሄረሰብ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ660 ዓ.ም አካባቢ ከየመን በመምጣት አሁን ባለበት አካባቢ ሲሰፍር "የ"ከመጣበት አካባቢ.የመን ከሚለው ቃል በመውሰድ "ንጋር" ከአሁን ከሰፈረበት አካባቢ ጋርበማገናኘት "የንጋር" በማለት አሁን ያለበትን አካባቢ በመሰየም ትርጉሙ የየሞች ሃገር ማለት ነው፤ እራሱን በራሱ ሲያስተዳድር የቆየ ሲሆን በመጀመሪያ የጋማ ጎሳ በሁለተኛ ደረጃ የጌመሎ ጎሳ ሲመራ ቆይቶ በመጨረሻም የሞዋ ጎሳ ሲያስተዳድር እንደቀጠለ የሚነገር ሲሆን መስፈርቱ ደግሞ ተቀባይነት፣ ተሰሚነት፣ በሳል ውሳኔ ሰጪነት፣ በሳል አስተሳሰብና ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታ ብልነነት ንቁና ፈጣን እልባት የሚሰጡ ፈጣን ልማት ያመጣሉ ተብሎ የታመነባቸው የሚመረጡና እነዚህም የሚለኩት በአደን፣ በአርበኝነት (ጦረኝነት) ያላቸውን የበላይነት በማየት የንግስና ስልጣን ይሰጣቸው ነበር ይህ ሁሉ የሚሆነው በሀይል ሳይሆን በአስተሰሮች ወይይት ተደርጎ ታምኖበት ነው የሚመረጠው፡፡

ተረክ 20.

የአንገሪ ቤተ-መንግስት በ13ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ቆርቁሮ የነገሰው የሞዋ ጎሳ ሲሆን ስልጣን የሚይዝበት መስፈርት የጎሳው አባል የሆነና የንጉሱ የመጨረሻ ልጅ የሆነ ወንድ ልጅ ሲሆን እሱም የባህላዊ እምነት መስፈርቱን ካለፈ የሚነግስ ሲሆን መስፈርቱን ካላሟላ ከመጨረሻ ሁለተኛ ልጅ ወንድ ሆኖ መስፈርቱን ካሚላ ይሾማል ካላሟላ የቅርብ ዘመድ ልጅ መስፈርቱ የሚያሟላ ተፈልጎ ይነግሳል፡፡ ባህላዊ መስፈርቱም ያን ለንግስና የተመረጠውን ልጅ ጫካ ወስደው ያስቀምጡታል፤ ከዚያም ዋሸንት ሲነፉ ነብር ወጥቶ ሳይተናኮለው ከቀረ ወይም ተሻሽቶት ከሄደ ለንግስና

ተመርጧል፣ በአምላክም ዘንድ ንግስናው ተቀባይነት አግኝቷል ብለው ያምናሉ ከዚያም በባህል ስነ-ስርዓት ይቀቡታል (ያስቀቡትና) ያነግሱታል፡፡ ነገር ግን ነብሩ ከተተናኮለው ወይም ካልተሻሸው ያን ወጣት ለንግስና አልመረጠውም ተብሎ ስለሚታመን ሌላ የዘመድ ልጅ ተፈልጎ መስፈርቱን ካሟላ ይሾማል፡፡

ተረክ21.

ወደ ንግስና ይመጡ የነበሩት ከሦስት ጎሳዎች ሲሆን ከጋማ ጎሳ፣ ከገሜሎ ጎሳና በመጨረሻም ከሞዋ ጎሳ የነገሱ ሲሆን መስፈርቱም ከተመረጠው ጎሳ የተመረጡ ልጆች የተለያዩ ባህላዊ ስነ-ስርዓቶች ከተደረጉ በኋላ ከብዙ ሰዎች ጋር ውጭ ያድራሉ፡፡ ከእነዚህም ሰዎች መሃል በተመረጠው ልጅ ላይ ዘንዶ ከተጠመጠመ ወይም ነብር መጥቶ ከታከከው ያ ሰው ለንግስና ተመርጧል፡፡ ንግስናውን አምላክ ተቀብሎታል ተብሎ ይሾማል መስፈርቱ ይህ ነው፡፡ በነብሩ ወይም በዘንዶ ያልተዳሰሰ አልተቀባም ይባልና አይነግስም ዋናው መስፈርት በዘንዶ ወይም በነብር መቀባት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ተረክ 22.

በአንገሪ ቤተ-መንግስት የመጀመሪያም የመጨረሻም ነጋሲያን የሞዋ ጎሳ አባላት ነብሩ የአንገሪ ቤተ-መንግስት በ12ኛው መቶክፍለ ዘመን አጋማሽ ተመሰረተ፡፡ በመጀመሪው የሞዋ ንጉስ “ታቶ ባላም“ ወይም ንጉስ ባለወልድ እኚህም ከጎንደር መጥተው የነገሱ፣ የሞዋ ጎሳ ናቸው ይባላሉ ተመሰረተ፡፡ ቀድሞ የነበረው የጋማ ጎሳ ስርወ መንግስት መቀመጫው አያ ቀበሌ ላይ ነበር፡፡ ቀጥሎም ለአጭር ጊዜ የነገሰው የጌሜሎ ስርወ መንግስት መቀመጫውን መሊሳ የሚባል ቦታ «ካን ፎቻ» ላይ ነበር አድርጎ የነበረው፡፡ ወደ ንግስና ለመምጣት መስፈርቱ በመጀመሪያ የዚያ የተመረጠው ጎሳ አባል መሆን ሲሆን በተጨማሪ ሌሎች መስፈርቶችም አሉት፡፡ እነሱም ሴት የሚያውቅ (ድንግላዊ) የሆነ መሆን፣ ሌላው በጫካ ውስጥ ለብቻው እንዲቀመጥ ተደርጎ በነብር መስል (የዱር እንስሳት) መፈተን አለበት ይባላል፡፡ ከዚያም ወደ ጊቤ ወንዝ ሄዶ “በዎማ“ ፍል ውሃ መታጠብ፣ቀጥሎም

በጊዜ ዳር የንግስና ዘመኑ ዕድል ትንበያ ሥርዓት ከተደረገ በኋላ “ማጎች“ ቀጣዩን ስርዓት ፈፅመው ያነግሱታል፡፡ አስተሰሮች ከንጉሱ የበለጠ ስልጣን እንዳላቸው ይነገራል ንጉሱ ደንቦችን ማፅደቅ ብቻ ነው ስራው ይባላል፡፡

ተረክ 23.

ይነግሱ የነበሩት ከጋማ ጎሳ፣ ከጌመሎ ጎሳና ከሞዋ ጎሳ ነበር፡፡ መስፈርቱም የዛ ጎሳ አባል የሆነና ሴት ያላወቀ (ድንግል የሆነ) ወጣት ነው፡፡ ከጌመሎ ጎሳ ቀጥሎ በመጨረሻ የሞዋ ጎሳ በመንገስ ቤተ-መንግስቱን በአንገሪ መስርቶ በቅደም ተከተል ከታቶባላም (ከንጉስ ባለወልድ) እስከ ንጉስ ፊትአውራሪ ገ/መድህን ድረስ መስፈርቱን የሚያሟሉ አስራ ሁለት ነገስታት የየምን ህዝብ አስተዳድረዋል፡፡ የጎሳ አለቆችም ህብረት (ጋኛ) ከአስተሰሮች ቀጥሎ የአመራርነት ሚና ነበራቸው ፡፡ በዚህ መልኩ የሞዋ ጎሳ ሲመራ ቆይቶ ከአፄ ኃይለስላሴ ንግስና ጀምሮ የየብሔር መሪ ሲቀረ ቀርቷል፡፡

ተረክ 24.

በአንገሪ ቤተ-መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ የንግስና ስልጣን የያዙት የሞዋ ጎሳዎች ናቸው፡፡ ከነሱ ቀደም ብሎ የጋማ ጎሳ አስራ ሁለተኛ ንጉስ ጊዜ (በሳቸው ዘመን) ድርቅ ተከስቶ ነበር ይባላል፡፡ ለሰባት አመት ሙሉ የዘለቀ ድርቅ ስለነበር ሕዝቡ የሞዋን ጎሳ አንግሰን ብናይ ጥሩ ዘመን ሊመጣ ይችላል በሚል እምነት ከብዙ ፍለጋ በኋላ አንድ ብቸኛ ሞዋ ተገኝቶ የየም ብሔረሰብ በሙሉ ካለበት አምጥቶ እንደ አነገሰው ይነገራል፡፡

ተረክ 25.

በመጀመሪያ የጋማ ጎሳ የነገሰ ሲሆን ቀጥሎ የጌመሎ ጎሳ ነግሶ በመጨረሻም የሞዋ ንጉስ መሆኑ ይነገራል መስፈርቱ በኃይልና ጫና በመፍጠር ሆኖ ቀድሞ የነበረው ከኋላው የመጣው ተዋግቶ በማሸነፍ እንደሆነ ይነገራል፡፡በየም ብሔረሰብ ካሉ ከ300 በላይ ጎሳዎች መካከል ለንግስና ተመርጠው የነበሩት እነዚህ ሶስቱ ጎሳዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ጎሳ አባላት መካከል ወደ ንግስና ለመምጣት መስፈርቱ በቤተሰቡ አንድ ወንድልጅ

ለንግስና ይመረጣል፡፡ እህቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ የሚከለክለው ነበር የለም፡፡ ነገር ግን ሴት የማያወቅ (ድንግል የሆነ) መሆን አለበት፡፡



አቶ ሃይሌ ቀልቢ ከየትኞቹ ጎሳዎች ሰዎች ወደንግስና በምን መስፈርት ይመረጡ እንደነበር ሲገልጹ

ተረክ26 .

ከጋማ፣ ከጌመሎና ከሞዋ ጎሳዎች ነበር ይነግሱ የነበረው በአንገሪ ቤተ-መንግስት ግን ይነግሱ የነበሩት የሞዋ ጎሳዎች ብቻ ነበሩ፤የጋማ ሥርወ መንግስት መቀመጫው «ዝማር-ኣማ»፣የጌመሎ ሥርወ መንግስት መቀመጫው «ካንፎቻ»ሲሆን የሞዋ ሥርወ መንግስት መቀመጫው የአሁኑ የአንገሪ ቤተ-መንግስት ነው በአንገሪ ቤተ-መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገስታት የንግስና አመጣጥን በተመለከተ የንግስና አመጣጡ የኦሪት ህግን የተከተለ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ የእነ ንጉስ ዳዊትንና የንጉስ ሰለሞንን የንግስና ሁኔታ ስንመለከት በህጻንነታቸው ፣ለቤተሰቡ የመጨረሻ የሆነ ወይም ለቤተሰቡ አንድ ልጅ ሆነ ነበር የሚነግሰው ዳዊት ለቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ነበር፡፡ ሰለሞን ደግሞ ለቤተሰቡ አንድ ልጅ ነበር የየም ብሄረሰብ አመጣጥንስንመለከት ከጎንደር የመጣው የሞዋ ጎሳ ከእስራኤል ሆኖ ወደ

ጎንደር ከገባ በኋላ በጎንደር የራሡን መንግስት መስርቶ ከቆየ በኋላ በጎንደር ውስጥ የመታሰቢያ ዛፍ በመትከል ወደ የም ምድር እንደመጣና ሌሎች ጎሳዎችም አብረውት እንደመጡ የሚነገር ሲሆን እነሱም «ዋዛም፣ ፉጋ ቴስቶ፣ጎሉማሽና ሞዋ ናቸው፡፡ ከሞዋ ጎሳ የመጡት የመጀመሪያው የሞዋ ንጉስ የነበሩት ባላም(ባለወልድ) እንደሆኑ ይነገራል፡፡እኚህ ሰው ከሶስት ወንድሞቻቸው ጋር 44 ታቦታትንና የክርስትናን እምነት ወደየም ምድር ያመጡና ያስፋፉ እንደነበር ይነገራል፡፡ የንግስና ሥርዓቱም ከእስራኤላዊያኑ የያሪት ስርዓት የተወሰደ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ተረክ 27.

ለንግስና የመጡት ጎሳዎች ጋማ፣ ጌመሎና ሞዋ፣ ሲሆኑ ሌሎች ጎሳዎች በአማካሪነት ንጉሱን ያገለግሉ ነበር፤ንግስናው ከሞዋ ጎሳ ከሆነ ንግስናው የሚተላለፈው ከአባት ወደ ልጅ እየተወራረሰ ነበር የሚሄደው፡፡ መስፈርቱ የዚያ ጎሳ አባል መሆን የመጀመሪያው ሲሆን ሌሎች ባህላዊ መስፈርቶችም አሉአንድ ወንድ ልጅ ሆኖ ድንግል መሆን አለበት፡፡

ተረክ28.

በአንገሪ ቤተ-መንግስት ለንግስና ይመረጥ የነበረው ጎሳ የሞዋ ጎሳ ነበር፡፡ መስፈርቱም የሞዋ ጎሳ አባል መሆን የመጀመሪያው ሲሆን ሌሎች መስፈርቶችም አሉት፡፡ እነሱም ለቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ መሆን ወይም ብቸኛ ልጅ መሆን፣ድንግልና ያላገባ መሆንና ከነዚህ በተጨማሪም ሌሎች ባህላዊ መስፈርቶችንም ማለፍ ይጠበቅበታል፤እነዚህም ያ ለንግስና የታጨው ወጣት ወደ ጫካ ይወሰድና በጫካ መሃል እንዲቀመጥ ይደረጋል፣ ከዚያም ነብር፣ዘንዶና መርዘኛ እባብና ሌሎችም የዱር አራዊቶች መጥተው ከተተናኮሉት ፈተናውን ይወድቃል፡፡ ሌሎቹ የንግስና ስርዓቶች ሳይፈጸሙለት ወደሌላ ወጣት ፍለጋ ይኬድና ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሲያሟላ ቀጣዮቹ ስርዓቶች ይካሄዱና ይነገሳል፡፡ ከዚያም በአስተሰሮች አማካኝነት ቆንጆ፣ ባለሙያና ድንግል የሆነች ወጣት ትመረጥና ንጉሱ ወደ ቤተ-መንግስት ሲገባ ለንጉሱ ሚስት ሆና አብራ ወደ ቤተ-

መንግስት ትገባለች፤በቤተ መንግስቱም ከፍተኛ ድግስ ይደረግና ንጉሱንም ከወጣቷ ጋር የጋብቻ ቃል ኪዳን አስገብተው ይድሩታ፡፡ ከዚያም ማስተዳደር ይጀምራል፡፡ በአንገሪ ቤተ-መንግስት በንጉስነት ሲመራ የቆየዉ የሞዋ ጎሳ ነው፡፡

ተረክ 29.

በመጀመሪያ ከጋማ ጎሳ ነግሶ ለሰባት አመታት ከመራ በኋላ በእርሱ የአመራር ዘመን ዝናብ፣ ጠፋ፣ሳር እንኳን መብቀል እንቢ አለ፣ ህዝቡን ተጨነቀ ከዚያም ህዝቡ፣ ወጥቶ ስብሰባ አደረገ፡፡ ከዚያም ሞዋ የሚባለው ጎሳ ቢነግስ የተሻለ እንደሆነ ተስማምተው ወሰኑና የሞዋ ጎሳ የሆነ ወጣት ፈልገው ያነገሱሲሆን የመጨረሻው የንግስናውን በትረ ንግስና የጨበጠው የሞዋ ጎሳ እስከ 19ኛውመቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያስተዳድሩ ነበር፡፡

ተረክ30.

ወደ ንግስና ይመጡ የነበሩት በቀድሞ ከጋማ ጎሳዎች፣ በማስከተልም ከጌመሎ የነበረ ሲሆን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በሰፊው ወደ ንግስና ይመጡ የነበረው ከሞዋ ጎሳ ነበር፡፡ መስፈርቱም ህዝብ ማስተዳደር ይችላል ተብሎ እምነት የተጣለበት ሰው ከዚያው ጎሳ ይመረጣሉ፡፡ንጉሱ በነገሱ ጊዜ ዝናብ የዘነበ እንደሆነ ከብቶች ከወለዱ ያ ንጉስ የበረከት ንጉስ ነው፡፡ ይባላል በተቃራኒው ንጉሱ በነገሱ ጊዜ ዝናብ ከጠፋ ሰዎች ግጭት የሚፈጥሩ ከሆነ ያ ንጉስ መምራት እንደማይችል ለህዝቡ የሚበጀው ንጉስ እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ያም ንጉስ ለሰባት ዓመታት ይመራል ችግሩ ቀጣይ ከሆነ ከንግስና እንዲለቅ ይገደዳል፡፡ አለቅም ካለ ህዝቡ ከንጉሱ ጋር ተዋግተው ካስፈለገም ገድለው አስግደው ሌላ ያነግሳሉ፡፡

ተረክ 31.

ለንግስና የታጨው ሰው በአንገሪ ቤተ-መንግስት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ጡሩንባ ይነፋል፡፡ ቀጥሎም ያን ለንጉስነት የታጨውን ሰው ሰዎች በየተራ እያዞሉት ከርዋ ቀበሌ (ኤንኪ) ወደ ሚባል ቦታ ይዘውት ይሄዳሉ፡፡

እዛም ንጉስ ቀብቶ የሚያነግስ ታዋቂ ሰው ነበር፡፡ ከዚያም ሰዎች« ለንጉሱ ከብት ስጠው» ይሉታል ፡፡ ያም ሰው ይቆጣና« ጡሩንባ እያስነፋህ የመጣኸው ከብት እኔን ልጠይቅ ነው?» ብሎ ይቆጣል፡፡ ከዚያም ሰዎች እንዲረጋጋ ያደርጉትና ከራሱ ከብት አውጥቶ ያርድና ንጉሱን ለንግስና ይቀባል፡፡ ከዚያም ንጉሱ ከተቀባ በኋላ ወደ ቤተ-መንግስቱ መልሰው ይወስዱትና አዋጅ ተነግሮ ህዝቡ ንጉስ መንገሱን እንዲያወቅ ይደረጋል፡፡

ተረክ 32.

በዚያን ዘመን (በነገስታቱ) ዘመን የሚያመልኩት በዓዞ ነበር ይባላል ንጉሱ ለዓዞ መስዕዋት ያቀርቡ ነበር ይባላል፡፡ መስዋዕቱም ከብት ሲሆን ወደ ጊቤ ወንዝ ተኪዶ የከብቱ ከኋላው ሰኮናው በመጀመሪያ በጦር ይወጋል፤ ከጮኸ መስዋዕቱን አዞው ለመቀበል ፈቃደኛ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ከዚያም ያ ከብት ይታረድና ስጋው እኩል ይካፈላል፡፡ አንዱ ወገን ከበለጠ ወይም ካነሰ አዞው ሲጣልለት አይበላም ፡፡ ነገር ግን ለንጉሱና ለአዞው እኩል ከተከፈለ ዓዞ ይበላል ዓዞው ከበላ መስዋዕቱን ተቀበለ ይባላል፡፡ መስዋዕቱ ተቀባይነት ካገኘ ደግሞ በሃገሩ ላይ ሰላም ፣ ጥጋብ፣ በረከት ይሆናል ተብሎ ይታመናል የንጉሱ የንግስና ዘመንም የተሳካ ህዝቡን የሚጠቅም ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

ተረክ 33.

በዚያ ዘመን ንጉሱ በበቅሎ መንገድ ሲጓዙ ሰዎች ልብሳቸውን አውልቀው አደግድገው መሬት እየሳሙ ይሰግዱላቸውና አጅበው እስከ ቤተ-መንግስቱ ይሸኗቸዋል፡፡ ወደ ቤተ-መንግስት ውስጥ መግባት አይችሉም፡፡ ንጉሱ ግን የሸኟቸው ሰዎች እንዲገቡ ከፈቀዱ ይገባሉ፣ ከገቡ ደግሞ ንጉሱ ግብዣ ይጋብዟቸውና ስራ ካለ አሰርተዋቸው ይሸኛቸዋል ፡፡የንጉሱን ግብዣ እንቢ ማለት ቂጣ ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ የንጉሱን ግብዦ እንቢ የሚል የለም፡፡

ተረክ 34

የመጀመሪያው የሞዋ ጎሳ ንጉስ ታቶ ባላም (ንጉስ ባለወልድ) የነገሱት በግንቦት አንድ ቀን ነው ይባላል፡፡ ሕዝቡም እስከ አሁን ድረስ ያንን ቀን በጣም ያከብራሉ ይባላል የሚያከብሩትም በአካባቢያቸውትልቅ ዛፍ ስር ከብት ታርዶ፣ የቆጮ ድፎ ተጋግሮና የእንሰት ስር (አምቾ) ተቀቅሎ ይከበራል፡፡ የሚከበርበት ምክንያትም የንጉስ ባላም ፈጣሪ ዝናብ ያመጣል፣ በረከት ሰላም ያመጣል በሽታ ከሀገራችን ይርቃል ተብሎ ይታመናል በተጨማሪም በዚያን ቀን ጎተራቸውን፣ ቀፎቻቸውን ወ.ዘ.ተ ክፍት ያሳድራሉ ይህንንም የሚያደርጉት" የንጉስ ባላም"ፈጣሪ በረከት ይሞላል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ በአንዳንድ የሃገሪቱ አካባቢዎች ይህ ባህላዊ ስርዓት እስከ አሁንም ይደረጋል ሲሉ መረጃ ሰጪዎቹ ነግረውኛል፡፡



ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሰንበትና አቶ ገ/ሚካኤል ባልቻ፣በዚያን ዘመን ስለ ነበረው የንጉስባላም የልደት በዓል አከባበርና ስሚያደርጓቸው ባህላዊ ስነ ሥርዓቶች ማብራሪያ ሲሰጡ

ተረክ 35.

ታቶ ባላም (ንጉስ ባለወልድ) የነገሱበትን ቀን (አብዞጋር) ቀንን ማክበር እየቀረ መጥቷል ሰዎች እንደ ጎጂ ባህል እየቆጠሩና እየናቁ ማክበር ትተዋል፡፡ በድሮ ጊዜየአብዞጋር ቀን በሚከበርበት ወቅት የእንሰት ስር

(አምቾ) ተቀቅሎ በትልቅ ዛፍ ስር ይበተን ነበር ያ በሚደረግበት ዘመን እንሰት በጥሩ ሁኔታ ይበቅልና ይለመልም ነበር፡፡ በሀገሪቱ ላይ ረሃብ የለም ነበር፡፡ ያ ስርዓት ስለቀረ በአሁን ጊዜ የእንሰት ምርት በጣም ቀንሷል፡፡ ያለውም በእንሰት በሽታ እያለቀ ነው፡፡

ተረክ 36.

በመጀመሪያ የሞዋን ጎሳ ለማንገስ ከወሰኑ በኋላ የሞዋ ጎሳ ወጣት ሲፈለግ ጠፋ ይባላል ከዚያም "አስተሰሮች" የሞዋ ጎሳ የሆነ ወጣት አግኝቶ ያመጣ ይሸለማል ብለው ተናገሩ ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ (የዞፉፉጋ) ጎሳ የሆነች ሴት (ፉጋ) የሚባለው ጎሳ አባል የሆነች ሴት የሚሸጥ የሸክላ ዕቃ ተሸክማ "ኤሬቶ" ወደሚባል ቦታ ስትሄድ በመንገድ ላይ ሁለት ወጣት ወንዶች ጎድጓድ ቆፍረው በእንጨት ጦር ሰርተው ኢላማ እያለሙ ሲጫወቱ አንዱ ወጣት አልሞ ይመታና እኔ የሞዋው ልጅ እያለ ሲፎክር ሰምታ የደከማት በመምሰል ዕቃዋን አውርዳ ጥላ ስር ተጠቀምጣ ስትጠባበቅ ልጆቹ ጨዋታቸውን ጨርሰው ወደ የቤታቸው ሲሄዱ የሞዋ ልጅ እናት ዕቃ መርጣ ወስዳ እህል ትሰጣታለች፣ ሸክላ ሰሪዋም« በእህል አልቀይርም እኔ የምፈልገው ተልባ ነው» በማለት እንቢ ትላለች ከዚያም የልጁ እናት ተልባ አምጥታ ትሰጣታለች፡፡ ሸክላ ሰሪዋም ተልባውን ትቀበልና የተደፋባት በማስመሰል ተልባውን ደፍታ ቁጭብላ ስትለቅምና ሰፈሩን ስታጠና ትቆይና የወጣቱ አባት ከሄደበት ሲመለስ የሞዋ ጎሳ መሆናቸውን ጠይቃ አጣርታ ወደ አንገሪ ትመለስና ለአስተሰሮች የሞዋ ወጣት ማግኘቷን ትናገራለች፡፡ ከዚያም በማግስቱ አስተስሮቹ ብዙ ስጦታ ይዘው ይሄዱና የልጁን አባት በማስፈቀድ ልጅህን ልናነግሰው እንፈልጋለን በማለት አምጥተው አነገሱት ያ የሞዋ ጎሳ በነገሰ ዕለት ለ7 ዓመታት ጠፍቶ የነበረው ዝናብ ይዘንባል በዚህ ጊዜ ከፈጣሪ የተሰጠ ንጉስ እንደሆነ ታመነበት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አፄ ሃይሌ ዘመን ድረስ የሞዋ ንጉስ ሲመራ ቆይቷል፡፡

ተረክ 36.

በንጉሱ ዘመን ህዝቡ ስብሰባ ተጠራ ይባላል ከህዝቡ መሀል አንድ ሰው ሚስት ጠልፎ አግብቶ ስለነበር ንጉሱ የጠሩትን ስብሰባ ቀረ ይባላል፡፡ ከዚያም "አስተሰሮቹ" (የንጉሱ አማካሪዎች) በግድ እንዲመጣ ያስደርጉታል፡፡ በዚህ ንጉሱ «እንዴት እኔ የጠራሁትን ስብሰባ ንቀህ ትቀራለህ ብለው በቁጣ ጠየቁት» ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው «አይ ስብሰባውን ንቄ ሳይሆን አንድ ወርቅ አግኝቼ እንዳትጠፋብኝ እየጠበኳት ነው» ሲል መልስ ይሰጣል ይባላል፡፡ በዚህን ጊዜ ንጉሱ ገብቷቸው ቶሎ ፍቱትና ልቀቁት ብለው ለአንድ ወር ፈቀዱለት ይባላል፡፡

ተረክ 37.

አንድ ጊዜ "ኤሬቶ" በሚባል ቀበሌ አካባቢ በሁለት ጎሳዎች መካከል ግጭት ተከስቶ ሊበርድ አልቻለም፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሱ« እኔ ከሄድኩ ይበርዳል»፡፡ ብለው ሄዱ ይባላል፡፡ ተመልካቾች ሰዎችም ወደ ፀቦኞቹ ቀርበው «ኧረ አቁሙ ንጉሱ መጥተዋል»፡፡ ቢሏቸው« እሳቸውንም አንምርም ብለው» ወደ ንጉሱ ለፀብ ሲመጡ ንጉሱ ፈርተው ይመለሱና ወታደሮታቸውን ልከው እነዚያን የግጭቱን ፈጣሪ ሰዎች አስጠርተው በእስራት ቀጧቸው ይበላል፡፡ እና ንጉሱ እስከ ታች ወርደው ህዝቡን ይከታተሉና ይመሩ እንደነበር ይነገራል፡፡



አቶ ጌታቸው ተ/ማርያም ስለ ነገስታቱ ከህዝቡ ጋር ተቀራርቦ መስራት ማብራሪያ ሲሰጡ

ተረክ 38.

የጅማው ንጉስ አባጅፋር የየምን ህዝብ አጠቃለው ለመግዛትና ሙስሊም ለማድረግ በየም ልዩ ወረዳ "ቦሪ ተራራ" ላይ መስኪድ አሰርተው ህዝቡን ለማስለም ይነሳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ፊት አውራሪ ገ/መድህን አባጅፋር ወንድማቸውን ሊጥ አሸክመው አዲስ አበባ በመውሰዳቸው ተቀይመው እኔም ህዝቤም የእስልምንናን ሃይማኖት አንከተልም በማለት በእግራቸው አዲስ አበባ ድረስ በመሄድ ከዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ በማስፈቀድ የመድህኒዓለምን ፅላት በማስመጣት እሳቸውም ክርስትና ተነስተው ህዝባቸውም ክርስቲያን እንዲሆን አደረጉ ይባላል፡፡ ይህ ማለት የየም ህዝብ ሃይማኖት አልነበረውም ማለት ሳይሆን በጥንት ዘመን ከጎንደር የመጣው የሞዋ ጎሳ መሪ የነበረው የክርስትናን እምነት ይዞ መጥቶ ህዝቡ የክርስትና እምነት ተከታይ ነበር፡፡ ነገር ግን በግራኝ መሃመድ ጦርነት ጊዜ ቤተክርስቲያናቱና ታቦታቱ ተቃጥለው ወድመው ስለነበር ህዝቡ ወደ ኢአማኒነትና ባእድ አምልኮት/በአዞ፣በዛር፣በተራራ ወዘተ.../አምልኮውስጥ ተዘፍቆ ነበር፡፡

ተረክ 39.

የንጉስ ፊት አውራሪ ገ/መድህን ባለቤት ተገርዘው ስለነበር ወደ ቤተ-መንግስት ውስጥ አልገቡም ነበር ይባላል፡፡ በዚህም ምክንያት ከቤተ መንግስቱ ውጭ በሌላ እልፍኝ ውስጥ ነበር የኖሩት ይባላል፡፡ ምክንያቱም በዚያን ዘመን ነገስታቱ በዛር ያመልኩ ስለነበር እምነታቸው አይፈቀድም የንጉስ ሚስት አትገረዝም በዚህም ምክንያት የየም ሴቶች በሙሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይገረዙም በየም ብሄረሰብ ባህል ሴቶች አይገረዙም፡፡

ተረክ 40.

ሕዝቡ ነገስታቱን ከፈጣሪ የተሰጡ ናቸው በማለት አምነው ተቀብለው በቅንነት ይታዘዙላቸዋል ፤ይወዷቸዋል፤ በዚህም ምክንያት ንጉስ ሲሞት በቃል ግጥም እያወዳደሱ ያለቅሱ ነበር፡፡ ህዝቡ ንጉስ ከሞተ ሙሾ እያወረዱ እንዲህ ይላሉ፡-

በየምሳ ትርጉም በአማርኛ

አምኖቴ አምኖቴ ኬምናሴ… ንጉሳችን ንጉሳችን አይናችን

አምኖቴ አምኖቴ አፋይናሴ ….ንጉሳችንውሎ አዳራችን

አምኖቴ አምኔ በዝኒ… ንጉሳችን ጀግናችን እያሉ ለንጉሳቸው ያላቸውን ከበሬታ፣ ፍቅርና ታዛዥነታቸውን ይገልፃሉ፡፡

ተረክ 41.

በሞዋ ስርወ መንግስት ወደ ዘጠነኛው ይሁን አስረኛው ንጉስ ዘመን አንድ ቀን ንጉሱ የየጎሳውን መሪዎች አባ ጂጋዎች (ተወካዮች) ወደ ቤተ-መንግስት ለስብሰባእንዲመጡ ይጠሯቸዋል፡፡ ከዚያም የሁሉም ጎሳ ተወካዮች ሲገኙ የአንድ ጎሳ (ኮርቦ) የሚባል ጎሳ ተወካይ ሳይገኝ ይቀራል፡፡ ከዚያም ንጉሱ

«እንዴት የኔን ትዕዛዝ ንቆ ይቀራል» ይሉና ወታደሮች ልከው ያስመጡትና ይጠይቁታል፡፡ «ለምንድነው? ትዕዛዜን ያላከበርከው እኔ ነኝ እግዚአብሔር ነው? የሚበልጠው» ብለው ሲጠይቁት ያ የጎሳ መሪ «እርሶ ከእግዚአብሔር አይበልጡም» ብሎ መልስ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ‹‹ዛንሶ›› (ጥፋተኛ ተገፍትሮ የሚገደልበት ቦታ) ወስዳችሁ ገፍትራችሁ ግደሉት፡፡ ብለው ለወታደሮቹ ትዕዛዝ ይሰጣሉ በዚያን ጊዜ ወታደሮቹ ያን ሰው ወስደው ገደሉ አፋፉ ያቆሙትና ሊገፈትሩት ሲሉ «እባካችሁ ቶሎ እንድሞት ከኋላ ተንደርድራችሁ መጥታችሁ ገፍትሩኝ» ይላቸዋል፡፡ ወታደሮቹም እሺ ይሉና ወደ ኋላ ሄደው እየተንደረደሩ ሲመጡ እሱ ጎንበስ ብሎ ለጥ ይላል፡፡በዚህ ጊዜ ራሳቸው ገፍታሪዎቹ ወደ ገደሉ ውስጥ ተወርውረው ገብተው ይሞታሉ፡፡ በኋላም ያ የጎሳ መሪ ንጉሱ ዘንድ ይመለስና የእርሶ ወታደሮች በኔ ፋንታ ገደል ውስጥ ገብተው ሞተዋል ይላቸዋል፡፡ ንጉሱም በጣም ይፀፀቱና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ ቅጣት እንዲቀር አደረጉ ይባላል፡፡



የዛንሶ መገፍተያ ገደል/በነገስታቱ ዘመን የሞት ፍርድ የሚፈረድባቸው ሰዎች ተገፍትረው የሚገደሉበት/

ተረክ 42.

በንጉሱ ቤት የምትኖር ሴት አገልጋይ ነበረች፡፡ ከዕለታት አንድቀን ንጉሱ ቤት ውስጥ የሌሉ ወስዷት «ይህንን ንጉስ አመድ ያድርገው፡፡» ብላ ስትራገም ንጉሱ ሰሙና ብቅ ብለው« አሁን ምንድነው ያልሽው (የተናገርሽው?)» ብለው ቢጠይቋት አገልጋይቱም «ይህንን ጭምር የታገሰ ነው ንጉስ የሚባለው» ብላ መለሰችላቸው ይባላል፡፡ ሌላው ደግሞ ንጉሱ ለም የሆነውን የእርሻ መሬት ለመጤ ሰዎች እየሰጡ አስቸገሩና ህዝቡም በንጉሱ ላይ እንዲህ እያለ አጎረመረመ «እኚህን ንጉስ አልሚ እንበላቸው ወይስ አጥፊ እንበላቸው?» እያሉ ሲማረሩ ሰሙና ንጉሱም «ለካ እኔ እያጠፋሁ ነው?» በማለት ከዚያ ጊዜ ወዲህ ለጥፋተኞች ምህረት ማድረግ ጀመሩ ይባላል፡፡

ተረክ 43.

በፃድቁ ንጉስ ዮሐንስ ጊዜ እሳቸው ንጉስ፣ ንግስቲቱና የነፍስ አባታቸው ሆነው በጾም ጊዜ ዓሣ ተጠብሶ በማዕድ ቀርቦ ሲበላ ሳለ ንጉሱ« ከኛ መሀል እውነት የተናገረ ሰው ቢገኝ ይህ የተጠበሰ ዓሳ ነፍስ ዘርቶ ወደ ውሃው ይገባል»፡፡ብለው ሲወራረዱ ነፍስ አባታቸው« እኔ ንግስቲቱን በጣም ወደታለሁ ባገባኋትና ሁሉ በቀረብኝ» ብለው ይናገራሉ፡፡ ንጉስቲቱም «በጣም የሚወደኝ፣ ደስ የሚያሰኝ ወንድ ባለጌም፣ እረኛም፣ ቢሆን አግብቼው ቆሎ እየበላሁ በኖርኩ» ሲሉ ተናገሩ፡፡ በእነዚህ ጊዚያት ዓሳው ነፍስ አልዘራም፡፡ ፃዲቁ ንጉስ ዮሐንስ ደግሞ «የዚህ ዓለም እውቀት፣ ሐብት፣ ዘመን፣ ክብር፣ ጥበብ ወደ ማላይበት ሩቅ ጢሻ፣ አጥቂ፣ አራዊት፣ የበዙበት አራዊት ገዳም ገብቼ በጭንቅና በስጋት በኖርኩ» ብለው ሲናገሩ ያ የተጠበሰ ዓሳ ነፍስ ዘርቶ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ አንስተው በውሃ የተሞላ ገበቴ ውስጥ አኑረው በፍጥነት ወደ ወንዝ እንዲጣል አደረጉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዓሳ ቅዱስ ስለሆነ ዘሮቻቸው ጃንጀሮዎች ዓሳ አይበሉም ይባላል፡፡ አሁንም ድረስ ትልልቅ አዛውንቶች በየም ብሄረሰብ ዓሳ አይበሉም፡፡ የጊቤ ዓዞም የዓሳ ዘር ስለሆነ ቅዱስ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ መስዋትም በየዓመቱ ለዓዞው ያቀርቡ የነበረው በዚህ መነሻ ነው ተብሎ ይነገራል፡፡

ተረክ 44.

በየም ብሔረሰብ እስከ 300 ያህል ጎሳዎች ተወካዮች ከንጉሱ ጋር ተቀራርበው የተለያዩ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችንና አፈፃፀሞችን የሚከተል ሂደት የሚካሄድበት መዋቅር ያለው ነው፡፡ ማንኛውም የጎሳ አባላት በተወካዮቻቸው በኩል መብትና ግዴታቸውን ይተገብራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ የተቀበለው ስለሆነ ታዛዥነትና ከበሬታው ከፍተኛ ነው፡፡ ነገስታቱ ህዝቡን ያስተዳድሩ የነበረው በፊውዳላዊ ሥርዓት ደንብ አገዛዝ በመሆኑ የበላይና የበታች አስተዳደር ወይም አገዛዝ ላይ የተመሰረተ ነው አስገብረው በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ተረክ 45.

ባህላዊ አስተዳደር እንደነበርና ይህንን ንግስና ምህታታዊ ሃይል ያለውና ቅዱስ አድርገው ስለሚወሰዱና ለንጉሳቸው የማይታዘዙ ከሆነ መቅሰፍት እንደሚደርስባቸው በማስፈራራት ይገዟቸው ነበር፡፡ ህዝቡም ይህንኑ አምኖ ስለተቀበለ ለንጉሱ የሚሰጠው ክብር ከፍተኛ ንጉሱን ብቻ ሳይሆን የንጉሱን ጎሳዎች ጭምር እንደሚያከብሩ ይነገራል፡፡

ተረክ 45.

የአስተዳደር ስልቱ ፊውዳላዊ ስርዓት ነው፡፡ በንጉሱ አስተዳደር ስር ያሉት የብሔረሰቡን መሬቶች ተከፋፍለው በመሬቱ ላይ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን በጭሰኝነት እየጨቆኑ ግብር ያስገብሩና ሁሉን አቀፍ ስራ በማሰራት ጉልበታቸውን ይመዘብሩ ነበር፡፡ የጠላት መከላከያ ምሽጎች ያስቆፍሯቸው ነበር፣ ህዝቡም እንዲሁ እየሆነ ንጉሱን በታማኝነትና በቅንነት ይታዘዝ ነበር፡፡ ንጉሱ በመንገድ ሲያልፉም ልብሱን አደግድጎ መሬት ተደፍቶ እየሰገደ ታዛዥነቱንና ከበሬታውን ይገልፅ ነበር፡፡

ተረክ 46.

በባህላዊና በንጉሳዊ አገዛዝ ሥርዓት ያስተዳድሩ ነበር ህዝቡ ከአምላክ የተሾሙ አድርጎ ይቀበላል፡፡ ንጉሱም ህዝቡን ያከብራል፣ ህዝቡም ለንጉሱ

ይታዘዙ ነበር፣ በተጨማሪም ከየጎሳው ተመርጠው የተቀመጡ ሽንጎዎች አሉ፡፡ እነዚህ በቤተ-መንግስቱ ዙሪያ ሆነው ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በየቦታው የተሾሙ (እራሾ፣ ጋኛ፣ ጁጋ) የተባሉ የንጉሱ እንደራሴዎች ነበሩ፡፡ በህዝቡና በንጉሱ መካከል እንደድልድይ ሆነው የሚወጡ አዋጆችን መመሪያዎች ያስተላልፋሉ፣ ህዝቡን ከንጉሱ ጋር ያገኛሉ፡፡

ተረክ 47.

ነገስታቱ ይመሩ የነበረው በንጉሳዊ አገዛዝ ስልት ሲሆን በተዋረድ ደግሞ የየጎሳ ተወካዮች (አስተሰሮች) የሚባሉ የንጉሱ አማካሪዎች ያሉ ሲሆን አስተዳደራዊ ሚናቸውን ስንመለከት በማናቸውም ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ወደ ንጉሱ ከመድረሱ በፊት ተወያይተው የመፍትሂ አቅጣጫ በማስቀመጥ በእነርሱ አቅም የሚፈቱ ጉዳዮችን የመፍታት (የመምራት) ስራ ይሰራሉ፡፡ ካልሆነ ግን ከበድ ያለ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን ብቻ ለንጉሱ የማቅረብ ስራ ይሰራሉ፣ ንጉሱም ይወስናሉ፡፡ በዚህ መልኩ ነበር ነገስታቱ ህዝቡን ያስተዳደሩ የነበሩት፡፡

ተረክ 48.

ነገስታቱ የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንደነበራቸው የታሪክ አዋቂ አባቶች ይናገራሉ ሥርዓቱም በአስተሰሮች (ከየጎሳ የተወከሉ ተወካዮች) የሚመራ ሲሆን አስተሰሮቹን በበላይነት የሚመሩት (ታቶ) ንጉሱ ናቸው «አስተሰሮቹ»፣ ለ"ጋኛዎች " ለየጎሳ መሪዎች መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ "ጋኛዎች " በየጎጥ አመራሩ አማካይነት ለንጉሱ ግብር ያስገብራሉ፡፡ ህዝቡ ለንጉሱ እንዲገዛም ያስገድዳሉ፡፡ በእነዚህ አማካይነት ንጉሱ ህዝቡን ይመራሉ፡፡

ተረክ 49.

ነገስታቱ የሚመሩት በባህላዊ ሃይማኖት እንደመሆኑ ያለ አድሎ ነው የሚመሩት፡፡ ንጉሱ በስራቸው የህዝብ (የየጎሳ ተወካይ "አስተሰር " የሚባሉ እንደ ተወካዮች ምክርቤት ዓይነት ስራ የሚሰሩ አሉ፡፡ እነሱም ችግሮችን

በተዋረድ እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ የባህላዊ አስተዳደር ስርዓት ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት የመሳሰሉት ስላሉ አብዛኞቹ ችግሮች በእነዚህ ይፈታሉ፡፡ ከእነዚህ አቅም በላይ የሆነ ችግር ከገጠመ ብቻ ወደ ንጉሱ ደርሶ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

ተረክ 50.

ህዝቡ ለነገስታቱ በሚገባ ይገዛል፡፡ ምክንያቱም አምኖ የሰጣቸው ስልጣን በመሆኑ የላቀ ከበሬታ ይጣቸዋል፡፡ ከፈጣሪ እንደተሰጡ ተደርጎ ስለሚወሰድ የንጉሱ ትዕዛዝ መሬት ጠብ አይልም፡፡ ንጉሱም ለህዝቡ ያስባል ፡፡ህዝቡንም ይወዳል፡፡ እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ መሪኤራሾ፣ ጋኛ የሚባሉ አሉት፡፡ እነዚህም የጎሳ መሪዎችና የመንደር መሪዎች ናቸው፡፡ ህዝቡ በቀጥታ ከንጉሱ ጋር አይገናኝም ከአስተሰሮች---> ለጋኛ---> ከጋኛ---> ለኤራሽ--->ከኤራሾ ለህዝቡ መልዕክት (ትዕዛዝ) ይተላለፋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ከህዝቡ ግብርና እጅ መንሻ ለንጉሱ የሚደርሰው በእነሱ አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ንጉሱ ህዝቡን ይመራሉ፡፡ ከዚህ ደንብ የሚያፈነግጥ ካለ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡ ቅጣቱም "ዛንሶ " የሚባል ገደል ውስጥ ተገፍትሮ መሞት ነበር ይባላል፡፡

ተረክ 51.

በየም ብሔረሰብ እስከ 300 መቶ የሚደርሱ ጎሳዎች ያሉ በመሆኑ የሁሉም ጎሳዎች ተወካዮች ከንጉሱ ጋር ተቀራርበው የተለያዩ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችንና አፈፃፀሞችን የሚከታተሉበት ሂደት ያለ በመሆኑ የማንኛውም ጎሳ አባላት በተወካዮቻቸው በኩል መብትና ግዴታቸውን ይወጣሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ከንጉሱ በተዋረድ ከንጉሱ ጋር የሚሰሩ አካላት ያሉ ሲሆን እነሱ ጥያቄዎችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ወደ ንጉሱ ምላሹንም ወደ ህዝቡ ያደርሳሉ፡፡ በአጠቃላይ የንጉሱን ፍላጎት ያስፈፅማሉ፣ የህዝቡንም መብትና ግዴታ ተግባራዊ እንዲሆን ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡በአጭሩ ነገስታቱ ህዝቡን የሚመሩበት ስልት ከየጎሳዎቹ በተወከሉ ተጠሪዎቻቸው አማካይነት ትዕዛዞችንም ሆነ መልክቶችን በማስተላለፍ ሲሆን ህዝቡም ለነገስታቱ ያለው

ከበሬታና ታዛዥነት ከፍተኛ ነበር፡፡የየጎሳ መሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ በተዋረድም ለየጎሳ አባላቶቻቸው ከንጉሱ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ በዚህ መልክ ነበር የዱሮ ነገስታት ያስተዳድሩ የነበረው፡፡

ተረክ 52.

የጃንጀሮ አስተዳደራዊ መዋቅር በኮንፌደሬሽን ነበር፡፡ የጋራ መከላከያ ስርዓትና የጋራ የንግድ ኢኮኖሚ ትስስር ኖሮት የራሱ ንጉስ ያለው በራስ ባህል የሚተዳደር ስርወ መንግስት ነበር፡፡ በጻድቁ ንጉስ ዮሐንስ በትውልዳቸው ንግስና ዘመን ነበር፡፡ ንጉሱ በመንፈሳዊ እምነት መነኩሴና የነገስታት ንጉስ ስለሆኑ መንፈሳቸው ያያል ይቆጣል፡፡ በሚል ሕዝቡ በፍርሃት በማክበር ይታዘዝላቸው ነበር፡፡ በዚህ የንግስና ስርዓት ከንጉሱ ቀጥሎ አስተሰር፣ ናግተሰር፣ ቱምታሰር፣ ፋሪታሰር፣ ፎንታሰር፣ ሜንታሰር፣ ፍላታሰር፣ ተብለው እያንዳንዳቸው ከተለያዩ ጎሳዎች ሰባት ሰባት አባላት ያሉት ከንጉሱ ጋር የሚሰሩ የበታች አመራሮችም ያሉበት የአስተዳደር ስርዓት ነበራቸው፡፡

አስተሰር ⟶ የአስራ ሁለትጎሳዎች ተወካዮች

ሜን ታስር ⟶ የጦር አዛዦች

ፎን ታሰር ⟶ የኑሮ ዘዴ ቀያሾች

ቱም ታሰር ⟶ ህግ አውጪዎች

ፍላ ታሰር ⟶ ነፃ አውጪዎች

ፋራ ታሰር ⟶ አዳዲስ ነገር ፈጣሪ

ያንግ ታሰር⟶ የሕዝብ ምክርቤት ተወካዮች ከእነዚህ ውጪ በርካታ በየጎጡ (መንደሩ) ባህላዊ ዳኞች ይገኙ ነበር እነዚህ አካላት አሁንም ድረስ አሉ፡፡ማለትም ባህላዊ ደኞች፣ ጂጋ፣ ሸኒ የተባሉት አሁንም በየመንደሩ የ1ለ5

መሪ ሆነው ያገለግላሉ፣ ዳኞቹም በሕዝቡ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በመፍታት ያገለግላሉ፡፡

ተረክ 53.

ነገስታቱ ህዝቡን ይመሩ የነበረው በባህላዊ አስተዳደር ሲሆን አሁን ላለው ዘመናዊ የመንግስት አወቃቀርም እንደ ምሳሌ ያገለግላል ማለት ይችላል፡፡ ይህምማለት ንጉሱ በስራቸው ባሉ ተዋርዳዊ የአስተዳደር እርከኖች አማካይነት ነው፡፡ እሳቸው ከበላይ ሆነው የሚመሩት ከንጉሱ በታች አስተሰሮች አሉ (የየጎሳው ተወካዮች) እነዚህ እንደ ፓርላማ አባላት ነው፡፡ ስራቸውን የሚያከናውኑት ንጉሱ በራሳቸም ምንም ውሳኔ አይወሰኑም፡፡ አስተሰሮች ከህዝቡ ጋር በወያየት ነው ንጉስ እንኳን የሚሾሙት፣ እነዚህ አስተሰሮች ትልቅ ስልጣን ነው የነበራቸው፡፡ ሌላው ህዝቡን በጥንቃቄና በፍቅር ነው የሚመሩት ህዝቡ አምኖ ነው የሚገዛላቸው ሲሞቱ እንኳን ህዝቡ "ኪምኒ ቲሹ " አይናችን ጠፋ እያሉ ህዝቡ በሙሉ ፀጉራቸውን ተላጭተው ያዝኑላቸው ነበር፡፡

ተረክ 54.

አስተዳደሩ ጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት መልክ ሆኖ እስከ 1900 ዓ.ም የቆየና ከ 16ኛው መ/ ክፍለ ዘመን አንስቶ ወደ ባለባታዊ ስርዓት የተሻገረ ሲሆን የበላይና የበታች አስተዳደር ያለበትና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው በጭቆና ነበር ያስተዳድሩ የነበረው፡፡ ሌላው ደግሞ ከነገስታቱ የሚወከሉ መሪዎች ከጎሳው ዘር ሀረግ ስለሚወከሉ ህዝቡን ከንጉሱ በላይ የሚጨቁኑ ናቸው፡፡

ተረክ 55.

ነገስታቱ ህዝቡን የሚመሩበት የአስተዳደር ሥርዓት ንጉሳዊ ሆኖ ግን የማስተዳደሪያ ስልቱም የህዝቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ የተባለበት ምክንያት አንዱ ጎሳ በሌላው ጎሳ ላይ በደል እንዳያደርስና በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና፣ ፖለቲካዊ አጠቃቀም ላይ አድልዎ /በደል/

እንዳይኖር ተዋረዳዊ የአስተዳደር መዋቅሮች በመዘርጋት ውሳኔዎች ከታችኛው መዋቅር እስከ አስተሰሮች (የየጎሳ ተወካዮች) ደርሰው በአስተሰር ሰብሳቢ ወይም «ዋሶ» አማካይነት ለንጉሡ ደርሶ ይፀድቃል፡፡ የውሳኔው ሁኔታ የሚያጠራጥር ከሆነ ንጉሱ እንደገና እንዲታይ ያደረጋል፡፡ ማሻሻያም ተደርጎ ይፀድቃል፡፡

የአስተዳደር መዋቅሩም ከላይ እስከታች ሲሆን አምኖ/ታቶ/ንጉሥ- አስተሰሰሮች ናንቴሰር ከዚያ ሜንቴሰር ከዚያ ፋንቴሰር ከዚያ ፍላቴሰር ከዚያ ቱምቴሰር ከዚያ ፉራቴሰር የሚባሉ ሲሆኑ ከሜንቴሰር እስከ ፉራቴሰር ያሉት መዋቅሮች በስራቸው 7 አባላት እያንዳቸው ያላቸው መዋቅሮች ናቸው፡፡

ተረክ 56.

በየም ብሄረሰብ ከ300 ጎሳዎች አንድ ጂጋ የሚሆነው ብቻውን 1000 ከሞላ ነው ካልሞላ ጎሳ ከሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ጎሳዎች አንድ ጋር እየሆኑ 1000 (አንድ ሺህ) አንድ ጎሳ ሆኖ ይደራጃል፡፡ ይህም የጎሳ አደረጃጀት ያስፈለገበት ምክንያት የሰው ብዛት ያለው ጎሳ አነስተኛ ቁጥር ባለው ጎሳ ላይ በደል እንዳያደርስ ተብሎ ነው፡፡ ይህ የጎሳ አደረጃጀት ከ12ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረና የቆየ ባህል የነበረ መሆኑን የታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተደራጁ ከ160/ ከአንድ መቶ ስልሳ/ በላይ ጂጋዎች እንደነበሩ ይናገራል፡፡ ራሳቸውን ችለው ከ1000(አንድ ሺህ) አባላት በላይ ኖሯቸው ጂጋ ሆነው የተደራጁ ጎሳዎች ጋማ፣ ሞዋ፣ ሀማ፣ የሱ፣ ጋዜውና ፉጋ ሲሆኑ ሌሎቹ ጎሳዎች አባላቶቻቸው ሺህ ስለማይሞሉ ከሁለት እስከ ሰባት ጎሳዎች በአንድ ላይ እየተቀናጁ ጂጋ እየመሰረቱ ነው 160 ጂጋ የሆነው የጂጋ መሪ አመራረጡ ካሉት ጎሳ መካከል ተሰሚነት ያለው (ተፅዕኖ ፈጣሪ) የሆነ በጎሳዎች መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር ማስተካከልና መምራት የሚችል በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰው ይመረጣል፡፡ አንዱ ጎሳ በሌላኛው ጎሳ ላይ በደል ቢያደርስ የሚዳኘው በአባ ጂጋው አማካኝነት ነው፡፡ በደል የደረሰበት ጎሳ አቤቱታውን የሚያቀርበውም ለአባጂጋው ሲሆን አባጂጋውም ግንኙነቱ በደል አድራሹ ጎሳ ላለበት ጂጋ ይሆናል፡፡ ሁለቱም ጂጋዎች

ከተነጋገሩ በኋላ የበደሉ ሁኔታ የሰው ህይወት የጠፋበት ከሆነ አስተሰሮች ጭምር እንዲገኙ በማድረግ የበዳይና የተበዳይ ቤተሰብ በተገኙበት የእርቅ ስነ-ስርዓት ይፈፀማል፡፡ የእርቅ ስነ-ስርዓቱ ዝም ብሎ የሚፈፀም ሳይሆን በዳዩ ጥፋቱን አምኖ ተፀፅቶ ከብት እንዲሰጥ ተደርጎ ያ ከብት ይታረድና የከብቱ አንጀት ተለይቶ ከወጣ በኃላ የበዳይና የተበዳይ እግር አወራ ጣት ይታሰራል፡፡ ይህም የሚደረገው ያለፈውን ቂምና በቀል ረስተው ፍቅርና አንድነት እንዲሰፈንና ፍፁም እርቅ እንዲወርድ ተብሎ ይታመናል፡፡ በተጨማሪም በዳዩ ለተበዳዩ ስምንት ክንድ መቀነትና ነጭ ቡልኮ ይገዛለታል እንጂ በዳይ በገንዘብም ሆነ በዓይነት የሚከፍለው ካሳ አይኖርም፡፡ ከዚህ የምናየው ነገስታቱ ከታች ባሉ ተዋረዳዊ መዋቅሮች አማካይነት ህዝቡን የሚመሩበት መዋቅር እንዳለ ነው እስከ አሁንም የሚታወቀው፡፡

ተረክ 57

የአዞ አምልኮ ስርዓት መጀመር መንስኤ የሆኑት የተለያዩ አበይት ምክንያቶች አሉ፡፡ የየም ህዝብ የእናሪያ ነገድ ነው፡፡ የእናሪያ ህዝብ በ1270 ዓ.ም.ክርስትና ሃይማኖት ተቀብሎ ብዙ አቢያተ ክርስቲያናትን የሃይማኖት መሪዎች ነበሩት፡፡ በ1515 ዓ.ም. በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜ በወቅቱ የነበሩት ቤተ-መቅደሶች፣ ቅዱሳት መጻህፍት እንዳልነበሩ ሆኖዋል፤ ተዘርፈዋል፤ ተቃጥለዋል፤ የሃይማኖት መሪዎችም እየታደኑ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የየም ብሔረሰብ አረማዊ በመሆን በአዞ፣ በዛፍ፣ በተራራ፣ በወንዝ፣ በደን፣ በፀሐይና በጨረቃ ማምለክ ጀመሩ፡፡ የየም ብሔረሰብ በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በግልና በቡድን የጊቤን ወንዝ ተሻግሮ በመምጣት እንደሰፈረ ይነገራል፡፡ በአንድ ጊዜ ባላም፣ዋዛም፣ ፉጋተስቶና ሶኦላ የተባሉ ዘሮች አብረው የጊቤን ወንዝ ሲሻገሩ የሶኦላ ዘር/ጎሳ/አባል ደክሞት ስለነበር የጊቤ ወንዝ ወሰዳቸውና በወሃ ውስጥ የነበሩ በአዞዎች ወይም በዘንዶዎች ይበሉ አይበሉ ሳይታወቅ ዱካቸው ስለጠፋ ብቻ የቀሩት ሰዎች የእህል ስንቅ ወደ ወንዙ ቢወስዱ የሚቀበላቸዉ ጠፋ፡፡ በድጋሚ የከብት ስጋ እንዲሰጥ ቢደረግ አዞ ወጥቶ በመቀበል ለሶኦላ፣

ለዲቻንጉ፣ለገበና፣ ለገመሎ፣ለካንሽሮ፣ለከሞሶ....ዘሮች የአምልኮ ጣዖት ሆነ ይባላል፡፡

ሌላው ባለወልድ ከነጓደኞቻቸው ከጎንደር ሲመጡ እንብርታቸውንና የተቆረጠበትን ምላጭ ኦና ከሚባለዉ እንጨት በተሰራዉ ሳጥን ውስጥ ጨምረው ያቆዩትን አሸከመው የጊቤን ወንዝ ሲሻገሩ በእንብርቱ ውስጥ ትል ይፈጠርና በውሃ ውስጥ ይወድቃል፡፡ ባለወልድም ወንድሜ በውሃ ውስጥ ስለወደቀ በየወሩና በየዓመቱ የከብት ግብር መስጠት አለበት ይላሉ፡፡ ስለዚህ በአካባቢው አፈ ታሪካዊ አመለካከት ባላምና ዓዞ ወንድማቾች ናቸዉ ይባላል፡፡ በሳጥኑ ውስጥ የነበረው ምላጭ ናቲሲ በሚባል ቦታ ላይ ተቀበረ፡፡ ባለወልድ ከመምጣቱ በፊት የኣዞ አምልኮ በብሔረሰቡ ዘንድ አልነበረም ይባላል፡፡

ሌላው ለዓዞ አምልኮ ሌላው ምክንያት ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በብሔረሰቡ ዘንድ አደን የተለመደ በመሆኑ በህብረት ወጥቶ በማደን ይመለሱ ነበር፡፡ በህዝቡ ባህላዊ የአደን ስርዓት መጀመሪያ የወጋ ነቀላ፣ ውለተኛ የወጋ ሽንጥ፣ ተከታትሎ የደረሰ እንደየ አመጣጡ ስጋ ስለሚያገኙ ለዚሁ በሚደረገውየውጊያ እሽቅድድም ውስጥ እኔ ነኝ መጀመሪያ የምወጋው በሚሉ በሁለት ሰዎች መካከል በሚፈጠረው አለመስማማት የአዳኞች ክስ ሰሚ ዳኛ ዘንድ ቀርቦ መተማመን ካልቻሉ የተወጋውን የእንስሳት ስጋ ሁለቱ ባለጉዳዮች የየራሳቸዉን የአምልኮ ጣዖት እየጠሩ ዓዞ ወዳለበት ውሃ ውስጥ ተራ በተራ ይጥላሉ፡፡ ስጋውበውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ከሄደ ዓዞው ተቀብሎ አልበላምና የመጀመሪያው ወጊ አይደለም፣ ስጋው ሲወረወር ውሃ ውስጥ የጠለቀ ከሆነ ኣዞውበውሃ ውስጥ ሆኖ ተቀብሎታልና ክሱን በመርታት የኋላ ነቀላ ስጋ ይወስዳል፡፡

አዳኞች የጊቤን ወንዝ ተሻግረው ስለሚያድኑ ያገኙትን የእንስሳት ስጋ ልቡን፣ ኩላሊቱን ወ.ዘ.ተ በማውጣት ለዓዞ ከምስጋና ጋር ይሰጣሉ፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በረሃውን እያቋረጡ ሲያድኑ ከመጥፎ አደጋ ሁሉ ጠብቆን ብዙ ስጋ እንድናገኝ የረዳን እሱ ነዉ ይላሉ፡፡ በተለይ ከጊቤ ማዶ የሚገኙ ጉራጌና የሃዲያ ብሔረሰቦች ወንዙን ተሻግሮ ከየም ብሔረሰብ ጋር

እየተመላለሱ ስለሚነግዱ በጓደኛሞች መካከል የመካካድና መሃላን ያፈረሱ ቂመኞች አብረው የጊቤን ወንዝ ለመሻገር በዳርቻው ሲደርሱ ዓዞውበውሃ ላይ እየተንሳፈፈ መሻገር ስለሚከለክላቸው የቃል ኪዳን ጓደኛሞች በአንድነት ተሰብስበው ይህ ጥፋት ከማን እንደሆነ ተጠይቆ ጥፋተኛው ጥፋቱን አምኖ የበደለውን ወንድም ካሳ ክሶ ወይም ለመካስ ቃል ከገባ በኋላ እያዩት ዓዞው ከአካባቢዉ እየተንሳፈፈ ይሄድላቸውና መሻገር ይጀምራሉ፡፡ነገር ግን ጥፋተኛዉ ጥፋቱን ባለማመን በውሃ ውስጥ ሊሻገር ከገባ ዓዞው እግሩን ወይም እጁን ሰብሮ ይጥላል፡፡ ይህ ሰው ከውሃ ወጥቶ ሰፈሩ ደርሶ ጥፋቱን ካመነ ይድናል፡፡ ከባለጋራውም ጋር ይቅርታ ጠይቆ የበደለውንም ክሶ ይታረቅና አምኖ በውሃ ውስጥ እንደገና ገብቶ ይሻገራል፡፡ ቂም ያለባቸው ሰዎች ቅራኔያቸውን ሳይፈቱ አምነውበውሃ ዉስጥ ገብተው አይሻገሩም፡፡ የአካባቢው ሰዎችም እነዚህን ድርጊቶች በማየት እውነተኛ ፈራጅ አምላክ በውሃ ውስጥ እንዳለ በማመን ማንኛውም በማህበራዊ ኑሮአቸዉ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች (በአጋጣሚ ሲፈጸም) የተባሉትን ጥጃ ወስደው በማሳረድ መስዕዋት ማቅረብ ጀመሩ ይባላል፡፡

ተረክ 58.

የየም ብሔረሰብ እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጥንታዊ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋና እምነት ያለው ህዝብ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከደቡብ አረቢያ /የመን/ አካባቢ ፈልሶ ወደ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ (ጎንደር) ልዩ ስሙ «ፎገራ» በሚባል አካባቢ ይኖር እንደነበር እና በ12ኛዉ መ/ክ/ዘ/ ወደ ደበብ ምዕራብና መካከለኛው ኢትዮጵያ /የአሁኑ የም ልዩ ወረዳ / እንደ መጣ በአፈታሪክ ይነገራል፡፡ከየመን ፈልሶ ሲመጣ መሪ ሆኖ ወደ አካባቢው መርቶ ያመጣው መሪ ሼ ዱንቡል የተባለ የእስልምና እምነት መሪ እንደነበረና የእኚህ ሼኪ መቃብር እስካሁን በየም ልዩ ወረዳ በኢዲያ ቀበሌ ልዩ ስሙ መሊሳ በተባለ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ሌላው አፈታሪክ ደግሞ መሪው ባላም ይባል ነበር ይባላል፡፡በታሪክ መፅሐፍት አገላለፅ በሼ ዱንቡል ዘመን የየም ህዝብ በጥንታዊው የኢናሪያ መንግስት አካል እንደነበር ነው፡፡ የኢናሪያ መንግስት በሊሙ ኢናሪያ /ኦሮሞ/ ፍልሰት ሲተካ ህብረ-ብሔር

የነበረው የኢ.ናረ.ያ መንግስት  ገሚሱ ወደ አሶሳ/ቤንሻንጉል ጉሙዝ/፤ ሌላው ወደ ደቡብና ቀሪው ወደ ምዕራብ /ከፋ፣ሼካ፣ቤንች...ወዘተ/ እንደተበታተነ ይገመታል፡፡

ለዚሁ ማረጋገጫ የሚሆነው በኢ.ናሪ.ያ ስር የነበሩ ብሔር ብሔረሰቦች ንጉስ መጠሪያ ታቶ ተብሎ የጋራ መጠሪያ መሆኑ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በየምኛ በከፋ፣ በዳውሮ፣በወላይታና በመሳሰሉት አካባቢዎች ንጉስ ማለት «ታቶ» ተብሎ ይጠራል፡፡ በኢ.ናሪ.ያ ዘመንም የጋራ መሪ/ጠቅላይ ሚኒስትሩ /ኢ.ናሮ ታቶ/ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡

ተረክ 59

የባሕላዊ ንግስናን በተመለከተ ንጉሱ በሞተ ጊዜአስተሰሮቹ የንጉሱን ልጆች ይሰበስቧቸዋል፡፡ የንጉሱ ልጆች 30ም 40ም ሊሆኑ ይችላሉ፤እናቶቻቸውም ቀርበው ከንጉሱ እንደወለዷቸው ይናገራሉ ከዚ.ያም ልጆቹን አንድ ቦታ ላይ ሰብስበው ያስቀምጧቸውና ብዙ ከብትም በየዓይነቱ ያርዳሉ፤የጠሰበሰበው ሕዝብም ከልጆቹ 2 ሺህ ክንድ ራቅ ብለው ይቆሙና ከልብ እየጮሁ በልዩ ልዩ ዜማ እየዘፈኑ ይጨፍራሉ፡፡ጩኸቱና ዘፈኑ እየቀለጠ ሲ.መጣ ዘንዶው ከጎሬው መሰስ ብሎ ይወጣና ከፈሰሰው ደም ይቀምስና ወደልጆቹ በመሄድ ከልጆቹ መሃል በአንዱ ላይ ይጠመጠማል ከዚ.ም ቀሪዎቹ ወንድሞቹና የተሰበሰበው ህዝብ ለዚ.ያ ልጅ ንጉስ ሆነ ብለው  በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱለታል፤ከዚ.ያ በኋላ በዛር መንፈስ ቀቢ.ው(ንግስናውን የሚሾመው ዘንዶ ከዚ.ያ ንጉስ ላይ ተተርትሮ ወርዶ ይሄደና ወደ ጎሬው ውስጥ ይገባል ከዚ.ያም ንግስና የተቀባውን ወጣት ህዝቡ ተነሳ ይሉትና ወንድሞቹም ጭምር ተደፍተው ይሰግዱለታል፤የስግደቱን ስርዓት ከፈጸሙ በኋላ የታረደው ስጋ ይበላል የተረፈው እዚ.ያው ይጣላል እንጂ ወደ ቤት አይሄድም ይህ ወጋቸው ነው፡፡

ተረክ 60

የየም ብሔረሰብ አመጣጥን በተመለከተ ከየመን ፈልሶ ሲ.መጣ መሪ ሆኖ ወደ አካባቢ.ዉ. መርቶ ያመጣዉ. መሪ ሼ ዱንቡል የተባለ የእስልምና እምነት

መሪ እንደነበረና የእኚህ ሼኪ መቃብር እስካሁን በየም ልዩ ወረዳ በኢዲያ ቀበሌ ልዩ ስሙ መሊሳ በተባለ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ሌላዉ አፈታሪክ ደግሞ መሪዉ ባላም ይባል ነበር ይባላል፡፡በታሪክ መፅሐፍት አገላለፅ በሼ ዱንቡል ዘመን የየም ህዝብ በጥንታዊዉ የኢናሪያ መንግስት አካል እንደነበር ነዉ፡፡ የኢናሪያ መንግስት በሊሙ ኢናሪያ /ኦሮሞ/ ፍልሰት /movement/ ሲተካ ህብረ-ብሔር / multi-nation/ የነበረዉ የኢናረያ መንግስት ግሚሱ ወደ አሶሳ/ቤንሻንጉል ጉሙዝ/፣ ሌላዉ ወደ ደቡብና ቀሪዉ ወደ ምዕራብ /ከፋ፣ሼካ፣ቤንች...ወዘተ/ እንደተበታተነ ይገመታል፡፡ለዚሁ ማረጋገጫ የሚሆነን በኢናሪያ ስር የነበሩ ብሔር ብሔረሰቦች ንጉስ መጠሪያ ታቶ ተብሎ የጋራ መጠሪያ መሆኑ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በየምኛ በከፋ፣ በዳዉሮ፣በወላይታና በመሳሰሉት አካባቢዎች ንጉስ ማለት ታቶ ተብሎ ይጠራል፡፡በአፈታሪክ በሰፊዉ ይነገራል፡፡

ተረክ 61.

የየም ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ በሁለት ይከፈላል፡፡እነሱም ነባርና ከተለያዩ ሃገራት መጥተው ወደ አሁኑ ቦታ የሰፈሩ በመባል ይታወቃል፡፡ከጥንት ጀምረው እዛው በየም ምድር የሰፈሩት «ጀነን» ወይም «ጀኮርድነን» በማለት ራሳቸውን ይጠራሉ፤ትርጉሙም ነባር ከጥንት ጀምረው የነበሩ ማለት ነው ወይም የዘር ሐረጉ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንደ ማለት ነው፡፡ሌላው ከተለያዩ ሃገራት ወደዚህ መጥተው ከነባሩ ህዝብ ጋር የተቀላቀሉት ከእስራኤል፣ከየመንና ከደቡብ አረቢያ የመጡ እንደሆኑ ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ፤እነዚህ ከሌሎች ሃገሮች ወደ አሁኗ የየም ምድር የመጡት የየም ጎሳዎች የዴዴሳንና የጊቤን ወንዞች ተከትለው መጥተው የሰፈሩ እንደነበር ይነገራል፡፡ እናም ግዛታቸው ከጊቤ ወንዝ እስከ ጎጀብ ወንዝ ድረስ እንደነበርና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኦሮሞዎች የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴ ምክንያት ግዛታቸው እንደተወሰደና እየጠበበ መጥቶ የሁኑ እንደቀረ ይነገራል «ጊቤ» የሚለውን የወንዝ ስያሜ የሰጡት ከእስራኤል ሃገር ወደ አሁኗ የየም ምድር የመጡት ጎሳዎች በመጀመሪያ ጎንደር ገብተው ጎንደር ላይ የመታሰቢያ ዛፍ በመትከል ወደዚህ

የመጡት«ዋዛም፣ ፋጋቴስቶ፣ ጎልማሸና ባለወልድ የተባሉት ወንድማማቾች የጊቤን ወንዝ ተሻግረው ከመጡ በኋላ ነጭ መልካቸው ወደ ጠይምነት ስለ ተቀየረ የወንዙን ስያሜ «ጊቤ»ትርጉሙ «ማዲያት» ማለት እንደሆነ አባቶች ይናገራል፡፡ እነዚህ ጎሳዎች ወደዚህ ምድር የመጡ ጎሳዎች ሲሆኑ ወደ አሁኗ የየም ምድር ሲመጡ ክርስትናንና 44 ታቦታትን ይዘው መጥተው በዚህ ቦታ ክርስትናን እንዳስፋፉ ይነገራል፡፡የአንገሪ ቤተ መንግስት መስራችም ከነዚህ መካከል «ባለወልድ» የሚባሉት እንደሆኑ ይነገራል፡፡

አባሪ 3

የቃለ መጠይቅ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. በአንገሪ ቤተ-መንግስት ይነግሱ የነበሩ ነገስታት ወደ ንግስና እንዴት ይመጡ ነበር? መስፈርቱ ምን ይመስላል?

2. በየም ብሄረሰብ ምን ያህል ጎሳዎች እንዳሉ ይታወቃል?

3. ከየትኞቹ ጎሳዎች ወደ ንግስና ይመጡ ነበር? ምክንያቱ ምንድነው?

4.ነገስታቱ ከሚመረጡባቸው ጎሳዎች ከአመራረጥ ሂደቱ፣ከሚከናወኑት ስርዓቶች ጋር ተያይዘው ይነገሩ ከነበሩ አፈ-ታሪኮችና ተረቶች መካከል የሚያውቁትን ቢነግሩኝ፡፡

5. እነዚህ አፈ-ታሪኮችና ተረቶች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምንድነው? ባህላዊ እሴቶችን ከማስቀጠል አንጻርና ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ምንድነው?

6. በወቅቱ የነበሩት ነገስታት ህዝቡን ያስተዳድሩበት የነበረው የአመራር ጥበብ ምን ይመስል ነበር

አባሪ- 4

## የጥናቱን አካባቢ.ያዊ ገጽታየሚ.ያሳዩ ፎቶ ግራፎች





የአንገሪ ታሪካዊ ቤተ መንግስትየነብርቆዳየሚገፈፍበትቦታበቤተ-መንግስቱዙሪ




አስራ ሁለተኛው የሞዋ ጎሳ ንጉስ ጌራዋ/ፊት አውራሪ ገ/መድህን





ለመስዕዋትየቀረበ በሬ

ለዓዞ መስዕዋት የሚቀርብበት ቦታ የጊቤ

ወንዝ




ለዓዞ መስዕዋት ማቅረቢያ ገበቴ



ዛንሶ የወንጀለኛ መገፍተሪያ ገደል



ለዓዞ መስዕዋት አቅራቢዎች (ማግ)

## ማረጋገጫ

የየም ብሔረሰብ የአንገሪ ቤተ መንግስት ባህላዊ የንግስና ስርዓአመጣጥ ተረኮች ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያነት ያዘጋጀሁት ይህ ጥናት የእኔ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡-----------------------------------------------------------

ፊርማ፡---------------------------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን፡-----------------------------------------------